

ነገ እስኪነጋ... ገጽ 16

ኢትዮጵያዊ ቀለም ካለው የስፌት ሥራ የተወዳጀች ወጣት ገጽ 13


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 077 ኅዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## የወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ጉዳይ የአፍሪካ ቀዳሚ አጀንዳ መሆኑን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ተናገሩ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- የአፍሪካን መጻኢ እድል ብሩህ ለማድረግ እና የተሻለች አፍሪካን ለመፍጠር የአፍሪካ መሪዎች የወጣቶችን ጉዳይ ቀዳሚ አጀንዳ በማድረግ መሥራት እንዳለባቸው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ተናገሩ።

አቶ ደመቀ በኒያሚ ከተማ እየተካሄደ ካለው 17ኛው የአፍሪካ ኅብረት ልዩ ጉባኤ ጎን ለጎን የአፍሪካ ኤሌክትሮኒክስ ግብይት መድረክ ላይ በመገኘት ባደረጉት ንግግር የወጣቶች የሥራ እድል ፈጠራ ጉዳይ የአህጉሪቷ ቀዳሚ ጉዳይ መሆኑን ጠቁመዋል።

አክለውም የኤሌክትሮኒክስ ግብይት እና ሌሎችም መሰል ውጥኖች በአፍሪካ ኅብረት አባል ሀገራት ሊደገፉ እንደሚገባ ጠቅሰው ከዚህ አልፎም ግብይቱ የምርጥ ተሞክሮ ማሳያ ሊሆን እንደሚገባ ተናግረዋል።

አፍሪካ በዓለም አቀፉ ዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ ፍትሐዊ ድርሻዋን ማግኘት አለባት ያሉት አቶ ደመቀ ይህ ካልሆነ ግን የአፍሪካ ሕዝቦች ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ነፃነት ሊያገኙ አይችሉም ብለዋል።

የአፍሪካን ችግሮች በአፍሪካ ለመፍታት እና አፍሪካውያን ጥበብን ለማሳደግና ለመጠበቅ ተመሳሳይ የዲጂታል ተሞክሮዎች ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑንም አቶ ደመቀ ገልጸዋል፡፡


የወጣቶች የሥራ ዕድል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







## መንግሥት ሰብዓዊ እርዳታን ለማዳረስ እያደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ መሆኑን የኮረም ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ

### - የውጭ ድርጅቶች አስቸኳይና ቀጣይነት ያለው እርዳታ እንዲያደርሱም ተጠይቋል

ሞገስ ጸጋዬ

ኮረም፡- መንግሥት የሰብዓዊ ርዳታን ለማዳረስ የሚያደርገው ጥረት የሚደነቅ መሆኑንና ካለው ከፍተኛ የተረጂ ቁጥር አንጻር የውጭ ድርጅቶች አስቸኳይና ቀጣይነት ያለው ርዳታ እንዲያደርሱ የኮረም ከተማ ነዋሪዎች ጠየቁ።

የኮረም ከተማ ነዋሪ አቶ መሳይ ገብረሥላሴ ለኢፕድ እንደገለጹት እርዳታ እየደረሰን ነው፣ ይሁንና ከተማዋ ለሁለት ዓመት ያህል በጦርነት መቆየቷን በመረዳት ከመንግሥት ጥረት በተጨማሪ የውጭ ረጂ ድርጅቶች አስፈላጊው እርዳታ ሊያደርጉ ይገባል ብለዋል። የእርዳታ ስርጭቱ በጣም ፍትሐዊ ከመሆኑም በላይ የተቸገረ ሁሉ በሥርዓቱ እየተረዳ ነው ያሉት አቶ መሳይ የባንክ አገልግሎት ክፍት ባለመሆኑ ችግሩን ለማቃለል ክፍት እንዲደረግ ተማጽነዋል።

ሌላዋ አስተያየት ሰጪ በላይነሽ ከበደ በበኩሏ፣ ችግራችንን ተገንዝቦ መንግሥት ፋፋና ስንዴ እያቀረበልን በመሆኑ የኮረም ከተማ ነዋሪዎች ተደስተናል። መንግሥት ሕዝቡን ለመርዳት የሚያደርገው ጥረትም ትልቅና የሚደነቅ ነው። ይሁን እንጂ በመንግሥት አቅም ለሁሉም



ፎቶ - ሳሙኤል ተስፋዬ

ማዳረስ ስለማይቻል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ግለሰቦች ተጨማሪ ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል። ዘይትና የወጥ እህሎች ችግሮች በመሆናቸው ለሕዝቡ ሊቀርብ ይገባል ብላለች።

የኮረም ከተማ ነዋሪ አቶ ግዛው ታደሰ ርዳታ ወደ


መንግሥት ሰብዓዊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## ስምምነቱ ሰላምን ለተጠማ ሕዝብ የደረሰ ትልቅ ፈውስ ነው

### - ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነእየሱስ

በዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተማ በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት ሰላምን ለተጠማው የትግራይም ሆነ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ ፈውስ መሆኑን የኢትዮጵያ ካቶሊክ ጳጳሳት ፕሬዚዳንት ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነእየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን ገለጹ፡፡ ብፁዕነታቸው ለመላው ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ለሰላም ፍላጎት ላላቸው የሰው ልጆች በሙሉ የእንኳን ደስ ያለን መልእክታቸውንም አስተላልፈዋል፡፡

ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነእየሱስ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በሁለቱ አካላት የተከወነው የሰላም ስምምነት እርሳቸውና ሌሎችም የሀይማኖት አባቶች በመልካም የሚመለከቱት ጉዳይ ነውና ወደ መሬት ወርዶ ተግባራዊ እንዲደረግ በመፀለይ ላይ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያውያን ባለፉበት ያለመግባባቶች ምክንያት


... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









ለፀረ- ሌብነት ትግሉ ውጤታማነት ተቋማዊ አሰራርን ማጠናከር ይገባል


ገጽ 4

ዜና



# ኤጀንሲው የትራፊክ አደጋን ለመከላከል ከመገናኛ ብዙኃን ጋር በትብብር እየሠራ ነው

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ ፡- በአዲስ አበባ በየጊዜው እየተባባሰ የመጣውን በትራፊክ አደጋ ለመከላከል ከመገናኛ ብዙኃን ጋር በመተባበር ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ እንደሚሠራ የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ በመንገድ ደህንነት ላይ ፕሮግራም ከሚያዘጋጁ እና ከሚዲያ ባለሙያዎች ጋር የፓናል ውይይት አድርጓል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አማካሪ አቶ አለምሰገድ ዘውዴ የብዙኃን መገናኛዎች የመንገድ ደህንነት ዙሪያ ተከታታይ የግንዛቤ ማሳደግ ሥራዎችን በመሥራት ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አመላክተዋል።

የአዲስ አበባ የመንገድ ደህንነት መረጃ ባለሙያ ወይዘሮ ሜሮን ጌታቸው በበኩላቸው የመንገድ ደህንነት ጋር የተያያዙ ዳታዎችን አቅርበዋል። በ2014 ዓ.ም በትራፊክ አደጋ 441 ሞት መመዝገቡን ጠቁመዋል። ከ2013 ዓመት አንጻር የተከሰተው የሞት መጠን የጨመረ ሲሆን በየጊዜው በሚከሰተው የትራፊክ አደጋዎች የሚሞተው የሰው ቁጥር እየጨመረ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በ2014 ዓ.ም በትራፊክ አደጋ ለሞት የተዳረጉት በጾታ ደረጃ 78 በመቶ ወንዶች ሲሆኑ 22 በመቶ ሴቶች መሆናቸውንም ገልጸዋል። በእድሜ ደረጃም ከ20 እስከ 39 ዓመት የእድሜ ክልል የሚገኘው አምራች የኅብረተሰብ ክፍል ይበልጥ በትራፊክ አደጋ ለሞት የተጋለጠበት እንደሆነ የጠቀሱት ወይዘሮ ሜሮን፤ በሳምንቱ ቀናት ደረጃ በ2014 ዓ.ም ቅዳሜ ቀን ከሌሎች ቀናት ከፍተኛ የሞት አደጋ የተስተናገደበት መሆኑንም ጠቁመዋል።

የመንገድ ደህንነት ባለሙያና የአውቶ ሴፍቲ ፕሮግራም አዘጋጅ ኢንስፔክተር አሰፋ መዝገቡ በበኩላቸው፣ አደጋ መከላከል ብቻ ሳይሆን የትራፊክ ፍሰቱን ማሳለጥ የትራፊክ ማኔጅመንት አንዱ ሥራው መሆኑን ገልጸዋል። እግረኛ የሚያቋርጥባቸው መንገዶች በ30 ብቻ መሄድ እንደሚገባ ቢቀመጥም ተገቢው የእግረኛ ማቋረጫዎች ባለመኖራቸው የተነሳ በሁሉም አካባቢዎች የሚያቋረጥ መሆኑ ችግሩን ያወሳስበዋል ብለዋል።

እግረኛ እንዳያቋርጥባቸው ከታጠሩት የፍጥነት መንገዶች ውጪ ሁሉም የከተማዋ መንገዶች እግረኛ የሚያቋርጥባቸው መሆኑን አመላከተው ነገር ግን ትምህርት ቤቶች፣ የገበያ ስፍራዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት አካባቢዎች ላይ በይበልጥ በ30 መታሰብ እንደሚገባው ጠቁመዋል። በተጨማሪም የመንገዱ አቀማመጥ ቁልቁለታማ ከሆነ ፍጥነት ሊወሰን ይገባል ብለዋል።

እንደ ኢንስፔክተር አሰፋ መዝገቡ ማብራሪያ የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ዋና ተግባር የተሠራውን መንገድ ማስተዳደር እና ፍሰቱን ማሳለጥ ሲሆን እንደሀገሪቱ የበጀት ሁኔታ መንገዶች እንዲሠሩ የሚያደርገው ደግሞ የመንገዶች ባለሥልጣን ነው።

በተለያዩ ዝግጅቶች መንገዶች ሲዘጉ፣ እንደ ውሃና ፍሳሽ፣ ቴሌኮሙኒኬሽን የመሳሰሉ ድርጅቶች መንገድ ሲቆፍሩ ተመልሶ ስለመሠራቱ ኦዲት መደረግ እንደሚገባቸውም አመላክተዋል። እግረኞችም በተሠራው መንገድ በአግባቡ የመጠቀም ሕግ የወጣ ቢሆንም ተግባራዊ አለመሆኑን አስታውሰዋል።

የእግረኛ ማቋረጫዎች ባሉባቸው መንገዶች በአግባቡ የማይጠቀሙ እግረኞች ተጠያቂ የሚሆኑበት እና የእግረኛ ማቋረጫ ባልተመቻቸባቸው አካባቢዎች ደግሞ ማመቻቸት የሚገባ መሆኑንም ተናግረዋል።

# ፌዴራል ፖሊስ የሕዝብ ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነቱን በተሻለ አፈጻጸም እያከናወነ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ፌዴራል ፖሊስ የአወቃቀርና አደረጃጀት ማሻሻያዎች ከማድረግ ባሻገርም የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ በመታገዝ የሀገርና የሕዝብ ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነቱን በተሻለ አፈጻጸም እያከናወነ መሆኑን አስታወቀ።

የፌዴራል ፖሊስ የወንጀል መከላከል ዘርፍ ኃላፊ ምክትል ኮሚሽነር ጄኔራል መላኩ ፋንታ እንደገለጹት፤ አገራዊ ለውጡን ተከትሎ የፌዴራል ፖሊስ አደረጃጀትን ዓለም አቀፋዊ የፖሊስ ዶክትሪን መሠረት ባደረገ መልኩ የማዘመንና የላቀ ሕዝባዊ አገልግሎት እንዲሰጥ የማድረግ ሥራዎች ተሠርተዋል። ከአወቃቀርና አደረጃጀት ማሻሻያዎች ባሻገርም የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ የታገዙ በማድረግ የአገርና የሕዝብ ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነቱን በተሻለ አፈጻጸም እያከናወነ ነው።

በሠራዊት አባላት ውስጥ የአፈጻጸም ግድፈቶች እንዳይኖሩ በከፍተኛ ጥንቃቄ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለዚህ ደግሞ የአፈጻጸም ጥሰትን በፍጥነት ማረም የሚያስችል አሠራር ተዘርግቷል ነው ያሉት።

ይህም የፌዴራል ፖሊስ አሠራርን በማዘመንና ተልዕኮውን በብቃት እንዲፈጽም በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ማበርከቱን ጠቅሰዋል። በዚህም የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ከሌሎች የጸጥታ መዋቅሮች ጋር



የፌዴራል ፖሊስ የወንጀል መከላከል ዘርፍ ኃላፊ ምክትል ኮሚሽነር ጄኔራል መላኩ ፋንታ

በመቀናጀት የኢትዮጵያን የልማት ግስጋሴ ለመግታት ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ጸረ-ሰላም ኃይሎችን በመከላከል ረገድ ከፍተኛ ሚና መወጣቱን ተናግረዋል።

የፌዴራል ፖሊስ መከላከያ ሠራዊትን ጨምሮ ሌሎች የፀጥታ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የሕዳሴ ግድብን ጨምሮ ሜጋ ፕሮጀክቶች፣ መሠረተ ልማቶች እንዳይስተጓጎሉ ሕዝብ የጣለበትን ኃላፊነት መወጣቱንም ተናግረዋል።

በዚህም የፀጥታ ስጋት በነበረባቸው አካባቢዎች ሰላም እንዲሰፍን መደረጉን ገልፀው፤ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከልና ካማሽ ዞኖች ወደ ሰላማዊ እንቅስቃሴ መመለሳቸውን ለአብነት አንስተዋል።

በተጨማሪም ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ፣ የአቪዬሽን ፖሊስ፣ የዩኒቨርሲቲ ፖሊስ፣ የምድር ባቡር፣ የአድማ ብተና፣ የድንበርና ፀረ ኮንትሮባንድ፣ የፖሊስ ኮማንዶ እና ሌሎች አደረጃጀቶችን በመምሪያ ደረጃ በማዋቀር የወንጀል መከላከል አቅሙን ማሳደጉን ተናግረዋል።

በጎረቤት አገራት የፀጥታ ተቋማት ጋር በመቀናጀትና የጋራ ዕቅድ በማውጣት ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን የመከላከያ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑንም ፌዴራል ፖሊስ አስታውቋል። በዚህም በተለይ በርካታ ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ አዘዋዋሪዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ግብርና ምርቶችን እና የማዕድን ውጤቶችን በኮንትሮባንድ ንግድ ከሀገር የማስወጣት እና አደንዛዥ ዕፅና የኮንትሮባንድ ቁሳቁሶችን ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት ወንጀሎችን በመከላከል ረገድ አመርቂ ውጤት መመዝገቡንም እንዲሁ።

የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ በአፍሪካ ደረጃ ስመ-ጥር የፖሊስ ተቋም የመሆን ግብ ሰንቆ ተቋሙን ለማዘመን የጀመራቸውን ሥራዎች አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል መላኩ ፋንታ ማስታወቃቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# በውሃ እጥረት ምክንያት ተቸግረናል

- የየካ ወረዳ አንድ ነዋሪዎች

# ችግሩን ለመፍታት እየሠራሁ ነው

- የውሃ ስርጭት ዘርፍ

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- በተደጋጋሚ በሚከሰት የውሃ አቅርቦት መቆራረጥና እጥረት ምክንያት እየተቸገርን ነው ሲሉ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ ራስ ካሳ አካባቢ ነዋሪዎች ገለጹ። የውሃና ፍሳሽ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በበኩሉ የመብራት መቆራረጥና መልከዓ ምድራዊ ሁኔታ ለውሃ እጥረቱ ዋነኛ መንስኤ ቢሆኑም ችግሩን ለመፍታት እየሠራሁ ነው ብሏል።

ቅሬታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያቀረቡት በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ በተለምዶ 41 ኢየሱስ ራስ ካሳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ የሆኑ ዜጎች በአካባቢው የውሃ መቆራረጥ ችግር እንዳለ፤ በሳምንት ያገኙ የነበረውም ውሃ ከጠፋ ሦስተኛ ሳምንት ላይ እንደደረሱና በዚህም በርካቶች ራቅ ካለ ሰፈር ውሃ ለማመላለስ እንደተገደዱ ገልጸዋል። የሚመለከተው አካል አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጣቸውም ጠይቀዋል።

ወይዘሮ ሙሉ ባቱ የተባሉ የአካባቢው ነዋሪ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ የውሃ እጥረት እያጋጠመ ነው። በሳምንት አንድ ቀን ይመጣላቸው የነበረው ውሃ ከጠፋ አሁን ላይ ወደ ሦስተኛ ሳምንት እየተጠጋ ነው። በዚህም ነፍሰ ጡር እናቶችን፣ አቅመ ደካማ እናቶችና አባቶች ውሃ በማጣታቸው ተቸግረዋል።

ይህ ሁኔታ ከዚህ በፊትም ደጋግሞ ይከሰት እንደነበር የተናገሩት ወይዘሮ ሙሉ፤ ለሚመለከታቸው አካላት ስልክ በመደወል ቢያሳውቁም አፋጣኝ መፍትሔ እንዳላገኙ ገልጸዋል። ይህም በአገልግሎት ሰጪው ተቋም ላይ የመልካም አስተዳደር ችግር እንዳለ ማሳያ ነው ሲሉ ቅሬታቸውን ለኢፕድ ገልጸዋል።

ሌላኛው የአካባቢው ነዋሪ አቶ ታምራት አሳምነው አካባቢው ላይ በተደጋጋሚ የውሃ መቆራረጥ እንዳለና በአሁኑም ለረጅም ጊዜ መጥፋቱን ጠቅሰዋል። ውሃ በቅርበት ባለመኖሩ ከሩቅ አካባቢ በገንዘባቸው በመግዛት ለውሃ አገልግሎት ተብሎ ከሚከፍሉት ወርሐዊ ክፍያ ባሻገር ለተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸውን ተናግረዋል።

አቶ ታምራት በአካባቢው ውሃ የሚለቀቀው በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑን፤ ይህም በውድቅት ሌሊት ለጥቂት ሰዓታት ብቻ እንደሚመጣ ገልጸው፤ አብዛኛው ሰው ሳይቀዳ እንደሚያልፈው ጠቁመዋል። ይህ ተገቢ ያልሆነ አገልግሎት እንደሆነና የሚመለከተው አካል መፍትሔ እንዲያበጅ ጠይቀዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የውሃ ብክነት



ቁጥጥር ንዑስ ሥራ ሂደት ኃላፊና የስርጭት ዘርፍ ተወካይ አቶ ክፍሌ አበበ፤ ደንበኞች መደበኛ በሆነ አግባብ መጥተው ቅሬታ ባያቀርቡም አካባቢው ላይ ከውሃ አቅርቦት ጋር ተያይዞ ችግር እንዳለ ገልጸዋል። የአካባቢው መልከዓ ምድር ዳገታማ መሆኑና ተደጋጋሚ የመብራት መቆራረጥ መፈጠሩ ለውሃ እጥረቱ ዋነኛ መፍትሔ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

አንድ ሰው ውሃን 24 ሰዓት ማግኘት አለበት ያሉት አቶ ክፍሌ፤ ውሃ በፈረቃ መሆኑ በራሱ ችግር እንደሆነ ገልጸው፤ ይህ የሆነው ግን ያለው ሀብት በቂ ባለመሆኑ ነው ብለዋል። ውሃው በሰው ሰራሽ መንገድ ብቻ የሚሄድ ሳይሆን፤ የመብራት፣ የጊዜ፣ የመልከዓ ምድር አቀማመጥ ተጽእኖ እንዳለበት ተናግረዋል። ከሰሞኑ የተፈጠረው ችግር በመብራት መቆራረጥና በመስመር ብልሽት እንደሆነ ጠቅሰው፤ ችግሩ ተፈትቶ ደንበኞች በተለመደው ጊዜ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ይደረጋል ብለዋል።

“ለአንድ አካባቢ ተራው ነው ብለን ውሃ ለቅቀን መብራት ሲጠፋ ውሃው ሊቋረጥ ይችላል። አካባቢው ዳገታማ ከሆነ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ውሃ በተፈጥሮው ወደ ዳገት ሲሄድ እያዘገመ ነው የሚሄደው። ምንም እንኳን ደንበኞች ውሃ ሌሊት እንደሚከፈትላቸው አድርገው ቅሬታ ቢያቀርቡም ሠራተኛው ግን ሥራውን የሚያከናውነው ከጠዋት 2፡30 እስከ 11፡30 ብቻ ነው። ውሃ ቀን ቢለቀቅላቸውም ዳገታማ አካባቢዎች ላይ ሌሊት ነው የሚደርሳቸው። እንደ ከተማ አስተዳደር የተጀመሩ ሥራዎች ካልተጠናቀቁና አጠቃላይ የከተማው የውሃ ችግር እስካልተፈታ የሌሊቱን ፈረቃ መቀየር አንችልም” ሲሉም አቶ ክፍሌ ተናግረዋል።

አቶ ክፍሌ እንዳሉት፤ እንደ አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ከዋና መሥሪያ ቤቱ ውጭ ዘጠኝ የአገልግሎት ቅርንጫፎች ያሉ ሲሆን፤ ከነዚህ ውስጥም ከፍተኛ የውሃ ችግር ያለበት የጉለሌ ቅርንጫፍ ነው። ይህ በከተማ ደረጃ ጭምር የሚታወቅ ነው። ይህንን በዘላቂነት ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ዋና መሥሪያ ቤቱ እየሠራ ነው። በሲስተም ያልተደረሰባቸው አካባቢዎች ጭምር ሮቶ ተገንብቶላቸው እየተጠቀሙ ይገኛሉ። ያለው ሀብት 24 ሰዓት ለመጠቀም ባያበቃም በፍትሐዊ መንገድ እኩል ተጠቃሚ የማድረጉ ሥራ እየተሠራ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ኮሙኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ አቶ በቀለ ክፍሌ በበኩላቸው፤ የመብራት መቆራረጥ በውሃ ስርጭት ላይ የራሱ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳለው ገልጸዋል። ሆኖም ተቋማቸው ለውሃ አገልግሎት ትኩረት ለመስጠት የኦፕሬሽን ሥራ የሚያከናውን ትልቅ አደረጃጀት ፈጥሮ እየሠራ እንዳለ ገልጸዋል።

መብራት ለፕሮጀክት ሥራ፣ በሰው ሠራሽ ችግሮች፣ በብልሽት ምክንያቶች እንደሚቋረጥና ተመልሶ አገልግሎት እስከሚሰጥ ድረስም ሰዓታትን ሊወስድ እንደሚችል አቶ በቀለ ጠቅሰዋል።በመብራት መቋረጥ ምክንያት የውሃ ሥርጭት እንዳይስተጓጎል ዲስትሪክት ላይ ያሉ የጥገናና ኦፕሬሽን ቡድኖች ከውሃና ፍሳሽ ባለሙያዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ተነጋግረው ችግሮችን እንደሚፈቱ ጠቁመዋል።

ዜና

# የትግራይ ሕዝብ የሰላም አየር መተንፈስ መጀመሩን የአክሱም፣ የዓድዋና የሽሬ ነዋሪዎች ተናገሩ

## - ለሰላም ስምምነቱ ተፈፃሚነት ሁሉም ዜጋ የበኩሉን እንዲወጣ ጠይቀዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ትግራይ፡- “በአሁኑ ወቅት የትግራይ ሕዝብ የሰላም አየር መተንፈስ ጀምሯል፤ ለስምምነቱ ተፈፃሚነት ሁሉም ዜጋ የበኩሉን ሚና ሊወጣ ይገባል” ሲሉ ኢዜአ ያነጋገራቸው የአክሱም፣ ዓድዋና ሽሬ ነዋሪዎች ገለጹ።

ነዋሪዎቹ እንደተናገሩት በመንግሥትና ሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምን በማረጋገጥ ረገድ ተስፋ የሰነቀ ነው።

በዚህም የመማር ሕልማቸው የተቋረጠባቸው ወጣቶች የተሻለ ነገን ማለም ጀምረዋል፣ ጦርነት በሚሉት ሰው ሠራሽ ጠላት የተነሳ የልጆቻቸውን ወጥቶ መመለስ ለሚጠባበቁ እናቶችም እፎይታ ፈጥሯል።

በትግራይ ክልል የሚገኙ ነዋሪዎችም በሰላም ስምምነቱ እጅግ መደሰታቸውን ገልጸው፤ ለተግባራዊነቱ ሁሉም በትብብር እንዲሠራ ጥሪ አቅርበዋል።

ነዋሪዎቹ እንደሚሉት፤ የሰላም ስምምነቱ መላ ኢትዮጵያውያንን ባለ ድል ያደረገ ነው።

በጦርነቱ ሕይወት ተገብሯል፣ ሃብትና ንብረት ወድሟል፤ ኢትዮጵያ ከዚህ በላይ ችግር ሊደርስባት አይገባም ብለዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ወንድማማቾች ነን፤ ችግሮቻችንን በሰላም በመፍታት አንድ መሆናችንን የምናሳይበት ጊዜው አሁን ነው ሲሉም ነው የገለጹት።

የትግራይ ሕዝብ ጦርነት ሰልችቶታል የሚሉት አስተያየት ሰጭዎቹ፤ በሰላም ስምምነቱ መላ ኢትዮጵያውያን አትራፊዎች ነን ብለዋል።

በመሆኑም ዘላቂ ሰላም ሰፍኖ ወደ መደበኛ ኑሯችን እንድንመለስ ሁሉም ዜጋ ለሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት በቁርጠኝነት ሊሠራ ይገባል በማለት መልዕክት አስተላልፈዋል።









# በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጾታዊ ጥቃትን ሁሉም ዜጋ በጽኑ ሊያወግዘው ይገባል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሴቶች ላይ የሚፈጸም ጾታዊ ጥቃት ጥሎት የሚያልፈው ጠባሳ ከፍተኛ በመሆኑ ሁሉም አመለካከቱንና ድርጊቱን በጽኑ ሊያወግዘው እንደሚገባ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳሕለ ወርቅ ዘውዴ ገለጹ።

ፕሬዚዳንት ሳሕለ ወርቅ የዘንድሮውን የ16ቱን ቀናት የጸረ-ፆታዊ ጥቃት ዘመቻ ትናንት በሀዋሳ ከተማ በይፋ ሲያስጀምሩ እንዳሉት፤ ሴቶች ላይ የሚፈጸም ጾታዊ ጥቃት ጥሎት የሚያልፈው ጠባሳ ከፍተኛ ነው። ሁሉም አመለካከቱንና ድርጊቱን በጽኑ ሊያወግዘውና ሊከላከለው ይገባል።

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ለተግባራዊነቱ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ያደነቁት ፕሬዚዳንቷ፤ ጥቃት የሚፈፀምባቸው ሴቶችና ሕጻናት ፍትሕ እንዲያገኙ መንግሥት በትኩረት እንደሚሠራ መግለጻቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳደር አቶ ደስታ ሌዳሞ እንደገለፁት፣ በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውም የጉልበትም ሆነ የሥነልቦና ጥቃት ኋላ ቀር ነው። የሴቶችን ጥቃት ለመከላከል የክልሉ መንግሥት በከፍተኛ ደረጃ እየሠራ ይገኛል። የተገኙ ውጤቶችን ዕውቅና በመስጠት በተሻለ ደረጃ ለመሥራት መትጋት ይጠበቅብናል ብለዋል።

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በበኩላቸው በሴቶች ላይ የሚደርሱ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከፍተኛ ሥራ መሥራቱን ገልጸዋል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለመከላከል አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ተናግረዋል።

ከትናንት ጀምሮ እስከ ታኅሳስ 1 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ባሉት 16 ቀናት የሚከናወኑ የዘመቻ ሥራዎች ላይ የፓናል ውይይት ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል። የጸረ-ጾታዊ ጥቃት ቀን በተደጋጋሚ የሚፈጸሙ ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል ላይ ትኩረት አድርጎ በየዓመቱ የሚካሄድ ዘመቻ ነው።

ከኅዳር 16 ቀን ጀምሮ እስከ ታኅሳስ 1 ድረስ በየዓመቱ በሚካሄድ በ16 የንቅናቄ ቀናት በፆታዊ ጥቃት ምክንያት የሚከሰቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች በተመለከተ ግንዛቤ የማስጨበጥና ችግሩን በዘላቂነት መከላከል የሚቻልባቸው ተግባራት ላይ ትኩረት በመስጠት በስፋት የሚሠራበት ወቅት ነው።

በተለይ በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች መንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትና ኅብረተሰቡ በአካባቢያቸው ለሚገኙ ሴቶች ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡ ማሳሰብን ይጨምራል።

# ‹‹የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የሁላችንንም ተቀራርቦ መሥራት ግድ የሚል ነው››

- ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ
  የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተቀራርቦ መሥራት ግድ የሚል መሆኑን የሴቶችና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ገለጹ።

ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በተስፋ ድርጅት 50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዮቤልዩ በዓል አከባበር ላይ በክብር እንግድነት ተገኝተው ባደረጉት ንግግር እንዳሉት፤ በኅብረት መሥራት አሁን ማኅበረሰባችን እያጋጠመው ያለውን ውስብስብ ችግር በተሻለ ሁኔታ ለመፍታት አቅም ይሆናል። ሀገራችን ያለችበት ነባራዊ ሁኔታ የሁላችንንም ተቀራርቦ መሥራት ግድ የሚል መሆኑን በመረዳት ሁሉም ባለድርሻ አካላት የየድርሻቸውን ኃላፊነት መወጣት አለባቸው ብለዋል።

መንግሥት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሁሉም መስክ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ፖሊሲና የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ በማውጣትና ደጋፊ የሕግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት በሥራ ላይ እንዲውል አድርጓል ያሉት ሚኒስትሯ፤ በችግር ውስጥ የሚገኙ ዜጎች ካሉባቸው ችግሮች ተላቀው ወደተሻለ ሕይወት እንዲያመሩ፣ መብቶቻቸውና ጥቅሞቻቸው እንዲከበሩ ማድረግ ለማኅበራዊ ትስስር መጎልበትና ለሁለንተናዊ ሀገራዊ እድገት ከፍተኛ ሚና እንዳለው ጠቁመዋል።

ለተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የተጋለጡ ዜጎች ችግር በአንድ ተቋም ሥራ ብቻ የሚፈታ አይደለም ያሉት ሚኒስትሯ፤ ተስፋ ድርጅትን የመሰሉ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና ሌሎችም መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የእነዚህን ዜጎች መጻኢ እድል ለማቃናት የሚያደርጉትን አይተኬ ሚና እውቅና ይሰጣል ብለዋል። በቀጣይነት ለሚያከናውኗቸው ተግባራትም አስፈላጊውን እገዛ እንደሚያደርግ አመላክተዋል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሡ ጥላሁን በበኩላቸው፤ ተስፋ ድርጅት ለግማሽ ክፍለ ዘመን ባከናወናቸው ውጤታማ ሥራዎች የብዙዎችን ታሪክ ቀይሯል ብለዋል።

በአገራችን ከከተማ እስከ ገጠር ከፍተኛ የሥራ አጥነት ችግር እንደሚስተዋል ጠቁመው፤ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት እነዚህን ዜጎች ወደ ሥራ እንዲሠማሩ ለማድረግ የተለያየ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ እየሠራ ይገኛል ሲሉም ጠቁመዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር እስከ 2030 ድረስ ለ20 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ እድሎችን ለመፍጠር እየሠራ መሆኑን አስታውሰው፤ ለዜጎች ሥራ መፍጠር ከዜጎች የየግል ተጠቃሚነት በላይ እንደ ሀገር ያለውን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለማሳለጥ ከሚያስችሉ ቀዳሚ አጀንዳዎች አንዱ ነው።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተቋቋመውም በመንግሥት አቅም ብቻ የማይሳካውን ይህንን ግዙፍ አገራዊ ተልዕኮ ለማሳካት ሁሉንም አቅም አቀናጅቶ ለመጠቀም ነው ያሉት አቶ ንጉሡ፤ ከዚህ አኳያ ተስፋ ድርጅት ለዘመናት ያካበተውን ዜጎችን አሰልጥኖ ሥራ የማስያዝ ልምድና ተሞክሮ በአግባቡ ለመጠቀም በቀጣይነት በቅርበት አብረን እንሠራለን ብለዋል።

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ፋሲካው ሞላ እንዳሉት ደግሞ፤ በኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው በሀገራዊ ሁለንተናዊ ልማት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለመወጣት እንዲችሉ መንግሥት የሕግና ተቋማዊ ሪፎርሞችን ሲሠራ ቆይቷል።

ለውጡን ተከትሎ በተደረገው ሪፎርም በአሁኑ ጊዜ ከ4 ሺ 300 በላይ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በተለያዩ መስኮች እየተንቀሳቀሱ ነው ያሉት አቶ ፋሲካው፤ ከቁጥር መጨመር ባለፈ እነዚህ ድርጅቶች በሀገራዊ የልማት ሥራዎችና አስቸኳይ የእርዳታ ሥራዎች በንቃት እየተሳተፉ ነው።

ለ50 ዓመታት በትምህርት፣ በሙያ ስልጠናና ክህሎትና በሰብዓዊ ድጋፎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ ድርጅቱ እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ለመደገፍ ለሠራው ሥራ ምስጋና አቅርበዋል።

በቀጣነትም ያለውን ልምድ ቀምሮ ለሌሎች አቅም በሚሆን መልኩ መሥራት እንዳለበት አሳስበው፤ ባለስልጣኑ ተስፋ ድርጅት ለሚያከናውናቸው የተለያዩ ልማትና ሰብዓዊ ሥራዎች አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እንደሚያደርግ ቃል ገብተዋል።

ተስፋ ድርጅት ላለፉት 50 ዓመታት በተለያ ድህነት ቅነሳና የልማት ሥራዎች የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ የሚገኝ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት መሆኑን ከተቋሙ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ዜና

# ለፀረ-ሌብነት ትግሉ ውጤታማነት ተቋማዊ አሠራርን ማጠናከር ይገባል

**ማሕሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- እንደ ሃገር የተጀመረው የፀረ-ሌብነት ትግሉ ውጤታማ እንዲሆንና ከሌብነት የፀዳ ሃገር ለመገንባት ተቋማዊ አሠራርን ማጠናከር እንደሚገባ የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ኅብረት ዳይሬክተርና የሕግ ባለሙያ አቶ መስኡድ ገበየሁ አስታወቁ።

የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ኅብረት ዳይሬክተርና የሕግ ባለሙያ አቶ መስኡድ ገበየሁ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ መንግስት ሌብነትን ለመከላከልና ተጠያቂነት ለማምጣት ያስችል ዘንድ ግብረ ኃይል ማቋቋሙ ይበል የሚያሰኝና የሚያበረታታ ነው። ይሁንና ግብረ-ኃይል ከማቋቋም ባለፈ አሁን ላይ ሌብነት በራሱ የገነገነ ወንጀል ስለሆነ በግብረ ኃይልና በኮሚቴ ደረጃ ብቻ ሥራ ተሠርቶ ለውጥ ማምጣት አዳጋች ነው። ስለሆነም እዚህ ላይ ኃላፊነት ተሰጥቶት የተቋቋመው የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽንም ሆነ አጠቃላይ መንግሥታዊ መዋቅሩን ማጠናከር ይገባል።

በተለይም የኮሚሽኑን ኃላፊነቱን አስፍቶ የበለጠ አቅሙን በማሳደግ ፀረ-ሌብነት ትግሉን በበላይነት እንዲመራው መደረግ እንደሚገባ ገልፀው፤ ‹‹ለዚህም ይረዳ ዘንድ ተጠሪነቱን ለሕዝብ ምክር ቤት በማድረግ ከሕዝብ ጋር ቅርበት ፈጥሮ እንዲሠራ ማድረግ ያስፈልጋል›› ብለዋል። በተጨማሪም ሌቦችን የሚያጋልጡ ሰዎችን በመሸለምም፤ ጥበቃ በማድረግም ሊያበረታታ እንደሚገባም ገልፀዋል።

በሌብነት ተጠርጥረው የሚያዙ ሰዎችን ደግሞ በማናቸውም ሁኔታ ክሳቸው የማይቋረጥበት ሁኔታ መፍጠርና ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ ወጥቶለት በሕግ አግባብ ተጠያቂነትን ማምጣት ያስፈልጋልም ብለዋል።

‹‹በተለይም ለእንደዚህ አይነት ተግባር የበለጠ ተጋላጭ ናቸው የሚባሉ ተቋማት ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ ይገባል። ለምሳሌ ግዢ ኤጀንሲ ጋር ተያይዞ



**አቶ መስኡድ ገበየሁ**

ብዙ የሚቀርቡ ቅሬታዎች አሉ፤ ገቢዎች አካባቢም ታክስ በመሰወር የሚታዩ ወንጀሎች ላይ በጣም ጠንካራ የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት እርምጃ መውሰድ ይገባል›› ብለዋል። ጎን ለጎንም ከሃይማኖት ተቋማት፤ ከሲቪል ማኅበራት ጋር በመሆን ግንዛቤ በማስጨበጥ ሌብነትን የሚፀየፍ ዜጋ የማፍራቱ ሂደት መጠናከር እንዳለበትም አስገንዝበዋል።

እንደርሳቸው ገለፃ፤ ይህንንም በተከታታይ በመተግበር ባህል ማሳደግ ካልተቻለ አሁንም ቢሆን የተጀመረው ዘመቻ የአጭር ጊዜ ሆኖ ከዚያ በኋላ የሚረሳ የሚሆንበት አሠራር ሊፈጠር ይችላል። ይህ መሆን ካልቻለ እንዲያውም ሌቦችን በጣም በረቀቀ መንገድ ስርቆት የሚፈጽሙበትን ሁኔታ የሚያበረታታ ስለሚሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

‹‹ሌብነትን በተመለከተ በሚዲያ ከሚነገረው በተጨማሪ መሬት ላይ የሚታይና የሚጨበጥ እርምጃ መወሰድ አለበት፤ ምክንያቱም ሕዝቡ መንግሥትን ማገዝ የሚችለው የሚጨበጥ ርምጃ ሲያይ ነው። የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት፣ይህን ደግሞ ከጸረ-ሙስና ኮሚሽንና ለዚህ ከተቋቋመው ግብረ-ኃይል ጋር በማገናኘት ከሲቪል ማኅበረሰብና መሰል ተቋማት ጋርም የግንዛቤ ማስጨበጡን ሥራ መሠራት አለበት›› ብለዋል።

## የወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የንግድ እና ልማት ጉባኤ እ.አ.አ. በ2021 ባወጣው ሪፖርት መሠረት ዓለም አቀፍ የኢ-ኮሜርስ የግብይት ዋጋ መጠን 26 ነጥብ 3 ትሪሊዮን ዶላር የነበር ሲሆን ከዚህም ውስጥ የአፍሪካ ድርሻ አንድ በመቶ ብቻ ነው።

አቶ ደመቀ መኮንን ከጉባኤው ጎን ለጎን ከሶማሊያ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሳላህ አሕመድ ጃማ እንዲሁም በኔፓድ የአፍሪካ ኅብረት የልማት ኤጀንሲ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናርዶስ በቀለ ጋር ተወያይተዋል።

አቶ ደመቀ ከሶማሊያ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሳላህ አሕመድ ጃማ ጋር በነበራቸው ውይይትም የኢትዮጵያንና የሶማሊያን የባለብዙ ወገን ትስስርና አጋርነት በማጠናከር የሁለትዮሽ ግንኙነቱን በላቀ ሁኔታ ለማሳደግ ተስማምተዋል። ለሁለትዮሽ ግንኙነቱ መላቅ አስተዋጽኦ የሚኖረውን የጋራ የሚኒስትሮች ጉባኤም በአፋጣኝ ለማካሄድ ተስማምተዋል።

አቶ ደመቀ ኢትዮጵያ በሁሉም መስክ ያላትን ምርጥ ተሞክሮ ለሶማሊያ ለማካፈል ዝግጁ ናት ብለዋል።

የሶማሊያ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሳላህ አሕመድ ጃማ በበኩላቸው የኢትዮጵያ ሰላምና ደህንነት መጠበቅ ለሶማሊያም ሆነ ለቀጠናው ወሳኝ ጉዳይ ነው ብለዋል። ኢትዮጵያ በቀጠናው ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ ቁልፍ ሚና እንዳላትም ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል አቶ ደመቀ በኔፓድ ከአፍሪካ ኅብረት የልማት ኤጀንሲ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናርዶስ በቀለ ጋር በተወያዩበት ፤ በኢትዮጵያ የሥራ አጥነትን ለመቀነስ እንዲሁም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፉን ለማሳደግ ስለተከናወኑ ተግባራት ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ሁለቱ አካላት በመጪው የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ላይ በኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ በተለይ በስንዴ ልማት እንዲሁም በቴክኖሎጂና በሳይንስ ሙዚየም ስለተከናወኑ ተግባራት የውጤት አፈጻጸም ለማዘጋጀት ተስማምተዋል።

የአፍሪካ ኅብረት የልማት ኤጀንሲ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናርዶስ በቀለ በበኩላቸው አህጉራዊ ተቋሙ የኢትዮጵያ መንግሥት እያደረገ ለሚገኘው የልማት ሥራዎች ስኬታማነት የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጠል መግለጻቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል።

በኔፓድ የአፍሪካ ልማት ኤጀንሲ በአፍሪካ አህጉራዊ ትስስር እንዲፈጠርና አጀንዳ 2063 ስኬታማ እንዲሆን በአህጉርና በቀጠና ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የልማት ፕሮጀክቶች የሚያስተባብርና ለተፈጻሚነታቸው ድጋፍ የሚያደርግ ተቋም ነው።

## ስምምነቱ ሰላምን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ደሀው ሕዝብ ሲቸገር ነው የምናዝነው ያሉት ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነእየሱስ፤ የሰላም ስምምነቱም ተስፋና ደስታ አምጥቶልናልና ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገርና በመጸለይ ለተግባራዊነቱ እንሠራለን ብለዋል።

እንደ ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነእየሱስ ገለፃ፤ እርቀ-ሰላም ከራስና ከሌሎችም ጋር ሰላም ከመፍጠር ይጀምራል፤ የሀይማኖት አባቶችም በየቤተ እምነታቸው ላይ እርቅ በማውረድ የሰላም ሰዎች ሊሆኑና የሰላም ቋንቋንም ሊናገሩ ይገባል።

ስምምነቱ ሰላምን ለተጠማ ሕዝብ የደረሰ ትልቅ ፈውስ ነው ያሉት ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነእየሱስ፤ ሰላምን ከሕፃን እስከ አዋቂ ሁሉም ሰው ይወዳታልና የሰላም አማራጭ በመወሰዱ ደስተኛ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በደቡብ አፍሪካ ሲካሄድ የሰነበተው የሰላም ድርድር ሁሉም ወገኖች በተስማሙበት ሁኔታ መጠናቀቁን በሚመለከት የተሰማቸውን ደስታ የገለጹት ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነእየሱስ፤ በሰላም ስምምነቱ የተገኘውን ሰላም በመንከባከብ ዘላቂ ሰላም ሰፍኖ ኢትዮጵያውያን እንደ ጥንቱ እየተደጋገፉና እየተረዳዱ በመልካም ጉርብትና እንዲኖሩ አደራ እንላለን ሲሉም ነው የተናገሩት።

በሁለቱም ተደራዳሪ አካላት ወገን የሚገኝ ሕዝብ በጦርነቱ እየተጎዳ ነበር ያሉት ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነእየሱስ፤ አሁን በተደረሰው የሰላም ስምምነት ምክንያትም በርካታ እናቶች እምባቸው እንደሚታበስ፣ ብዙ ሕጻናትም ሰቆቃቸው እንደሚቆምም ነው የገለጹት።

ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነእየሱስ፤ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ስለ ሰላም መስፈን የሚመለከታቸው በሙሉ የሀገራችን ሰላሟ በዘላቂነት እንዲረጋገጥ ትብብር አድርጉ ሲሉ አባታዊ ምክራቸውንም አስተላልፈዋል።

የሰላም ስምምነቱ ወደ መሬት ሊወርድ ይገባዋል ያሉት ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነእየሱስ፤ እርሳቸውም ለተግባራዊነቱ እንደሚጥሩና ምዕመኑ ወደሰላም እንዲመጣ በመምከርና በመፀለይ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክቱ አመላክተዋል።



በላይነሽ ከበደ



ግዛው ታደሰ



መኩንን ዘገየ



ትዕግስት በርሄ



መሳይ ገብረስላሴ

## መንግሥት ሰብዓዊ እርዳታን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ኮረም ከተማ እየገባ ነው፣ ይሁንና የተረጂው ሕዝብ ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ በበቂ ሁኔታ እየተዳረሰ አይደለም። ላለፉት ሁለት ዓመታት ሙሉ የኮረም ከተማ የግጭት ቀጠና በመሆኑ የመንግሥት ሠራተኛ ጭምር ተረጂ ነው። ስለሆነም ከስንዴው በተጨማሪ እንደ ዘይትና ከክ የመሳሰሉ እርዳታዎችም ሊደርሱ ይገባል። በጦርነት ወቅት በቀን አንዴ ከመብላት እስከ ምንም አለመብላት ከነበረው ችግር አንጻር የሚደረገው እርዳታ ትልቅ ተስፋ ሰጭ ነው። ነገር ግን ከምግብ ነክ ርዳታው በተጨማሪ እንደ ልብስና ፍራሽ ያሉ መገልገያዎች መቅረብ አለባቸው ብለዋል።

እርዳታው ፍትሐዊ በሆነ መልኩ መሰራጨቱ ያስደስታል ያለችው ወይዘሮ ትግስት በርሄ፣ ፋፋና ስንዴ እየተሰራጨ ነው፣ ተስፋችንም ለምልሟል። ይህ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፣ ከጦርነት ውጭ የነበሩ አካባቢዎችና የውጭ ድርጅቶች ቀጣይነት ባለው መልኩ ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል ስትል ሃሳቧን ሰጥታለች።

የኮረም ከተማና አካባቢው ከጦርነት በመውጣቱ ደስታችን ወደር ባይኖረውም አስቸኳይ የሆነ እርዳታ ያስፈልገናል። መንግሥት ለኮረም ሕዝብ ደርሷል፣ ይሁንና በዚህ ላይ ተጨማሪ እርዳታዎች ያስፈልጋሉ መሠረታዊ አገልግሎቶችም ክፍት ሊሆኑ ይገባል ስትል ጠይቃለች።

የኮረም ከተማ የሎጂስቲክ አስተባባሪ አቶ መኮንን ዘገየ በበኩላቸው፣ አካባቢው ነጻ ሲወጣም መንግሥት ለተጎዱ እርዳታ ሰጥቷል። ነገር ግን የተረጂው ቁጥር ብዙ በመሆኑ ሌሎች አጋዦችም ተደማሪ ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል ሲሉ ሃሳባቸውን ገልጸዋል።

በኮረም ከተማ ብዙ ተረጂ አለ ያሉት አስተባባሪው፣ ይሁንና እስካሁን አንድም የውጭ ረጂ ድርጅቶች አልገቡም። የኢትዮጵያ መንግሥት የላከው የእርዳታ ስንዴ ግን በመሰራጨት ላይ ነው። የወፍላና የዛታ ወረዳዎች ከመንግሥት ሠራተኛ እስከ አርሶ አደር ምንም አይነት እርዳታ እያገኙ አይደለም። የፌዴራልና የአማራ ክልል መንግሥት ለኮረም ከተማ ያቀረበው እርዳታ እየተሰራጨ ነው ከችግሩ ስፋት አኳያም ዘይትና ሽሮን የመሳሰሉ ድጋፎች መቅረብ አለባቸው ብለዋል።

በቀጣይ ባንኮች እንዲከፈቱ መንግሥት እንቅስቃሴ እያደረገ በመሆኑ ለውጦች እንደሚመጡና፣ የምግብና የሸቀጥ እቃዎች እንዲገቡ በማድረግ ገበያውን የማረጋጋት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

የቀዳሚ መጽሔት

# አገልግል

## የንባብ ባሕልን ከማዳበር የንባብ ፍቅር ይቀድም

ገጽ 11



«ብሔራዊ የጸረሙስና ኮሚቴ መቋቋሙ የሚበረታታና መንግሥት ተጠያቂነትን ለማምጣት ቁርጠኛ መሆኑን ማሳያ ነው»

- አቶ መስኡድ ገበየሁ
የሕግ ባለሙያ

ገጽ 6



## አልጣጣም ያለው የሲሚንቶ ፍላጎት፣ አቅርቦትና መፍትሄው

ገጽ 14

የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን
HOUSING DEVELOPMENT CORPORATION

ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ተሰርዞ የነበረው የ20/80 እና 40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ ወጣ

በመዲናዋ የሚስተዋለውን የቤት አቅርቦትና ፍላጎት ልዩነት ለማጣጣም በ10 ዓመት ውስጥ ሁለት ሚሊዮን ቤት ለመገንባት እቅድ ተይዟል፡፡ መንግሥት ይህንን ዕቅድ ለማሳካት የቀጣይ የቤቶች ልማት ስትራቴጂ 80 በመቶ በግሉ ዘርፍ 20 በመቶ ደግሞ በመንግሥት ድጎማ እንዲከናወን ወስኗል፡፡ በዚህም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን በአዋጅ 74/2014 በድጋሚ ሲቋቋም የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት 20 በመቶ በመንግሥት አስተባባሪነት የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ገንብቶ ማስተላለፍ ሆኗል፡፡

ስለዚህ ተቋሙ በአዋጅ ከተሰጠው ሁለት ዓበይት ተግባራት (የጋራ መኖሪያ ቤቶችን መገንባትና ማስተላለፍ) አኳያ ከዚህ ቀደም ተሰርዞ የነበረውን የ20/80 እና የ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ዕጣ አውጥቷል፡፡ የ14ኛው ዙር የ20/80 እና 3ኛው ዙር የ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ የማውጣት ሥነ-ሥርዓት ከሰሞኑ ተካሂዷል፡፡ በዕጣ ማውጣት ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ አዳነች አቤቤን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተወካዮች በታዛቢነት ተገኝተዋል፡፡

በዕጣው የ20/80 የቤት ልማት ፕሮግራም 18 ሺ 930 ቤቶች፣ በ40/60 ደግሞ 6 ሺ 843 ቤቶች እንዲሁም ተጨማሪ 18 ስቱዲዮ ቤቶች በድምሩ 25 ሺ 791 ቤቶች ዕጣ ወጥቶባቸዋል፡፡ ከዚህ ቀደም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ ሐምሌ 01 ቀን 2014 ዓ.ም ወጥቶ የነበረ ቢሆንም በዕጣው ማውጣት ሂደት በገጠመ ችግር ምክንያት ዕጣው



ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣

በመሰረዙ ነው ከሰሞኑ በድጋሚ የዕጣ ማውጣት ሂደት የተከናወነው፡፡

የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዕጣ ማውጣት ሥነ ሥርዓቱ ላይ እንዳሉት፤ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ከግንባታ እስከ ዕጣ ማውጣት ሂደት ባለፉት ጊዜያት ከውስጥም ሆነ ከውጭ በርካታ ችግሮች አስተናግዷል፡፡ ከዚህ አንፃር ዳግም የወጣው የ20/80 እና 40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ በርካታ ችግሮችን በማለፍ በስኬት መከናወኑን አንስተዋል፡፡

በተለይ በለውጡ ዋዜማ የሥራ ተቋራጮች ሥራውን አቋርጠው የመጥፋት፣ የመሠረተ ልማት ዝርፊያ፣ የግንባታ ጥራት ችግር፣ የፋይናንስ እጥረትን ጨምሮ ዘርፉ የተወሳሰበ ሂደት ውስጥ ለማለፍ ተገድዷል ነው ያሉት፡፡

የከተማ አስተዳደሩ እነዚህን ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከ21 ቢሊዮን ብር በላይ በመበደር ጥረት ሲያደርግ መቆየቱንም እንዲሁ አንስተዋል፡፡ ሆኖም ከዚህ በፊት ዕጣ የወጣባቸውን የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለተጠቃሚዎች ለማድረስ የተደረገው ሙከራ በተለያዩ የሌብነት ተግባራት ምክንያት ሳንካ ገጥሞት እንደነበርም ጠቅሰዋል፡፡ ይህ ደግሞ ለረጅም ዓመታት በትዕግስት ሲጠባበቅ ለነበረው ሕዝብ አሳዛኝ ዜና እንደነበር አውስተዋል፡፡

በዕጣ ማውጣት ሂደቱ ከተፈጠረው ችግር ጀርባ የቤት ልማት መርሐ-ግብርን ለግል ጥቅም ማካበቻ ከማድረግ ባለፈ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል አለመተማመን ለመፍጠር ያለመ ሴራም እንደነበር ከንቲባዋ ጠቁመው፤ የከተማ አስተዳደሩ የገጠመውን ችግር ለሕዝብ በግልፅ ይፋ በማድረግ በአጥፊዎች ላይ ተጠያቂነትን ማስፈኑን ጠቅሰዋል፡፡

ተዓማኒነቱ የተረጋገጠ አዲስ የዕጣ ማውጫ ሥርዓት በማልማትም ከዚህ ቀደም ተሰርዞ የነበረው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ በድጋሚ እንዲወጣ መደረጉን ከንቲባዋ አክለው ገልጸው፤ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ በድጋሚ እንዲወጣ ያለመታከት ጥረት ያደረጉ ሠራተኞችና አመራሮችን አመስግነው ባለእድለኞችንም እንኳን ደስ ያላችሁ ብለዋል፡፡

ምንጭ:- ኢዜአ

# የዘመን እንግዳ

## «ብሔራዊ የጸረሙስና ኮሚቴ መቋቋሙ የሚበረታታና መንግሥት ተጠያቂነትን ለማምጣት ቁርጠኛ መሆኑን ማሳያ ነው»

- አቶ መስኡድ ገበየሁ
የሕግ ባለሙያ

ማህሌት አብዱል

**በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ሌብነት መንግሥታዊ ሥርዓትን በመላበሱና አቅሙ በመደንደኑ የአገር ህልውና ስጋት እየሆነ መጥቷል፡፡ ዜጎች መብቶቻቸውንም ሆነ አገልግሎት ያለ ጉቦ ማግኘት ህልም እየሆነባቸው መምጣቱን ያነሳሉ፡፡ መንግሥትም ቢሆን ሌብነት በራሱ መዋቅር ውስጥ ከላይ እስከ ታች ሰንሰለት ፈጥሮ አሳሰራ እንዳለው በተደጋጋሚ ሲገልፅ ይደመጣል፤ ጥቂትም ቢሆኑ ሌቦችን ተጠያቂ ለማድረግ ጥረት ሲያደርግ ይስተዋላል፡፡ በቅርቡም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው የችግሩን አሳሳቢነት፤ ለአገር ህልውና ስጋት እየሆነ ስለመምጣቱ ለአባላቱ አስረድተዋል፡፡ ይህንን የአገርና የሕዝብ እድገት ፀር የሆነ ክፉ ባህል መንቀል ያስችለው ዘንድ ብሔራዊ የጸረሙስና ኮሚቴ አቋቁሞ በሌብነትና በሌቦች ላይ ሊዘመት እንደሆነ አብስረዋል፡፡ ለመሆኑ ይህ የመንግሥት እርምጃ እንዴት ከስኬት ይደርሳል? ምንስ ሊሠራ ይገባል? በሚሉ ዝርዝር ጉዳዮች ዙሪያ የሕግ ባለሙያ፤ የሰብአዊ መብት ተሟጋችና የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ህብረት ዳይሬክተር ከሆኑት አቶ መስዑድ ገበየው ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡**



**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ ስለመጣው ሌብነት ወይም ሙስና አጠቃላይ ገፅታ ምን እንደሚመስል ያብራሩልንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**አቶ መስዑድ፡-** በኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥታዊ ሌብነት ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩን እየቀያየረና በጣም ተቋማዊ በሚመስል ደረጃ ጎልብቶና የአገር ህልውና ስጋት ሆኖ ነው የሚታየው። ግለሰቦች ሳይቀሩ ምንም ዓይነት ተጠያቂነትን ባለመፍራትም ጭምር በአደባባይ የሚያደርጉት ነገር እየሆነ መጥቷል። ሁላችንም እንደምናስታውሰው ይሄ ሪፎርም እንዲመጣ አንዱ መነሻ ምክንያት ሕዝቡ በመንግሥታዊ ሌብነት እጅግ በመማረሩና ያንን ለማስወገድ በተደረገ ትግል ነው። በተለይም በሕዝብ አገልግሎት በሚሰጥባቸው እንደመሬት አስተዳደርና ገቢዎች አካባቢ ምንም ዓይነት አገልግሎት ለማግኘት ገንዘብ መክፈል ግዴታ የነበረበትና ያ ደግሞ ሕዝቡ ከአቅሙ በላይ በመሆኑ መንግሥት ላይ ያለው እምነት ተሸርሽሮ ወደ ተቃውሞ እንዲያመራ ምክንያት ሆኗል።

ለውጡ ከመጣ በኋላ የዶክተር ዐቢይ መንግሥት በተለይ ከባድና ቆራጥ እርምጃ እወስድባቸዋለሁ ብሎ ከጀመራቸው ሥራዎች አንዱ የሌብነቱ ጉዳይ ነው። እንደምናስታውሰውም «ሙስና እያሉ ማንቆለባበስ አያስፈልግም፤ ሌብነት ሌባ ብለን በስሙ ልንጠራው ይገባል» በማለት በአደባባይ ሲናገሩ አድምጠናል። በዚህ ላይ መንግሥታቸው ምንም ዓይነት ርህራሄ የሌለው እንደሆነ ተናግረውም ነበር። ሆኖም ለውጡን ተከትሎ የነበረው አንዳንድ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችና በተለያዩ አካባቢዎች የነበረው ግጭት የመንግሥትን ትኩረት በመሳቡ ሌብነት ላይ ለማድረግ ታቅዶ የነበረውም እርምጃ መሬት ላይ ሳይወርድ ቀርቶ ቆይቷል። ይህን ሁኔታ እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሌቦች ከፍተኛ የሆነ ሰንሰለት በመፍጠር የተደራጁበት ሁኔታ ነው ያለው።

ይሄ እንግዲህ በሁሉም ዘርፎች ላይ ጎልቶ የሚታይ ከመሆኑም በላይ በጣም ስር የሰደደ ሰዎች በሌብነት ሀብት ማፍራትን፤ ገንዘብ ማግኘትን፤ ገንዘብ ያገኙ ሰዎችን ወደ ድህነት መቀየር ሳይቀር በዚህ ደረጃ በጣም ተንሰራፍቶ በተለይ በአንዳንድ ተቋማት ጥቅሙ በገሃድ ማንም ሰው ምንም ዓይነት አገልግሎት እንዳያገኝ ሲያደርግ ነበር። ለምሳሌ ይሄ መሬት አስተዳደር፤ በጉምሩክ አካባቢዎች ጎልቶ ይታያል። ለዚህም ነው ከኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ይሄን ያክል ሚሊዮን ዕቃ በቁጥጥር ስር ዋለ ሲባል የምንሰማው። ሆኖም እነዚህ እንቅስቃሴዎች አልፎ አልፎ የሚደረጉ ናቸው። በየጊዜው ምንያክል የሕዝብ ሀብት እንደሚባክን፣ እንደሚበዘበዝ፤ አላግባብ ጥራታቸውን ያልጠበቁ ዕቃዎች እንደሚገቡ መገመት የሚቻል ነው። ስለዚህ የእነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት አሁን ላይ መንግሥትም በከባድ ሁኔታ እየተፈተነበት ያለ መሆኑ እሙን ነው።

ለዚህም ነው በቅርቡ ሁላችንም እንደሰማነው መንግሥት ይህንን ልዩ ራሱን የቻለ ሁኔታ የሚመራ ግብረኃይል አቋቁሞ የነፃ የስልክ መስመር ከመዘርጋት ጀምሮ፤ ግብረኃይሉ ወደ ተግባር ገብቶ ውጤት ማምጣት እንዲችል አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ ያደረገው። በዚህ አጋጣሚም እያንዳንዱ ሰው በማናቸውም መልኩ ጥቆማቸውን በመስጠት፤ መረጃን በማጋራት፤ ሌሎችንም ከሕዝብ የሚፈለጉ ማናቸውንም ትብብሮች በማድረግ ይህንን የፀረ-ሌብነትን ዘመቻ ሁሉም ሰው እንዲያግዝ ጥሪ አቅርቧል። እንግዲህ እኛም የሲቪል ሶሳይቲ ማህበራት ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ አንዱም የምንሠራበት የትኩረት አቅጣጫችን በመሆኑ ሌብነት ባለበት ሰብአዊ መብት አይከበርም፤ ሰላም አይመጣም ብለን ነው የምናምነው። ምክንያቱም ሌቦች ሰላም በተፈጠረ፤ አገር በተረጋጋና ሥርዓት በተዘረጋ ጊዜ ቦታ ስለማያገኙ አይመቻቸውም። ሌብነት በራሱ ሥርዓት አልበኝነት ስለሆነ የእነሱ መጠቀሚያቸው ሰላም እንዲመጣ አይፈልጉም።

አንዳንዴም ግጭቶችንም በማባባስ፤ ስፖንሰርም በማድረግም ጭምር ለሌብነት እንዲመቻቸው ሲያደርጉ ይስተዋላል። የገበያ ግርግር ለሌባ ይመቻል እንደሚባለው በዚህ ዓይነት መልኩ እኛ በተለያየ ጉዳዮች ላይ በምናተኩርበት ጊዜ እነሱ ይህንን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም የአገርን ክብር በሚያዋርድ መልኩ በሌብነት ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ተሰማርተው ይገኛሉ። አሁን ላይ ሌቦቹ በጣም ከባድ የሆኑ ሰንሰለቶችን በመፍጠር ሕዝብና አገርን እንደሚበዘብዙ በቅርብ የወጣው የመንግሥት መግለጫ ያመለክታል። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ምክር ቤት ቀርበው ያስረዱት ይህንኑ ነው። ስለዚህ ይሄ ጉዳይ እጅግ አሳሳቢ በመሆኑ መንግሥት የወሰደው እርምጃ ጥሩና ይበል የሚያሰኝ ነው ባይ ነኝ። ምክንያቱም እኛ ሁሌም የምንወተውተውና መንግሥት ይሄንን የሌብነት ጉዳይ ትኩረት አልሰጠውም የምንለው ነገር በመሆኑ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እስካሁን ባለው ሂደት መንግሥት ሌብነትን ለመዋጋት የተለያዩ ሥራዎችን ቢሠራም ለውጥ ሊመጣ ያልቻለበት ምክንያት ምንድን ነው ይላሉ? ጥቂት ሰዎችን ብቻ ማዕከል ያደረገ እርምጃስ ምን ያህል አስተማሪ ነው?**

**አቶ መስዑድ፡-** ከዚህ ጋር ተያይዞ አሁንም ትልቁ ችግር ሌብነት ተቋማዊ መሆኑ ነው። ይህ በመንግሥታዊ መዋቅር ሁሉ ስር የሰደደውን ሌብነት አንድን አመራር ፍርድ ቤት በማቅረብ፤ ተጠያቂ በማድረግ የሚፈታ አይደለም። እርግጥ ነው የሥራ ኃላፊዎች ተቋሙን በሚመሩ ጊዜ በግዴለሽነት ወይም ደግሞ አውቀው እንዲህ ዓይነት ነገሮች እንዳይፈፀሙ ለማድረግና አስቻይ ሁኔታ በመፍጠር ሊጠየቁ ይችላሉ፤ ይገባልም። ጥያቄው ግን ሌብነት የሚባለው ጉዳይ ሥርዓታዊ በሆነ በራሱ የሌብነት ሰንሰለት ተዘርግቶ ልክ ከከፍተኛ አመራሮች ጭምር እየተሠራ ያለበት ጉዳይ መሆኑ ነው። እርግጥ የመንግሥት ሰዎች ይህንን አያውቁም፤ ወይ ደግሞ ከእነሱ ትኩረት የተሰወረ ነው ልንል አንችልም። ምክንያቱም አሁንም በመንግሥት መዋቅር ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብት እየተመዘበረ ነው ያለው።

ስለዚህ የፀረ-ሌብነት እንቅስቃሴ በሚፈለገው ደረጃ ውጤት እንዳያመጣ ምክንያት የሆነው ባህል ሆኖ እንደመብት የተቆጠረበት ደረጃ በመድረሱ ነው። በሁለተኛ ደረጃ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ አንዳንድ አመራሮች ስለሚሳተፉበት ራሳቸውን አጋልጠው የማይሰጡ በመሆኑም ጭምር ነው። እንዲሁም አሁን ያለውን የፖለቲካ ችግር እንደሽፋን በመጠቀም ሰዎች ዘርፈው፤ ሰርቀውና አጭበርብረው ሲጠየቁ «የዚህ ብሔር አባል ስለሆንኩኝ ነው፤ የዚህ ሃይማኖት ተከታይ ስለሆንኩኝ ነው» በማለት ነገሩ ተድበስብሶ እንዲያልፍ የሚደረግበት ሁኔታ አለ። በተጨማሪም ትልልቅ የወንጀል ክሶች ቀርበው ሰዎች ሲከሰሱ የፖለቲካ ምህዳርን ለማስፋት በሚል የሚለቀቁ ሰዎች መኖራቸው በራሱ ወንጀሉ እንዲበረታታ አድርጎታል ባይ ነኝ። ለምሳሌ የሜቴክ ጉዳይን ማንሳት ይቻላል፤ ክሱ በመቋረጡ መንግሥት በሚሊዮን የሚቆጠር ሀብት አጥቶበታል።

በአጠቃላይ ባለፉት አራት ዓመታት ሌብነትን ከምንጩ ለማድረቅ የተጀመሩ ሥራዎች ቢኖሩም ይሄነው የሚባል ለውጥ አልመጣም። ለዚህ ደግሞ በዋናነት መንግሥት በተለያየ ጊዜ ጫና ላይ ሲሆን እዚያ ላይ በማተኮሩ ለዚያ ለገባበት ጫና እንደማስተንፈሻ ተጠቅመውበታል የሚል እምነት አለኝ። ከዚህ ባሻገር በሌብነት ላይ የተሳተፉ ሰዎችንም በሚገባ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ ያለመቻሉም ችግሩን አባብሶታል ባይ ነኝ። እርግጥ ነው በተለይ ጠቅላይ አቃቢ ሕግ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ክሶችን የማቋረጥ ስልጣን አለው፤ እሱም ቢሆን በተወሰነ ደረጃ የሕዝብ ጥቅምን አደጋ ላይ የጣሉ ሰዎችን በዚህኛው ቀዳዳ እንዲያመልጡ ዕድል የፈጠረ ነው ብዬ አምናለሁ።

በሌላ በኩል ሌቦችን የሚያጋልጡ ሰዎች ደህንነታቸውን የሚያስጠብቅ ሕግና ተቋምም አለመኖሩ ለሌብነቱም ሆነ ለሌቦቹ መስፋፋት አንዱ ችግር ነው። እርግጥ ነው የምስክሮች ጥበቃ የሚባል አዋጅ አለ፤ ግን ብዙ ጊዜ በይፋ ክስ ተመስርቶ ፍርድ ቤት ለሚቀርቡ ጉዳዮች እንጂ ለሚሰጡ ጥቆማዎች እምብዛም የሉም። በአገሪቱ ይህንን የሚያደርግ የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ የለም። ስለዚህ የሕግ ማዕቀፍ አለመኖሩ እንዲሁም በተቋም ደረጃ የፀረ-ሙስና ኮሚሽንም ቢሆን ጠንካራ ያለመሆኑ በራሱ ሌቦች እንዲበረታቱ ምክንያት ሆኗል። በተለይም ይህ ተቋም ከሶ፤ ተከራክሮ ተጠያቂ የማድረጉ ስልጣን ወደ ጠቅላይ አቃቢ ሕግ መሄዱ በራሱ የፈጠረው ችግር አለ። ይህ መሆኑ በመርህ ደረጃ ችግር ባይኖረውም ግን ደግሞ ኮሚሽኑ ራሱ መርምሮና አጣርቶ ሰዎቹን ለፍትሕ አቅርቦ የሚያስወስንበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት። ጎን ለጎንም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችንም ሊሠራ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ መንግሥት ሌብነትን ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማምጣት ብሔራዊ የጸረሙስና ኮሚቴ ማቋቋሙ ምን ያህል ችግሩን ይፈታዋል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ መስዑድ፡-** አስቀድሜ እንደገለፅኩልሽ ብሔራዊ የጸረሙስና ኮሚቴ መቋቋሙ በራሱ የሚበረታታና መንግሥት ተጠያቂነት ለማምጣት ቁርጠኛ መሆኑን ማሳያ ነው። ይሁንና አሁን ላይ ሌብነት በራሱ ሥርዓት ዘርግቶ እየተፈፀመ ያለ ወንጀል ስለሆነ በኮሚቴ ደረጃ ብቻ ሥራ ተሠርቶ ለውጥ ይመጣበታል ብዬ አላምንም። ከዚያ በተጨማሪ እዚህ ላይ ኃላፊነት ተሰጥቶት የተቋቋመ ተቋም ኃላፊነቱን አስፍቶ የበለጠ አቅሙን በማሳደግ ፀረ-ሌብነት ትግሉን በበላይነት እንዲመራው መደረግ ነው የሚገባው። አሁን ባለው ሁኔታ ካልተሳሳትኩት የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ይመስለኛል። ከዚህ ይልቅ የሕዝብ አድርጎ ከሕዝብ ጋር ቅርበት ፈጥሮ እንዲሠራ

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

ማድረግ ያስፈልጋል ባይ ነኝ።

በተጨማሪም ሌቦችን የሚያጋልጡ ሰዎችን በመሸለምም፤ ጥበቃ በማድረግም ሊያበረታታ ይገባል። በሌብነት ተጠርጥረው የሚያዙ ሰዎችን ደግሞ በማናቸውም ሁኔታ ክሳቸው የማይቋረጥበት፤ ለፖለቲካው ምህዳር መስፋት ወይም በሌላ ብዙም አጥጋቢ ባልሆነ ምክንያት እንዳይፈጠር ተደርጎ ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ ወጥቶለት በሕግ አግባብ ተጠያቂነትን ማምጣት ያስፈልጋል። በተለይም ለእንደዚህ ዓይነት ተግባር የበለጠ ተጋላጭ ናቸው የሚባሉ ተቋማት ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ ይገባል። ለምሳሌ ግዢ ኤጀንሲ ጋር ተያይዞ ብዙ የሚቀርቡ ቅሬታዎች አሉ፤ ገቢዎች አካባቢም ታክስ በመሰወር የሚታዩ ወንጀሎች ላይ በጣም ጠንካራ የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት እርምጃ መውሰድ ይገባል። ጎን ለጎንም ከሃይማኖት ተቋማት፤ ከሲቪል ማህበራት ጋር በመሆን ግንዛቤ በማስጨበጥ ሌብነትን የሚፀየፍ ዜጋ የማፍራቱ ሂደት መጠናከር አለበት።

ይህንንም በተከታታይ በመተግበር ባህል ካላደረግነው አሁንም ቢሆን ስጋቴ የተጀመረው ዘመቻ የአጭር ጊዜ ሆኖ ከዚያ በኋላ የሚረሳ እንዳይሆን ነው። ይህ መሆን ካልተቻለ እንዲያውም ሌቦችን በጣም በረቀቀ መንገድ ስርቆት እንዲፈፅሙ የሚያበረታታ ስለሚሆን እዚህ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ነው የማምነው። ሌብነት ላይ በሚዲያ ከሚነገረው በተጨማሪ መሬት ላይ ደግሞ የሚታይ የሚጨበጥ እርምጃን መውሰድ ይገባል። ምክንያቱም ሕዝቡ መንግሥትን ማገዝ የሚችለው የሚጨበጥ እርምጃ ሲያይ ነው። በተጨማሪም የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት፣ይህን ደግሞ ከጸረ- ሙስና ኮሚሽንና ለዚህ ከተቋቋመው ብሔራዊ የጸረሙስና ኮሚቴ ጋር በማገናኘት ከሲቪል ሶሳይቲ ከአካባቢ ተቋማት ጋርም የግንዛቤ ማስጨበጡን ሥራ መሠራት አለበት። ሌብነትን የሚጸየፍ ማኅበረሰብ የመፍጠር ሂደት፤ በተወሰነ ጊዜ የዘመቻ ሥራ ሊሆን አይገባም። በተቋም ደረጃ ሀብት መድቦ ሰፊ ተከታታይነት ያለው ሥራ መሥራት ካልተቻለ እንዲያውም ሌቦችን በጣም በረቀቀ ዘዴ ሌብነትን እንዲፈጽሙ ስለሚያደርግ ጥንቃቄ ማድረግ እና በብዙሃን መገናኛ ጉዳዩ ትኩረት የተሰጠው አድርጎ ማቅረብ ያስፈልጋል።

መሬት ላይ ደግሞ የሚታይ ርምጃ እየወሰዱ ማኅበረሰቡ መንግሥት እያደረገ ያለውን ተግባር እያደነቀና ድጋፍ እየሰጠ እንዲቀጥል ማድረግ ይገባል። ማኅበረሰቡ የሚጨበጥ ነገር ማየት ይፈልጋል። ስለዚህ በተግባር መሬት ላይ በሌብነት የተሰማሩ ሰዎችን ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በሌብነት የተገኘ ሀብትንም መልሶ የሕዝብ በማድረግ ወደ ነበረበት እንዲመለስ በማድረግ፣ እንዲህ ዓይነት ክሶችን ደግሞ በአፋጣኝ መልስ በመስጠት ማሳየት ያስፈልጋል። እንዲህ ዓይነት ነገሮችን በአፋጣኝ ልስ መስጠት የግድ የሚል ነው። ምክንያቱም በተራዘመ ቁጥር ከተጠያቂነት የሚያመልጡበት መንገድ ይሰፋል። በአጠቃላይ መከላከሉ ላይ አተኩሮ መሥራት በጣም አስፈላጊ ነው ብዬ አስባሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ይህንን ሲሉ ብሔራዊ የጸረሙስና ኮሚቴ መቋቋሙ በራሱ ብቻውን ችግሩን በዘላቂነት አይፈታውም እያሉ ነው?**

**አቶ መስኡድ፡-** ይህንን ስል ልብ እንድትዪልኝ የምፈልገው ነገር ብሔራዊ የጸረሙስና ኮሚቴ መቋቋሙ ተገቢ አይደለም እያልኩ አለመሆኑን ነው። አስቀድሜ እንዳልኩሽም የሚበረታታና የመንግሥትን ቁርጠኝነት አንዱ ማሳያ ነው። ግን ደግሞ ተቋም እየገነቡ መሄድ እንጂ በተቋም ላይ ሌላ ተቋም መፍጠር አስፈላጊ አይደለም። እርግጥ ነው የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ከሰባቱ የኮሚቴ አባላት አንዱ ናቸው። በመርህ ደረጃ ብዙ ችግር ያለው አይደለም። ግን አሁንም በአገር ውስጥ በሪፎርሙ የሚቀርበው ትችት ተቋማዊ አልሆነም በሚል ነው። ደግሞም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ብዙ ጉዳዮች ላይ በጣም ተጨናንቀው ከአቅማቸው በላይ እንዲሠራ ያደርጋሉ፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ግን የተቋቋሙበትን ዓላማ በአግባቡ እየፈጸሙ አይደለም። ያለመፈጸማቸውም ሪፎርሙ ወደ መሬት ባለመውረዱ፤ ወደ ክልል፣ ወደ ዞንና ወረዳ ስንመጣ ችግሩ በጣም የተንሰራፋ ሆኖ በመገኘቱ ነው። በእኔ እምነት ሪፎርሙ ተግባራዊ እንዳይሆን ያደረገው ተቋማዊ ችግር ከሆነ የስልጣን ከሆነ ስልጣኑን ማሻሻል፣ የመፈጸም አቅም ከሆነ የመፈጸም አቅሙን ጥናት አድርጎ ማሻሻል ነው የሚገባው።



ሰዎች ሌብነትን ቀላል እያደረጉት የመጡት ሰርቆ መለወጥ ትልቅ ደረጃ መድረስ እንደሚቻል፤ ሰርቆ ምንም ችግር አይመጣም የሚለው ልምምድ የፈጠሩት የተጠያቂነት ሥርዓቱ ደካማ በመሆኑ ነው

እንደሚታወቀው ተቋሙ በአዋጅ የተቋቋመ ነው፤ ግብረ-ኃይል ወይም ኮሚቴ መቋቋሙ ደግሞ ከአዋጅ ባነሰ መመሪያ የኮሚሽኑን ስልጣን ለሌላ አሳልፎ እንደመስጠት ሆኖ ነው የሚታየኝ። በርግጥ ሃሳቡ ጥሩ ነው የሚበረታታ ነው፣ ሁኔታውንም እገነዘበዋለሁ። ግን ደግሞ ተቋማትን እየገነባን፣ ሥርዓት እየፈጠርን መቀጠል ጥሩ ነው። የሕግ-ማዕቀፍ ከሆነ ሕግን ማሻሻል፣ የማሻሻል አቅም ከሆነ የአቅም ማሻሻያ ሥራ መሥራት ተገቢ ነው። የአመለካከት ባህል ማሳደጉ ላይ ነው ብዙ ሥራ መሠራት ያለበት። ምክንያቱም ሰዎች ሌብነትን ቀላል እያደረጉት የመጡት ሰርቆ መለወጥ ትልቅ ደረጃ መድረስ እንደሚቻል፤ ሰርቆ ምንም ችግር አይመጣም የሚለው ልምምድ የፈጠሩት የተጠያቂነት ሥርዓቱ ደካማ በመሆኑ ነው። ሌብነትን የሚጠየፍ ባህል ለመፍጠር ደግሞ ከታች ጀምሮ ሥነ- ምግባር ላይ መሥራት፣ የትምህርት ሥርዓቱን ማሻሻል፣ የሃይማኖት ተቋማትና ከሲቪል ሶሳይቲ እና ከብዙኃን መገናኛ ጋር መሥራት፣ የምርመራ ጋዜጠኝነትን ማበረታታትና እውቅና በመስጠት በምክረ ሃሳቦች መሠረት መሥራት ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ከሀብት ምዝገባ ጋር ተያይዞ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ምዝገባ ተካሂዷል፣ አሁንም እየተካሄደ ይገኛል ።ነገር ግን ምንም ውጤት አይታይበትም። ለመሆኑ ምክንያቱ ምንድን ነው ብለው ያምናሉ?**

**አቶ መስኡድ፡-** አንቺም እንዳልሽው ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለዓመታት ሲሠራ የቆየው ይህንኑ ነው። ከሆነ ደረጃ በላይ ያሉ ወይም ደግሞ በባህሪያቸው ለሌብነት ተጋላጭ ናቸው ተብሎ የሚገመቱ ተቋማት ላይ የሚሠሩ ሰዎች ያላቸውን ሀብት እንዲያስመዘግቡ ይደረጋል። ከመጀመሪያውም ቢሆን የሰረቀ ሰው የሰረቀውን በራሱ ስም አያስመዘግብም፤ ይሄንን ማንም ተራ ሰው ሊሠራው የሚችለው ስሌት ነው። ስለዚህ ያስመዘገብከው ሀብት ይሄ ነው፤ አሁን ግን ካስመዘገብክ በኋላ እንዲህ ዓይነት ሀብት በስምህ ተገኝቷልና ትጠየቃለህ ብሎ መሄድ በራሱ ስሜት አይሰጠኝም። ሌባ የሰረቀውን ንብረት አስመልክቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለምክር ቤት እንደተናገሩት የሰረቁ ሰዎች የሰረቁትን ገንዘብ ወደ ገበያው አያስገቡም፤ ምክንያቱም ደግሞ በሕገወጥ መንገድ ገንዘብ ያገኘ ሰው በሕጋዊ መልኩ ግብይት አያደርግም።

በመሆኑም በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብ በሕጋዊ መልኩ ገበያ ውስጥ ስለማይገባ የሕገ ወጥ ንግድ፣ የውጭ ምንዛሬ በጥቁር ገበያ እና በመሳሰሉት ሕገ ወጥ መንገዶች ነው ገንዘቡ ዝውውር የሚያደርገው። ወይንም ከአገር ውጪ ወጥቶ ነው የሚቀመጠው። ይህ ደግሞ ለአገር ኢኮኖሚ ፋይዳ አይሰጥም። ይሁን እንጂ ሌብነት የሚበረታታ ጉዳይ ባይሆንም ሰርቆ ሆቴል ገንብቶ የሆቴል አገልግሎት ቢሰጥ ይህም አንድ ነገር ነው። ግን ደግሞ የተሰረቀ ገንዘብ ወደ ሕጋዊ ሂደቱ ሲገባ ‹‹ከየት መጣ?›› የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ስለሚችል ሰው ይህንን አይመርጥም። በሩቅ ዘመድ ወይንም በሽርክና አብሮ ከሚሠራ ሰው ጋር፣ በሕገ ወጥ መንገድ በዘረጓቸው ኔትወርኮች ነው የሚፈፅሙት።

ለምሳሌ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ጠቅላይ ላይ ሚኒስትሩ ሲያነሱ አዲስ አበባ ውስጥ ኦዲት ሲደረግ በርካታ ትላልቅ ባለቤት የሌላቸው ሕንፃዎች ተገኝተዋል። ሕንፃ ድንገት አይበቅልም። ሕንፃ እንደጨረቃ ቤት በአንድ ጀምበር አይገነባም። ለሕንፃ ሲገነባ ብዙ የሚያስፈልጉ ግብቶች ሊሟሉለት ይገባል፤ ደግሞም በሆነ ሰው ስም ካልተመዘገበ ሊጀመር አይችልም። በአጠቃላይ የሀብት ምዝገባ ሂደቱ ጥሩ ነው። ነገር ግን ንብረትን መርምሮ ከዚህ በላይ ያለው ንብረት ካንተ ገቢ ጋር አይጣጣምም ማለት በራሱ ቀልድ ነው የሚመስለኝ። ደግሞም ከልብ ለውጥ ያመጣል ብዬ አልገምትም። ሰዎች ሰርቃችኋል ተብለው ሲጠረጠሩ ንጽህናቸውን ለማወጅ ይህንን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ያስመዘገብኩት የራሴ ነው ማለት ይችላሉ።

በተለያየ ጊዜ ከዚህ ጋር ተያይዞ አንዳንድ ንጹህ የሆኑ ባለስልጣናትም ሲከሰሱ፣ ሲታሰሩና ሲጠየቁ እናያለን። ይሄ በፖለቲካው ውስጥ ሲፈጠሩ የምናያቸው ችግሮች ናቸው። ግን ይሄ ብዙ ለውጥ ያመጣል ብዬ አላስብም። ወደ ትክክለኛ መንገዱ ወደ ገበያው ስለማይገባ ማለት ነው። በዋናነት አሁንም በዚህ ላይ የመንግሥትን ቁርጠኝነት እንደመልካም አጋጣሚ በመውሰድ፣ ከተጠያቂነት ጋር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተባብሮ ጠንክሮ በመሥራት ለውጥ ይመጣ የሚል እምነት ነው ያለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ በአ ንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግ ናለሁ።**

**አቶ መስኡድ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# ለህሙማን ፈውስ የመንፈስ ህክምና

**እፀገነት አክሊሉ**

በህመም እየተሰቃዩ አልጋ ይዘው በቤትም ይሁን በየሆስፒታሉ ያሉ ሰዎች ከምንም በላይ የሚፈልጉት «ፈጣሪ ይማርህ» የሚላቸውን ጠያቂ ነው። ይህ ቃል በውስጡ ብዙ ነገር የያዘ በመሆኑም በታማሚዎቹ ላይ የሚፈጥረው የስነ ልቦና ጥንካሬ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

በተለይም ራቅ ካለ አካባቢ ለህክምና የመጡ ብሎም አካባቢያቸውም ላይ ሆነው ጠያቂ ተመልካች ወገን የሌላቸው በርካቶች አይናቸው ከሚቁለጨለጭበትና በልባቸው ከሚያዝኑበት ነገር አንዱ ጠያቂ ማጣታቸው ነው። በመሠረቱ አንዳንድ ጥሩ ልምድ ያላቸው ሰዎች የማያውቁትን የታመመን ብቻ ሳይሆን የታሰረን ሰውም እየሄዱ የሚጎበኙ አሉ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል ሃምሳ አለቃ ዘሪሁን ደጋጋ አንዱ ናቸው።

ሃምሳ አለቃ ዘሪሁንን ያገኘናቸው በአለርት ሆስፒታል የታካሚዎች መንፈሳዊ የህክምን ቀን በማለት በየዓመቱ በሚያዘጋጀው የጥየቃ ፕሮግራም ላይ ነው። ሃምሳ አለቃ ዘሪሁንን ለየት የሚያደርጋቸው ቀኑን ምክንያት አድርገው ሳይሆን በግቢው የተገኙት ሁሌም የማያውቋቸውን በሽተኞች እየዞሩ ፈጣሪ ይማራችሁ የማለት ልምድ ስላላቸው ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሃምሳ አለቃ ዘሪሁን በቅርቡ ለአንድ ወር ያህል በሆስፒታል ተኝተው ህክምና ሲያገኙ ቆይተው ወደሙሉ ጤንነታቸው ተመልሰው ቤታቸው ገብተዋል። ያም ተጨምሮ አሁን ላይ አስታማሚና ጠያቂ የሌላቸው ወገኖች የፈጣሪን ፈውስ አግኝተው ከበሽታቸው አገግመው ቤታቸው ይገቡ ዘንድ በተወሰኑ ቀናት ልዩነት «ምህረቱን ይላክላችሁ» ሊሉ በሆስፒታሉ ይገኛሉ።

ሃምሳ አለቃ ዘሪሁን «እኛ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለን ኢትዮጵያውያን ነን። ሌላው መገለጫችን ደግሞ እርስ በእርስ የምንተዛዘነውና የምንጠያየቀው ነገር ነው፤ በመሆኑም እኔም በሚመቸኝ ቀንና ሰዓት እየመጣሁ ወገኖቼን ፈጣሪ ምህረት ይላክላችሁ ማለት ለእኔ ቀላል ለሰዎቹ ግን ትልቅ ዋጋ ያለውና በመንፈስም በአካልም የሚያጠነክራቸው በመሆኑ ሕይወቴ እስካለም ድረስ ይህንን ዓይነቱን ተግባር አጠናክሬ እቀጥልበታለሁ» ይላሉ።

ሃምሳለቃ ዘሪሁን ሁሉም ሰው ይህንን ነገር ልምድ ቢያደርገው የሚያዝን የሚተክዝ አይኖርም በማለት ሀሳባቸውን ይሰጣሉ።

«የሃይማኖት አባቶች ጉብኝት ለታካሚዎች ፈውስ ጉልህ አስተዋጽዖ አለው» በሚል አለርት ሆስፒታል ለአምስት ተከታታይ አመታት ይህንን ሥራ ሲሠራ ቆይቷል። በዚህም ብዙ ጥቅሞች ስለመገኘታቸው ይነገራል። የሃይማኖት አባቶች በየመኝታ ክፍሉ እየተዘዋወሩ «ፈጣሪ ይማራችሁ» ሲሉም በህሙማን ላይ የሚታየው መንፈሳዊ ደስታና የመፈወስ ስሜት በእውነት ላቅ ያለ ነው። በተለይም አስታማሚ የሌላቸው በተለያዩ ምክንያቶች ቦታው ላይ የተገኙ ሁሉ ይህንን የፈውስ በረከት ለማግኘት አቅማቸውን ሁሉ አሟጠው ቀና ሲሉ ማየት ደስታው የተለየ ነው።

ከደብረ ቢታንያ አቡነተክለሃይማኖትና ቅድስት ልደታ ለማርያም ቤተክርስቲያን የመጡት ቀሲስ ለይኩን ብርሃኑ እንደሚሉት አለርት ሆስፒታል ከሌሎች ሁሉ ለየት የሚያደርገው ከሚሰጠው ስጋዊ ህክምና ጎን ለጎን ተኝተው ለሚታከሙ ህሙማኑ የመንፈስም ህክምና ያሻቸዋል በማለት በየዓመቱ የሃይማኖት አባቶችን እየጠራ ጸሎት እንዲደረግ «እግዚአብሔር ይማራችሁ» እንዲባሉ ያደርጋል፤ ይህ በእውነቱ በጣም አስደሳች ነው በሰዎቹ ላይ የሚፈጥረውንም ደስታ እየተመለከትነው ነው ።

«እኛ ገብተን ማጥንት ስናጥን መስቀል ስናሳልማቸው ከአልጋቸው መነሳት ያቃታቸው ህሙማን ሳይቀር ተነስተው እልል እያሉ የሚያሳዩት ደስታ በቃላት የሚገለጽ አይደለም ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሁሉም በየእምነታቸው መቼ ቤተክርስቲያን ሄጄ መስቀል



ተሳልሜ ማጠንት ሽቶኝ ብለው የሚመኙ መሆናቸው ነው እነዚህን ሰዎች እግዚአብሔር ይማራችሁ ማለት ለእነሱም ተስፋ ነው» ብለዋል።

ህክምና የሚጀምረው ከአእምሮ ነው የሚሉት ቀሲስ ለይኩን እነዚህ ሰዎች በዚህ መልኩ መጎብኘታችን ከፍ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነው ሌሎች ሆስፒታሎችም ይህንን አካሄድ ቢከተሉት ለሚያክሚቸው ህሙማኖቻቸው ከፍ ያለ ጥቅም አለው በማለት ይመክራሉ።

ካርዲናል አቡነ ብርሃነ እየሱስ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳስና የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጳጳሳት ጉባኤ ፕሬዚዳንት ዕለቱን አስመልክተው ሲናገሩ የሃይማኖት አባቶች ህሙማንን ጎብኙ ብሎ አለርት ሆስፒታል ሲጠራን ላቅ ያለ ደስታ ተሰምቶኝ ነው የመጣሁት።

ሆስፒታሉ ሰፊና ብዙ ዘርፎች ያሉት ታካሚዎቹም በዚያው ልክ ቁጥራቸው ላቅ ያለ ነው። እነዚህን ህሙማን በቦታው ላይ ተገኝቶ መጠየቅ አስታማሚዎችን በርቱ ማለት ደግሞ ጥቅሙ ከምንም በላይ ላቅ ያለ ነው በማለት ይናገራሉ።

የሃይማኖት አባቶች ምእመኖቻችንን ማስተማር በምግባር ማነጽ ትልቁ ሥራችን ነው፤ ከዚያ አልፎ ደግሞ ችግር፣ ህመም፣ ጉስቁልና ሲደርስባቸው ከጎናቸው ሆነን አይዟችሁ ያልፋል ፈጣሪ ይርዳችሁ ይማራችሁ ማለት ደግሞ ይጠበቅብናል። ሆስፒታሉም ይህንን የሰው ልጆችን የሚቀይር የሚያረጋጋና የሚያጽናና ተግባር በየዓመቱ ማዘጋጀቱ ሊያስመሰግነው እንደሚገባም ተናግረዋል።

«ወንጌሉ የታመመን ጠይቅ» ይላል የታመመን የምንጠይቀው ደግሞ እቤቱ አልያም በየሆስፒታሉ ነው። ይህንን ባደረግን መጠን ፈጣሪያችንን ያዘዘንን ተወጥተናል ማለት ነው ። ስለዚህ ሁሉም ምዕመን ዛሬ ጤነኛ ቢሆን ነገ ተራው ሲደርስ ታማሚ የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለምና በተቻለ መጠን አወቅነው አላወቅነው ሳንል የታመመን መጎብኘት ልምዳችን ልናደርግ ይገባል ሲሉም መክረዋል።

የሚፍታህ መስኪድ ዋና ኢማም ሼህ መሀመድ ፈትህ አለርት ሆስፒታል የሁላችንም ነው፤ በተለይም በዚህ መልኩ የሁሉንም እምነት ተወካዮች ጠርቶ ህሙማንን ጎብኙልን በዱኣ አስቡን ማለቱ ሊያስመሰግነው የሚገባ ነገር ነው።

ምን ጊዜም ሰዎች ስንታመም ስጋዊ ፈውስን ፈልገን ወደ ሆስፒታሎች ብንሄድም ልባችን ያለው እምነታችን ላይ የፈጠረን አምላክ ጋር ነው፤ በዚህ መልኩ ደግሞ ታማሚው የእምነት አባቱ ያለበት ቦታ ድረስ ቀርቦ ፈጣሪ ይማርህ "አላህ ያሽር" ሲለው የሚሰማው ፈውስ እንዲህ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም። በመሆኑም ሆስፒታሉም በዚህ መልኩ መሄዱ ሥራውን ውጤታማ ያደርግለታል ለሌላውም አርዓያ ሊሆን የሚገባ ሥራ ነው።

የእኛ ጸሎት ለታማሚው ብቻ ሳይሆን ጥበቡን ገልጦላቸው ህክምና ለሚሰጡት ባለሙያዎች በሙሉ ነው፤ በመሆኑም በሆስፒታሉ መጥተው ህክምና ላይ ያሉትን ህክምና በመስጠት ላይ ያሉ ባለሙያዎችም አላህ ጥበቡን ይግለጽላቸው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ህብረት አገልጋይ መጋቢ ሰለሞን ተስፋዬ እንዳሉት ደግሞ ፈጣሪያችንም ያለው «ታምሜ አልጠየቃችሁኝም፤ ታርዤ አላለበሳችሁኝም ነው» የት ነው ታመህ ያልጠየቅንህ ብለው ሲጠይቁትም «የታመሙትን አልጠየቃችሁም» የሚል ምላሽ ነው የሰጣቸው፤ በመሆኑም ሰውን ታሞ መጠየቅ ጌታ እየሱስ ያስቀመጣቸው ዋና ነገሮች ናቸው ይላሉ።

በሌላ በኩልም እንደ ሰውም ሆነ እንደ ሃይማኖት አባት በየሆስፒታሉ በአጋጣሚ እንኳን ገብተን ስንጠይቅና ፈጣሪ ይማራችሁ ስንላቸው ሃይማኖታችንን እንኳን ሳያውቁ በአንድ ቃል «አሜን» ነው የሚሉት ይህ የሆነው ደግሞ የፈጣሪ ስም የማጽናናት የመፈወስ ኃይሉ ከፍ ያለ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ይህችን አንድ ቃል ተናግረን ሰዎችን ከህመማቸው የምንፈውስ ከሆነ በየጊዜው በየሆስፒታሉ ያሉ ወገኖቻችንን ሄደን የመጎብኘት ልምድ ይኑረን ይላሉ ።

«የተቸገሩ በተለይም የታሰሩና የታመሙ ሰዎችን መጠየቅ ትልቅ ዋጋ የሚያሰጥ ነገር ነው፤ በመሆኑም እግረ መንገዳችንን እንኳን ወደ ሆስፒታሎች ጎራ እያልን የታመሙትን የተጨነቁትን ወገኖቻችንን እግዚአብሔር ይማራችሁ አስታማሚዎችንም ብርታት ይስጣችሁ ብንል በምድር ከፍ ያለ እርካታ በሰማይም ዋጋው ትልቅ ነው፤ በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

አለርት ሆስፒታልም ከሚሰጠው ስጋዊ ህክምና ባሻገር ሰዎች በመንፈስም ሊታከሙ ይገባል ብሎ ይህንን ዓይነቱን ሥራ በየዓመቱ አለማቋረጥ ማካሄዱ ሊያስመሰግነው ለሌሎች ሆስፒታሎችም አርዓያ ሊሆንበት የሚገባ ሥራ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል።

የሆስፒታሉ ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ሽመልስ ገዛኸኝ እንዳሉት በተለያየ ሆስፒታል ከተራ ሠራተኝነት ጀምሮ በኃላፊነት ደረጃ ሠርቻለሁ በዚህን ያህል ህሙማን ከስጋዊ ህክምና ጎን ለጎን መንፈሳዊ ፈውስ ያስፈልጋቸዋል ብሎ የሠራ አላየሁም፤ አለርትም በዚህ በጣም ልዩና ሊመሰገን የሚገባው ሥራ እየሠራ ነው ብለዋል።

እኛ የስጋ ህክምና የማስታገሻ መድኃኒት ልንሰጥ እንችላለን፤ እናንተ ደግሞ መንፈሳዊውን እና ትልቁን ለሰው ልጆች ሁሉ አስፈላጊ የሆነውን ህክምና የምትሰጡ ናችሁ፤ በዚህ ልክ እናንተም ወደኛ መጥታችሁ መሥራታችን ሆስፒታሉ የተሟላ ህክምና የሚሰጥ ተቋም ያደርገዋል ይላሉ።

ወደፊትም ይህ መሰሉ ሥራ በዓመት አንዴ ከመሆን አልፎ ሁለቴና ሦስቴ ይሠራል፤ እኔ ለቦታው አዲስ ነኝ ነገር ግን ጅምሩ ጥሩ በመሆኑ ወደፊትም ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን መንገድ በበኩሌ አመቻቻለሁ ብለዋል።

እናንተ በዚህ ተገኝታችሁ መጎብኘታችሁ የፈውስ አገልግሎት መስጠታችሁ ሆስፒታሉ የእኛ ነው ህሙማኑም የእኛው ናቸው ብላችሁ መምጣታችሁ ለእኔ ትልቅ ነገር ነው ወደፊትም ጸሎት ልመናችሁ እንዳይለየን ይላሉ።

ከሰላሌ የመጡት ታካሚ ወይዘሮ መሠረት በቀለ እግራቸው ተቆርጦ ሰፊ ህክምናን እየተከታተሉ ነው ። በዚህ መልኩ የናፈቃቸውን የሃይማኖት አባቶች ድምጽ የተኙበት ድረስ መጥቶ መስማታቸው ህመማቸውን እንዲረሱ እንዳደረጋቸው ይናገራሉ።

«በሽተኛ የሰው ዓይንና ድምጽ በተለይም እግዚአብሔር ይማርህ የሚለውን ቃል አብዝቶ ይናፍቃል፤ እንደእኛ ራቅ ካለ አካባቢ የመጣ ሰው ደግሞ ጠያቂም የለውም፤ በዚህ መልኩ ሃይማኖት አባቶች መጥተው ስለጎበኙን የተሰማኝ ደስታ ወደር የለውም፤ በሽታዬንም ረሳሁት» በማለት ከፍ ባለ የደስታ ስሜት ውስጥ ሆነው ሀሳባቸውን ገልጸዋል።

አቶ ደረሰ አዳሙ ከደራ ወረዳ የመጡት የስጋ ደዌ ህመም ታማሚና ለህክምና ብቻቸውን የመጡ ናቸው። ለአገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ ቢሆኑም በተለይ የሃይማኖት አባቶች በዚህ መልኩ መጥተው ሲጎበኟቸው እጃቸውን ይዘው አይዞህ በርትታ ትድናለህ ማለታቸው በጣም እንዳስደሰታቸው ነው የተናገሩት።

አቶ ደረሰ ሆስፒታሉ ከሚሰጠን ህክምና ጎን ለጎን በዚህ መልኩ በእምነታችን እንድንጽናና ያደረገው ጥረት ሌሎች ቦታዎች ያላየነው በጣምም የሚያስመሰግን ነው በማለት ሀሳባቸውን ይገልጻሉ።

አለርት ሆስፒታል «የታካሚ መንፈሳዊ የህክምን ቀን» ብሎ በዚህ መልክ የሃይማኖት አባቶችን አሰባስቦ ማስጎብኘቱ በህሙማኑ ላይ ከፍ ያለ የደስታና የእረፍት ስሜት ሲፈጥር ተመልክተናል ። ሌሎች ሆስፒታሎችም ከሚሰጡት የስጋዊ ህክምና ጎን ለጎን ይህንን ተሞክሮ ቢወስዱት መልካም መሆኑንም ለመግለጽ እንወዳለን።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# የሀገራዊ ተስፋችን ሙላት

**ተስፋ ማለት...**

ከዓመታት በፊት ያነበብኩትን አንድ ጥቅስ በሚገባ ቃል በቃል አስታውሰዋለሁ። እንዲህ ነበር የሚለው፤ “የሰው ልጅ ያለ ምግብ አርባ ቀናት፣ ያለ ውሃ ሦስት ቀናት፣ ያለ አየር ስምንት ደቂቃ መቆየት ይችላል። ያለ ተስፋ ግን አንድም ሰከንድ መኖር ከቶም አይችልም። ” የዚህ ጽሑፍ ዋነኛ ትኩረት በጥቅሱ ውስጥ ሁነኛ አጽንኦት ስለተሰጠው መሠረታዊ የሰው ልጆች ሁሉ የጋራ ጉዳይ በሆነው ተስፋ ላይ ይሆናል።

ያለ ምግብ፣ ያለ ውሃም ሆነ ያለ አየር የመቆያው ጉዳይ “ያንሳል ወይንም ይበዛል” አሰኝቶ ሊያከራክር ይችል ይሆናል። ለተስፋ የተሰጠውን ማረጋገጫ በተመለከተ ግን የክርክር አታካራ ይገጥመዋል ተብሎ አይታመንም። ምክንያቱም በማናቸውም የሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ተስፋ ሁነኛ መልሕቅ መሆኑ የተረጋገጠ ነውና። የማንኛውም ግለሰብ የሕይወት ድርና ማግ የተሸመነው በተስፋ ነው። ተስፋ ቆርጫለሁ የሚል ሰው እንኳን ተስፋ ለቆረጠበት ችግር መፍትሔ አለ ብሎ ተስፋ እንደሚያደርግ ልብ ሊባል ይገባል። ።

ከአራት አምስት ዐሥርት ዓመታት በፊት በኑሯቸው ተስፋ የቆረጡ የአዲስ አበባ ወጣቶች “ግፋ ቢል አዶላ፤ ጨብጥ ቢል አካፋ” የሚል የተስፋና የመጽናኛ አባባል ነበራቸው። ቢከፋ ቢከፋ አዶላ ሄጄ በወርቅ ቁፋሮ አሰማራለሁ ማለታቸው ነበር። ወርቅ በሚታፈስበት ሀገር ተቸገርኩ ማለት የሀገራዊ ዕንቆቅልሻችንን ግዝፈት በሚገባ የሚያሳይ የወቅቱ መስታወት ብቻም ሳይሆን ዛሬም ቢሆን የተወሳሰበ ሀገራዊ ጉዳያችን እንደሆነ ቀጥሏል።

ከተስፋ መገለጫ ወይንም አመለካከቶች መካከል ጥቂት ማሳያዎችን በማከል ሃሳቡን ለማፍታታት እንሞክር። አንባቢያንም የየግላቸውን መረዳት በማከል “ተስፋ” ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ ማብራሪያ ቢያክሉበት ያለ ጥርጥር ለአንድ መዝገበ ቃላት የሚበቃ ትንታኔ መሰብሰብ ይቻላል።

ሠላሳ ቀናት በመደበኛ ሥራችን ደፋ ቀና ስንል የምንውለው በወሩ መጨረሻ ደመወዝ እንደሚከፈለን ተስፋ በማድረግ ነው። አንድ በሉልኝ። በታክሲ ወይንም በግላችን ትራንስፖርት የምንጓጓዘው ያሰብንበት ቦታ እንደምንደርስ ተስፋ በማድረግ ነው። ሁለት ልንል እንችላለን። ወንበር ስበን ለመቀመጥ ስንዘጋጅ እንኳን መሬቱ ወንበሩንም ሆነ ተቀማጩን መሸከም እንደሚችል ስለምናምን ነው። ሦስት እንበል።

ሕጻናት “ሀ ሁ...” ብለው ፊደል እንዲቆጥሩ ወደ ቄስ ትምህርት ቤት ወይንም እንደ ኑሮ ደረጃችን ከአቅማችው በላይ የሆነ ቦርሳ አሸክመን ወደ መዋዕለ ሕጻናት የምንልካቸው ነገ በእውቀት የበቁ ሆነው ለቤተሰብ ኩራት፣ ለሀገር በረከት እንደሚሆኑ ተስፋ ሰንቀን ነው። አራተኛ ላይ ደርሰናል። ገበሬ በክረምት የእጁን ዘር የሚበትነው የታህሣሥ አዝመራን፣ የጥር ወር ደስታን ተስፋ በማድረግ ነው። እንደ አምስተኛ ምሳሌ ይቆጠር።

ላልዘልቅበት ለምን አንድ፣ ሁለት ብዬ ለመንደርደር እንደሞከርኩ ባይገባኝም ተስፋ በቁጥር ተዘርዝሮና ተዘክሮ እንደማይዘለቅ ግን በሚገባ እረዳለሁ። “ተስፋ ቆርጫለሁ” የሚል ሰው ወደ አንድ ክፉ ውሳኔ ለመሄድ እየተንደረደረ መሆኑ ለማናችንም የተሰወረ አይደለም። ይህንን መቋጫ የሌለውን ጉዳይ እዚህ ላይ ገታ አድርገን ራሳችንንና ሀገራችንን በተስፋ መስታወት ውስጥ ለመመልከት እንሞክር።

**ተስፋ መስጠት፤ ዕዳ ለመግባት መወሰን፤**

የሰሜኑ የሀገራችን ጦርነት ማብቂያው መቃረቡን በተመለከተ የተደረሰበትን የሁለት ወገን ስምምነት በሰማን እለት የነበረው ደስታና በሕዝቡ ውስጥ የተፈጠረውን ተስፋ በቃላት ለመግለጽ ያዳግታል። እናቶች እንደየሃይማኖታቸው በየቤተእምነታቸው ደጅ

> **“የአፍሪካ ዋና ከተማ” እያልን ስናንቆለጳጵሳት የኖረችው አዲስ አበባችን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ስሟና መልኳ መቀራረብ ሲጀምር እያስተዋልን ነው። ስንጓጓለት የነበረው ሀገራዊ ምኞት ወደ ሙላት ደረጃ እየተቃረበ በመሄዱ የላሸቀው ተስፋችን በመነቃቃት ላይ ነው። በአጭር ጊዜያት ተገንብተው ለሕዝብ ይፋ የሆኑት “የአደባባይ ገነቶች” ቁጥር መበራከት እንኳን ለእኛ ለባእዳንም ቢሆን የስበት ኃይል እየሆኑ ነው**

ሰላም ላይ ተንበርክከውና ተደፍተው ፈጣሪያቸውን ያመሰገኑት ምናልባትም ለመጀመሪያ ጊዜ እንባቸውን ዋጥ አድርገውና በምሥጋና ፊታቸው ፈክቶ እንደነበር የበርካታ እምዬዎችን/አደዬዎችን ምስክርነት ሳናደምጥ አልቀረንም። “ፈጣሪ በቃችሁ ብሎ እምባችንን ሊያብስ ቀኑ የደረሰ ይመስላል” በማለት አንድ አባት/አቦይ የተናገሩት የተስፋ ቃል ሁኔታውን በሚገባ ይገልጽ ይመስለኛል።

በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ በደመና ተመስሎ የተከማቸው የተስፋ መቁረጥ ብሶትና የጭንቀት ጣር ከሰላም ስምምነቱ ማግሥት ጀምሮ ጥቂትም ቢሆን የመገፈፍ አዝማሚያ ስለታየበት ሕዝባችን ትልቅ እፎይታ ያገኘ ይመስላል። ቢያንስ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ውስጥ የጦርነትን ዜና ሳንሰማ ውለን ያደርንበትን “ክፉ ቀናት” በቁጭት ስናስታውስ ሰሞንኛውን የሰላም ስምምነት ተስፋ አቅልለን ልንመለከት አይገባም። ተስፋው ዕዳም ጭምር ስለሆነ። ይህ ጉዳይ ከተስፋም ሆነ ከዕዳ በላይ ሆኖ “ሃሌሉያ” ያሰኘን የወቅቱ የደስታችን ምክንያት ስለሆነ ፈራሚዎቹና አስፈራሚዎቹ የተግባራዊነቱን ጉዳይ በጥብቅ እንዲከታተሉ መልእክታችን ይድረስልን እንላለን።

“ትኩሱ ሬሳ፤ ደረቁን አስነሳ” እንዲሉ በዛሬ ማሳያነት ያለፈውን መከራችንን ማስታወሱ የሰላም ስምምነቱን የተስፋ መልሕቅ አጥብቀን ለመጨበጥ ስለሚያግዘን ከቀዳሚዎቹ “ክፉ” ቀናት መካከል በግማሽ ክፍለ ዘመን ውስጥ አድቅቀውን ያለፉትን ጥቂቶቹን የጦርነት ታሪኮች ብቻ እንደሚከተለው እናስታውሳለን።

የደርግ ሥርዓት “ከውልደት እስከ ሞቱ” ዕድሜውን ፈጅቶ ያለፈው በጦርነት ውስጥ እንደነበር ማን ሊረሳ ይችላል? “የምሥራቁና የሰሜኑ” በመባል ይታወቁ የነበሩት ጦርነቶች ትውልዳችንን እንክት፣ እምሽክ አድርገው ለመብላታቸው ምሥክሩ ዛሬም ድረስ እናቶቻችን ያልለወጡት የሀዘን ጨርቃቸውና ያልደረቀው እምባቸው ነው።

በጦርነት ነግሦ የጦርነት ነጋሪት ሲደልቅ ኖሮ “ያሸለበው?” ኢህአዴግም ቢሆን መንበረ ሥልጣኑን ባደላደለ ማግሥት የጦረኛነቱ ሱስ አቅበዝብዞት ጡብመንጃ አስወልውሎ ትውልዱን ወደ ኢትዮ ኤርትራ ጦርነት የማገደው ገና በጠዋቱ ነበር። በዚያ ጦርነት የረገፈውንና በድኑ የአሞራ ሲሳይ ሆኖ በምድረበዳ ወድቆ የቀረውን የኢትዮጵያ ወጣትና አካለ ጎዶሎ ሆኖ የተረፈውን ቤቱ ይቁጠረው ማለቱ ይቀላል። የወደመውን የሀገር ሀብትማ ያለማስላትና ያለመቁጠሩ ይበጃል።

የሀገርን ሀብትና የሺህዎችን ነፍስ ቅርጥፍ አድርጎ አኝኮ ያደቀቀውና ብዙ ወገኖችን አፈናቅሎና ተስፋ አስቆርጦ ምድሪቱን በደም አበላ ያጨቀየው የበቀደሙ የጦርነት ወላፈንም በተስፋ በተቋጠረ ስምምነት ለጊዜውም ቢሆን ጨኸት መቆሙ “ተስፋ” ብለን የምንገልጸው ብቻም ሳይሆን እፎይታ ለማለትም አስችሎናል። በሰላም ንግግሩ ማጠቃለያ ላይ የተገባው ተስፋ ሙሉ ለሙሉ እስኪተገበር ድረስ ግን ሰፊው የዓለም ማኅበረሰብም ሆነ እኛ ባለጉዳዮቹ ዜጎች ፊርማቸውን ያኖሩት ሁለቱ አካላት ወደ ተግባር እርምጃ ፈጥነው እንዲገቡና እፎይታችን ቀጣይነት እንዲኖረው አደራችንን የምናሸክማቸው እንደየእምነታችን በጸሎትና በጾም እየደገፍናቸው ጭምር መሆኑን ሊረዱት ይገባል። ተስፋችንም መክኖ ወደ ተለማመድነው የጦርነት ዜና እንዳንመለስ አደራችንን አጥብቀን እናሸክማቸዋለን።

በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የደረሰው ሰብዓዊና ቁሳዊ ክስረት አልበቃ ብሎ ዳግም ጦርነት አገርሽቶ ሀገሪቱ በባሩድ ጭስ የምትታጠን ከሆነ ግን ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ከመገመት ይልቅ “እክሕደከ ሰይጣን” በማለት ከማማተብ ባለፈ ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ የሰላም ቀበኞቹን ፍጻሜ እውን እንደሚያደርግ በብዙኃን ድምጽ እናረጋግጥላቸዋለን።

እንደ ኢትዮጵያ በብዙ ዘርፈ ችግሮች ውስጥ ተዘፍቆና ተጨንቆ የኖረ ሕዝብና ሀገር አይኖርም ማለት ባይቻልም እኛን መሰል መከራን በአናቱ እንኮኮ በማለት ተሸክሞ ሲንገዳገድ ዘመናትን ያስቆጠረ ተወዳዳሪ ይፈለግ ከተባለ ግን ሊጠቀስ የሚችለው ምናልባትም በግሪኮቹ አፈ ታሪክ ዝነኛ የሆነው “አትላስ” ብቻ ሳይሆን አይቀርም።

አትላስ የግሪክ አማልክት ተባብረው ያለ ጥፋቱ ዓለምን ከነጉዳጉዱ መከራዋ ለዘለዓለም በትከሻው ላይ ተሸክሞ እንዲኖር የተፈረደበት የራሳቸው የአማልእክቱ ዘመድ ነው ይባላል። ይህንን አፈ ታሪክ በተመለከተ ከአሁን ቀደም በአንድ ጽሑፌ ዘርዘር አድርጌ ታሪኩን ማስታወሴ አይዘነጋም።

ሀገሬ የዘመናት መከራዋ እየተቀረፈ በአዳዲስ የተስፋ ሙላቶች ቀና ማለት የጀመረችበት ወቅት እንደሆነ ብዙዎችን ያስማማል። ይህንን እውነታ የሚክዱት ቁጥርም ቀላል ስላይደለ ከእነርሱ ጋር እንካ ሰላንትያ መግጠሙ እጅግም አስፈላጊ ስላልሆነ ጉዳዩን የክርክር አጀንዳ አናደርገውም። ተስፋን የሚገድለው አንዱ ምክንያት የማይረባ እሰጥ አገባ ውስጥ ተዘፍቆ መቆራቆስ እንደሆነ ከማናችንም የተሰወረ አይደለም።

“የአፍሪካ ዋና ከተማ” እያልን ስናንቆለጳጵሳት የኖረችው አዲስ አበባችን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ስሟና መልኳ መቀራረብ ሲጀምር እያስተዋልን ነው። ስንጓጓለት የነበረው ሀገራዊ ምኞት ወደ ሙላት ደረጃ እየተቃረበ በመሄዱ የላሸቀው ተስፋችን በመነቃቃት ላይ ነው። በአጭር ጊዜያት ተገንብተው ለሕዝብ ይፋ የሆኑት “የአደባባይ ገነቶች” ቁጥር መበራከት እንኳን ለእኛ ለባእዳንም ቢሆን የስበት ኃይል እየሆኑ ነው። ይህ ጉዳይ አንዱ የተስፋችን እውነታ ማረጋገጫ ተደርጎ ቢጠቀስ አግባብም ተገቢም እንደሆነ ሊታመን ይገባል።

ከገበሬው ማሳ ከሚታፈሰው የዘንድሮ ምርት ውስጥ ተቆንጥሮ ለመጀመሪያ ጊዜ “ወደ ውጭ ኤክስፖርት እናደርጋለን” የሚለው ዜና ስንመኘው የኖርነው ተስፋ ምን ያህል ወደ እውነት እየተቃረበ እንደሆነ ጥሩ ማሳያ ነው። አንዳንዶች “ራስ ሳይጠና ጉተና” እያሉ ቢያሽሟጥጡም ትርጉሙ ከዘባቾቹ ምፀት ከፍ ያለ ስለሆነ ተስፋ ለማስቆረጥ አቅም አይኖረውም።

የህዳሴ ግድባችን ትሩፋትም የሀገራችን ታላቅ ህልምና ተስፋ እንደምን ወደ ተግባር እንደተለወጠ ጥሩ ማሳያ ሊሆን ይችላል። በወንዛችን እንዳንጠቀም ከወደረኞቻችን የሚሰነዘረው ኡኡታና የዲፕሎማሲ ጫና፣ የጉልበት ትምክህትና ማስፈራራት ትቢያ መልበሱን በሚገባ እያስተዋልን ነው። ይህስኬት በዋነኛነት የሀገራችን ተስፋ በሙላት የመገለጹ አንዱ ማስረጃ ተደርጎ ሊቆጠር ይገባል።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ “የመንግሥት ያለህ! የፍትሕ ያለህ!” እያለ ሲጮኽ የኖረበት የሌቦችና የሙሰኞች ጉዳይም ትኩረት እንዳገኘ መንግሥታዊ ማረጋገጫ ስለተሰጠበት ሲያጣጥር የባጀው ተስፋችን ወደ መነቃቃትና ማገገም ደረጃ ላይ እየደረሰ መሆኑን ማስታወሱ ክፋት የለውም። ምንም እንኳ ጅምሩ በተግባር መፈተን ቢኖርበትም።

“ካላዘሉኝ አላምንም” እንዳለችው ሙሽሪት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተነቃቃ ያለውን መልከ ብዙ ተስፋችንን የምንጠራጠር ከሆነ ግን ለማንም ስለማይበጅ ይሆናል ብለን በአሜንታ መቀበልና የየግላችንን ጠጠር በማዋጣት “ለተስፋችን ጋን” መደገፊያ ማድረጉ ይበልጥ የተሻለ አማራጭ ይሆናል። “ጋን በጠጠር ይደገፋል” - የሚለው ብሂል “የዜግነት ግዴታን እንዴት ልንወጣ እንችላለን?” ለሚለው የቅኖች ጥያቄ መልስ ሊሆን ይችላል።

ሁሉም ዜጋ በሀገራችን ላይ እየታየ ባለው የተስፋ መነቃቃት እኩል መረዳትም ሆነ እኩል እውቀት ይኖረዋል ተብሎ አይገመትም። ይኑረው ብሎ አታካራ መግጠምም ተገቢ አይሆንም። ለአንዳንዱ ዜጋ የሚታየው ድቅድቅ የተስፋ መቁረጥ ጨለማ ሊሆን ይችላል። አንዳንዱም ነፍስያው በተቃውሞ ስለተገራ በጎው ሀገራዊ ገጽታ እየታየውም ቢሆን ሽምጥጥ አድርጎ በመካድ ምንም እንዳልተሰራና እንዳልተፈጠረ ወገቡን ይዞ ሊከራከር ይችላል። መብታቸው ነው። ቶማሳዊው ጥርጣሬያቸው ውሎ አድሮ ሊገፈፍላቸው ስለሚችል በትእግሥት መመልከቱ ብስለት ብቻም ሳይሆን በጥበብ የመባረክ ምልክትም ጭምር ነው።

አንዳንዱ ከዛሬ ይልቅ የነገ ጀንበር ብሩህና ደማቅ እንደምትሆን ስለሚያምን ተስፋው የደደረ ነው። “የችግሮቻችን ጨለማ ሲበረታ የተስፋችን ከዋክብት ደምቀው ይታያሉ” የሚል የሕይወት ፍልስፍና ስላለው ነገን የሚጠብቀው በጉጉት ነው። “ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ” እንዳለችው የቤት እመቤት፤ “የጥያቄያችን ዕንቆቅልሽ ሁሉ ዛሬውኑ ካልተፈጸመ እንጦሮጦስ ይውረድ!” ባይ ድምጾች በብዛት መሰማታቸው በእና ዘንድ የተለመደ ነው። ይህን መሰሉ አመለካከትም መብት ስለሆነ “ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው” በሚል ስብከት መገዳደሩ አግባብ ላይሆን ይችላል።

በዚያም ተባለ በዚህ ኢትዮጵያ እየተራመደች ያለችው ወደ ፊት እንጂ በኋልዮሽ የእርምጃ ጉዞ አይደለም። እርግጥ ነው ሀገራዊ ችግሮቻችን ብዙ ተብለው ብቻ በወል ቋንቋ የሚገለጹ ሳይሆን በሸበሸ መሆናቸው የታወቀ ነው። የዚያንው ያህል ደግሞ ስንመኛቸው የኖረነው ተስፋዎቻችን ወደ እውነታ እየተቃረቡና የኢትዮጵያን ከፍታ እያፋጠኑ ስለሆነ እንደ ዜጎች ማመስገንና መመሰጋገን፤ ለፈጣሪም ገላታ ልናደርስ ይገባል። ሰላም ይሁን።

## ተናጋሪው ዶሴ

# የተከበረ ሙያን ለውንብድና

አስመረት ብስራት

ወጣት ነው፤ በሥራና በትጋት የሚያምን ትጉህ ወጣት። ለፍቶ ጥሮ ግሮ የማግኘት ትርጉም የገባው ወጣት ቢኒያም ሴካሞን በስራው ባፈራው ሀብት ከራሱ አልፎ ለበርካቶች የሥራ ዕድል ፈጥሯል። ለትልቅ ለትንሹ ታዛዥ እና ሥራውን አክባሪ የሆነው ወጣት ዘወትር ቀኑን የሚጀምረው በፀሎት ነው።

ቢኒያም ዛሬም እንደልማዱ ከእንቅልፉ የተነሳው በሰላም መዋልን ተመኝቶ ነው:: ፀሎቱን አድርሶ ፈጣሪውን አመስግኖ አካላዊ እንቅስቃሴ ቢያደርግም ምንም የመነቃቃት መንፈስ ሊሰማው አልቻለም። ጊዜው የእንቁጣጣሽ ኢጋማሽ የመስቀል በዓል መቃረቢያ ሳምንት መስከረም 11 ቀን 2014 ዓ.ም ነበር:: ክረምቱ እየተገፈፈ ፀሃይ መድመቅ ከጀመረች ሰነባብታለች:: የዛን ቀንም ቀኑ ደመቅ ብሎ ጀማምሯል።የመስከረም ወር የአዲስ አመት መጀመሪያ ነውና ብዙዎች በአዳዲስ እቅድና በተስፋ የሚጀምሩበት ወር ነው።

ምንም ብሩህ ቀን ቢሆንም የቢኒያም የደስታ መንፈስ ሊቀሰቅስ አልቻለም፤ ድብርት ተሰምቶታል:: ማልዶ ከቤት መውጣት አልፈለገም:: መልሶ ሊተኛ ካሰበ በኋላ በጣም እንዳይጫጫነው በመስጋት ያገኘውን መፅሄት ሲያገላብጥ ቆየ። እንደምንም ራሱን አነቃቅቶ አረፋፍዶ ቁርሱን ተመግቦ እንደልማዱ ቡናውን ጠጥቶ ዘመናዊ መኪናውን እያሽከረከረ ከቤቱ ወጣ::

### የዝርፊያ ዕቅድ

ዜጎች በሰላም ወጥተው በሰላም እንዲገቡ ህግን የማስከበር ሀላፊነት የተጣለባቸው የህግ አስከባሪዎችም በየደረጃው ሀላፊነታቸውን ለመወጣት ስምሪት ይዘው ተንቀሳቅሰዋል። ሆኖም ግን ሁሉም የፍትህ አካል ሀላፊነቱን በሚገባ ይወጣል ብሎ ማሰብ አልፎ አልፎ የማይቻልበት ሁኔታ ያጋጥማል። መስከረም 11 ቀን 2014 የሆነውም ህግ ለማስከበር የተሰማሩ አካላት በሙያቸውና ሙያው በሚጠይቀው ስነምግባር ዙሪያ አልነበሩም። የፀጥታ አስከባሪ የመሰሉት ወንጀል ለመፈጸም የተዘጋጁ የፖሊስ የደንብ ልብስ የለበሱ ናቸው ።በጋራ ሆነው በእለቱ ስለሚፈጽሙት ውንብድና መዶለት ከጀመሩ ሰነባብተዋል:: ምክትል ሳጅን አዲስ አለም አባተ ቢሻቶ ፤ ዋና ሳጅን ሚሊኪያስ አበራ ማሞ፤ ሳጅን ኤልያስ ታፈሰ እና ዳዊት በልሁ ከሌሎች ግለሰቦች ጋር በመሆን ከማን ምን እንዴት እንደሚዘርፉ ተመካከሩ። ምን ቢያደርጉ የተሳካ ዘረፋ ሊያከናውኑ እንደሚችሉ ቁጭ ብለው ዓቅደው ተዘጋጅተው ነው የመጡት ።

በተሰማሩበት የህግ ማስከበር ሂደት ውስጥ የተመለከቱትን የወንጀል ልምድ በሙሉ በመቀመር ለእነሱ የዘረፋ ሂደት ይጠቅመናል ብለው የሚያስቡትን እቅድ ከማውጣት አልፈው የስራ ድርሻ ተከፋፍለዋል። ለዝግጅታቸው ተግባራዊነት መንግስት ለደንብ ማስከበር ያገለግላቸዋል ብሎ የሰጣቸውን መሳሪያና አልባሳት ለእኩይ ሥራቸው ማስፈፀሚያ እንደሚያደርጉት ተማምነዋል።

### በመንገድ ላይ...

ሊዘረፉ ዕቅድ ከተያዘባቸው መካከል ወጣት ቢኒያም አንዱ ነው:: ቅድመ ዝግጅት አድርገው ጥርሳቸው ውስጥ አስገብተው ሲከታተሉት ከራርመዋል:: መስከረም 11 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀኑ 4፡00 ሰዓት አካባቢ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ልዩ ቦታው ኔክሰስ ሆቴል ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ በአሳቻ መንገድ ላይ እየጠበቁት መዘግየቱ አሳስቧቸው ተስፋ ለመቁረጥ በማመንታት ላይ እያሉ፤ የቢኒያም መኪናን ከሩቅ ተመለከቱ::

ቢኒያም ከቤቱ ሲወጣ የኮረኮንች መንገዱን እየገሰገሰ አለፈው:: ጉዞውን በቀጥታ ወደ ኔክሰስ ሆቴል መንገድ አደረገ:: ብዙም ሳይርቅ ደብል ጋቢና ፒካፕ የፖሊስ መኪና በተጨማሪ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-47692 ኦ.ሮ ዶሊፊን መኪና የቢኒያምን መኪና መከተል ጀመሩ::



ፍጥነቱን ቀንሶ መንዳቱን ቀጠለ:: እየተጠጉት መሆኑን ሲያውቅ ግራ ተጋብቶ በቀስታ መኪናውን ጥግ አሲይዞ አቆመ። የሚከተሉት መኪናዎች ትተውት አልሔዱም ጭራሽ ከፊትና ከጎን መንገድ ዘግተውበት ቆሙ:: ነገር ግን መኪኖቹን ሲመለከት የፖሊስ መኪና መሆናቸው ብቻ ሳይሆን መኪናዎቹ ውስጥ ያሉት ሰዎችም የደንብ ልብስ የለበሱ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ተስፋ አደረገ:: ብዙም ስጋት እንዳይሰማው ለማድረግ ለመረጋጋት ቢሞክርም፤ ከመኪናው ውስጥ የሚወርዱት ሰዎች አኳኋን ግን ግራ የሚያጋባ ሆነበት።

የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ኔክሰስ ሆቴል አካባቢ ተገኝተው ትርዒቱን ሲያዩ የነበሩ ሰዎች፤ የፖሊስ ዳብል ጋቢና ፒካፕ መኪናን በማየታቸው ቢኒያም ወንጀለኛ ሆኖ እየተያዘ መሆኑን አልተጠራጠሩም:: ቢኒያም በበኩሉ ጥርጣሬና ስጋት እየተከታተሉ ቢፈታተኑትም ራሱን ተቆጣጥሮ ከተሽከርካሪው ሳይወጣ ባለበት የሚሆነውን መከታተል ጀመረ::

የፖሊስ ዳብል ጋቢና ፒካፕ መኪና እያሽከረከረ ቢኒያምን ሲከተል የነበረው ዋና ሳጅን ሚሊኪያስ ምክትል ሳጅን አዲስ አለም ፣ ሳጅን ኤልያስ ታፈሰ፤ እና ሌሎች ወንጀል ፈጻሚዎች ጋር አብረው በመኪናው የመጡት በሙሉ ከመኪና ወረዱ:: የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3-47692 ኦ.ሮ የሆነ ዶልፊን መኪና እያሽከረከረ የነበረው፤ ዳዊት በልሁም እንደሌሎቹ ከመኪናው ወርዶ ወደ ቢኒያም መኪና ተጠጋ:: መኪናቸውን ከቢኒያም መኪና አጠገብ አቁመው ምክትል ሳጅን አዲስ አለም የፖሊስ የደንብ ልብስ ለብሶ መጥሪያ የሚመስል ወረቀት እያሳየ ሽጉጥ ወደ ቢኒያም ግንባር ደቀነ:: ሳጅን ኤልያስ ታፈሰ ደግሞ፤ ለቢኒያም ‹‹ከመኪናው ውረድ አንተ ሀገር አፍራሽ ጁንታ›› በማለት ከመኪናው አስወረደው።

በካቴና ሁለት እጁን በማሰር በፖሊስ መኪና አስገቡት:: ‹‹የመኪናዬ በር ስላልተዘጋ ልዝጋው ፍቀዱልኝ›› አላቸው:: ‹‹እንደውም ውረድ›› በማለት፤ እጁ በካቴና እንደታሰረ በራሱ መኪና ከኋላ ወንበር በማስገባት ሌላኛው ወንጀል ፈጻሚ የቢኒያምን መኪና እያሽከረከረ ምክትል ሳጅን አዲስ አለም በቢኒያም ግንባር ላይ ሽጉጥ በመደቀን ‹‹እንቀሳቀሳለሁ ብትል እገልሃለው፣ የምጠይቅህን ብቻ መልስ :: ›› በማለት፤ መኪናውን እና እርሱን ፈትሸው የዋጋ ግምታቸው 70 ሺህ ብር የሚገመት ሁለት ዘመናዊ ሳምሰንግ ስልኮች ፣ ከተለያዩ ባንኮች ተፅፎ የተፈረመባቸው የ200,000 ብር እና የ350,000 ቼኮች፣ የመኪና ቁልፍ እና የተለያዩ ሰነዶችን ወሰዱ::

በቢኒያም ጭን ላይ ሽጉጥ በመደቀን ‹‹ብልትህን ነው የማወጣልህ›› በማለት እያስፈራሩ ወደ ጉርድ ሾላ አቅጣጫ መኪናውን እየነዱ ወሰዱት:: እየወሰዱት እያለ ፤ ‹‹ዝቅ በል ካቴናውን ሰው እንዳያየው›› በማለት መኪናውን ወደ ሰዓሊተ ምህረት አቅጣጫ ሲያሽከረክሩ ስራ አመራር አካባቢ ማርያም ባቡር መሻገሪያ ተብሎ ከሚጠራው ስፍራ፤ ትራፊክ መንገዱን በማጨናነቁ ምክንያት መኪናው ፍጥነቱን ቀነሰ:: ቢኒያም እጁን በካቴና እንደታሰረ የመኪናውን መስኮት በመክፈት እጁን እና አንገቱን ወደ ውጭ በማውጣት የድረሱልኝ ጥሪ አሰማ:: ጩኸቱን አቀለጠው::

የአካባቢው ህብረተስብ ሲሰበሰብ በመስኮት ዘሎ በመውጣት ‹‹ሌቦች ናቸው አፍነውኝ ነው አስጥሉኝ›› ሲል ወንጀል ፈፃሚው፤ ከመኪናው በመውረድ ‹‹በወንጀል ተፈላጊ ነው›› በማለት ይዞ መልሶ ወደ መኪናው ውስጥ ሊያስገባው ሲሞክር በአካባቢው የነበሩ ፖሊሶችና ሌሎች ሰዎች የደንብ ልብስ የለበሰውን ወንጀለኛ ተባብረው ያዙት::

የፖሊስ ምርመራ

የህግ አስከባሪነት ሀላፊነትን ተቀብለው ለረዥም አመታት ሲያገለግሉ የቆዩት እነዚሁ ግለሰቦች የተሰጣቸውን ሀላፊት ያለአግባብ በመጠቀም ህዝቡን ማሸበር ዋነኛ ተግበራቸው ካደረጉት መቆየታቸው በፖሊስ ምርመራ ተረጋገጠ። በዚህ ተግባራቸው የመዲናዋን ሰላማዊ ሰዎች ሀብት ንብረት ከመቀማት አልፎ በማስፈራራት የስነ ልቦና እና የአካል ጉዳት ማድረሳቸውም ታወቀ።

የፖሊስ ምርመራው እንደሚያሳየው በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የውንብድና ተግባር ሲፈፅሙ ከለላ ያደረጉት ህዝብ የጣለባቸውን ሀላፊነት ነበር። ለስራቸው ቅልጥፍና ሲባል የተሰጣቸውን የደንብ ልብስ ከስራ ውጪ በመጠቀም በህግ ማስከበር ሰበብ ሰዎችን ሲያስፈራሩና፤ ለወንጀላቸው መሸፈኛ ይሆን ዘንድ የፖሊስ ማዘዣ ወረቀትን በማስመሰል ያለአግባብ ሰዎችን ሲያንገላቱ ቆይተዋል።

ዳዊት በልሁ ፣ ሳጅን ኤልያስ ታፈሰ፤ ሌላው ወንጀል አድራጊ በዶልፊን መኪናው ካመለጡት መካከል አንዱ ክትትል ሲደረግባቸው በሽጉጥ ሌላ ተበዳይንም እያስፈራሩ ጥርሱን በቦክስ በመምታት ጥርሱ እንዲደማ በማድረግ ይዘውት በመጡት የፖሊስ መኪና የኋላ ወንበር ካስገቡት በኋላ የዋጋ ግምቱ 11,000 ብር የሆነ ሞባይል 5,000 ጥሬ ገንዘብ ፣ መንጃ ፍቃድ እና የባንክ ደብተር ከኪሱ አውጥተው መውሰዳቸው ታወቀ::

ሌላውን እንደቢኒያም ዓይነቱን ተበዳይን ይዘው በላምበረት ወደ ሲቪል ሰርቪስ አቅጣጫ ከወሰዱት በኋላ ሲቪል ሰርቪስ ሲደርሱ ያልተያዘው ግብረ አበራቸው አንገቱን ይዞ ከመኪናው በማስወረድ ጥለውት መሄዳቸው ተረጋገጠ።

ምርመራውን መሰረት በማድረግ ምክትል ሳጅን አዲስ አለም ህጋዊ ፍቃድ ሳይኖረው የጦር መሳሪያ ይዞ የተገኘ እና ሰዎችን ለማስፈራራት የተጠቀመ በመሆኑ በፈፀመው ከባድ የውንብድና እና ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት ወንጀል ተከሰሰ:: እርሱ ብቻ አይደለም፤ ወንጀል ፈፃሚዎቹ ጓደኛሞች ከባድ የውንብድና ወንጀል እንዲሁም ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት ወንጀልን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ በመተላለፋቸው በፍትህ ሚኒስቴር ቦሌ ቅርጫፍ ጽህፈት ቤት ዐቃቤ ህግ ክስ ተመሰረተባቸው::

## ውሳኔ

ተከሳሾች በችሎት ቀርበው ክሱ ደርሷቸው ከተነበበላቸው በኋላ የእምነት ክህደት ቃላቸውን ተጠየቁ:: 4ቱም ተከሳሾች ‹‹ድርጊቱን አልፈፀምንም ጥፋተኛም አይደለንም›› ሲሉ ቃላቻውን ሰጡ።

ዐቃቤ ህግ በበኩሉ የተከሳሾችን ጥፋተኝነት የሚያስረዱ ምስክሮች፣ የሰነድ፣ ገላጭ እና የኤግዚቢት ማስረጃዎችን በበቂ ሁኔታ ለችሎቱ አስረዳ:: ፍርድ ቤቱ ተከሳሾችን እንዲከላከሉ ብይን ቢሰጥም፤ በዐቃቤ ህግ የቀረበባቸውን ክስ እና ማስረጃ ማስተባበል ባለመቻላቸው የግራ ቀኙን ክርክር ያዳመጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ 4ኛ ወንጀል ችሎት ተከሳሾች በተከሰሱባቸው ክሶች የጥፋተኝነት ፍርድ አስተላለፈባቸው።

በዚህም መሰረት ተከሳሾች ከዚህ በፊት የጥፋተኝነት ሪከርድ የሌለባቸው፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ የቅጣት ማቅለያዎች ተይዘውላቸው 1ኛ ተከሳሽ ምክትል ሳጅን አዲስ አለም አባተ ቢሻቶ የ12 ዓመት ከ3 ወር ፅኑ እስራት እና 2,000 ብር ተፈረደበት:: ሁለተኛ ተከሳሽ ዋና ሳጅን ሚሊኪያስ አበራ ማሞ ፤ ሶስተኛ ተከሳሽ ሳጅን ኤልያስ ታፈሰ የ12 ዓመት ፅኑ እስራት ተፈረደባቸው:: የመጨረሻውና 4ኛ ተከሳሽ ዳዊት በልሁ በ9 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኖበታል።

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የንባብ ባሕልን ከማዳበር የንባብ ፍቅር ይቅደም

**ደበበ ከሳ**

ኢትዮጵያውያን ጀግንነታችንን፣ አትንኩኝ ባይነታችንና ለነጻነት የምንሰጠው የላቀ ዋጋና ይህንኑም ለማረጋገጥ የከፈልነውን ውድ መስዋዕትነት ዓለም ሁሉ የሚያደንቀው መልካም ዕሴታችን ነው። አሁን አሁን እየተሸረሸረ መጣ እንጂ ሃቀኝነታችን፣ እንግዳ ተቀባይነታችንና በአብሮነት ላይ የተመሰረተ ማህበራዊ ኑሯችን በዓለም ላይ የሚያስከብሩንና የሚያኮሩን ውድ ባህሎቻችን ናቸው። በአንጻሩ እኛ ኢትዮጵያውያን በተደጋጋሚ ከምንተችባቸውና ከምንታማባቸው ነገሮች መካከል ደካማ የንባብ ባህላችን ቀዳሚውን ድርሻ ይወስዳል።

ሃሜት ብቻም ሳይሆን ከሁለት ዓመት በፊት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረገ አንድ ጥናት የንባብ ባህላችንን በእጅጉ ደካማ መሆኑን አመላክቷል። ዋና ከተሞቻቸውን እንደማሳያ በመውሰድ የዓለም አገራትን የንባብ ባህል የገመገመው ጥናት እንደ ጃፓንና ጀርመን የመሳሰሉትን አገራት በማንበብ ባህላቸው ከፍተኛ ደረጃ መድረሳቸውን የጠቆመ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ያለው የንባብ ባህል ግን በጣም በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሷል። የዓለም አገራት ዋና ዋና ከተሞችን የንባብ ባህል "ከፍተኛ"፣ "መካከለኛ" እና "ዝቅተኛ" በሚል በሦስት ምድብ ውስጥ በቅደም ተከተል ስማቸውን ያስቀመጠው ጥናቱ የእኛዋን አዲስ አበባ ግን ዝቅተኛም ቢሆን ከነጭራሹ ደረጃ ውስጥ ሳያስገባት "የማታነብ ከተማ" በማለት ተሳልቆባት አልፏል።

የንባብ ባህላችንን በሚመለከት የተሠራው ጥናት ውጤቱ ቢመረንም ሃቁ ግን ይኸው ነው። የማያነብ ሕዝብ ደግሞ የብልጽግና ትንሳኤው ሩቅ ነውና ጉዳዩ አሳሳቢ በመሆኑ የንባብ ባህላችን ለማሻሻል እንደዜጋ እያንዳንዳችን የበኩላችን መወጣት ይጠበቅብናል። የዛሬው ትዝብቴ በዚሁ ዙሪያ የሚያጠነጥን ይሆናል። በነገራችን ላይ የንባብ ባህል ዝም ብሎ የሚመጣ ነገር አይደለም። ጀርመናውያን በአንድ ወቅት "በመጻዳጃ ቤቶቻችን የምናነበው ነገር ይቀመጥልን" በማለት ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተው መንግሥታቸውን መጠየቃቸውን ታሪክ ይነግረናል።

እናም ታሪክ ጥራዝ ነጠቆች እንደሚሉት ፋይዳ የሌለው ባዶ ተረት ተረት አይደለምና፤ ሰዎች በተግባር አድርገው ለትውልድ ያስተላለፉት ሰርቶ ማሳያ ቅርስ ነውና እኛም ከዚህ ታሪክ የምንማረው ትልቅ ቁም ነገር አለ። ይህም ጀርመናውያኑ እንዲህ ዓይነቱን ድንቅ የንባብ ባህል እንዴት አዳበሩት?፣ እኛስ የንባብ ባህላችንን ለማሻሻልና እነርሱ የደረሱበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ምን ማድረግ አለብን? የሚለውን እንድናጤን ዕድል የሚፈጥር ነው።

ከዚህ ታሪክ የምንረዳው ትልቅ ቁም ነገር ጀርመናውያኑ መጻዳጃ ቤት ውስጥም ሆነው ማንበብ ይፈልጋሉ ማለት እጅግ የሚደነቅ ከፍተኛ የሆነ የንባብ ባህል አላቸው ማለት ነው። ለመሆኑ ጀርመናውያኑን መጻዳጃ ቤት ውስጥ ሳይቀር እንዲያነቡ ያነሳሳቸው ምክንያት ምንድነው? እንዲህ ዓይነቱን አንባቢነትስ "የንባብ ባህል" የሚለው ብቻ ይገልጸዋልን? ደካማውን የንባብ ባህላችንን ለማሻሻል እነዚህን መሠረታዊ ጥያቄዎች መመርመርና መመለስ ይገባል። ምክንያቱም የንባብ ባህላችን ለማሻሻል ትልቁ ምስጢር ያለው በእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ ነውና።

አዎ፣ የዳበረ የንባብ ባህልን ለመፍጠር በቅድሚያ "የንባብ ፍቅር" ሊኖረን ይገባል። አንባቢ ትውልድ ለመፍጠር፤ እንደ አገር የዳበረ የንባብ ባህል ባለቤት ለመሆን መፍትሄውም ይኸው ነው-መጽሐፍትን ማፍቀር፣ ንባብን ማፍቀር! ምክንያቱም አንድን ነገር ሳንፈልገው ወይንም ሳንወደው እንዴት እንዲኖረን እናደርገዋለን? በምንፈልገው ነገር ላይ ጥሩ ችሎታ እንዲኖረን ከፈለግን ደግሞ ከሁሉም በፊት ለዚያ ነገር ፍቅር ሊኖረን ይገባል። ከላይ የተገለጸው የጀርመናውያኑ ታሪክም የሚያሳየን ይህንኑ ነው። እነሱ አይደለምና በመደበኛው ጊዜያቸው በዚያች የደቂቃ የመጸዳጃ ቤት ቆይታቸውም የሚነበብ ነገር ማጣት አይፈልጉም።

ለምን ቢሉ ንባብን ያፈቅሯታልና! ከማንበብ ፍቅር ይዟቸዋልና! ይህም የንባብ ፍቅራቸው በከፍተኛ ደረጃ የዳበረና የበለጸገ የንባብ ባህልን ፈጠረላቸው። የእኛም አገር ችግር የንባብ ባህል አለማደግ ሳይሆን የንባብ ፍቅር አለማደግ ይመስለኛል። ለመሆኑ ማንበብ እንወዳለን? ስንቶቻችን ነን ለመደበኛ ትምህርት ወይም የሆነ አስገዳጅ ነገር ተፈጥሮብን ካልሆነ በስተቀር ለንባብ ፍላጎት ኖሮን፣ ፍቅሩ ኖሮን የምናነበው? ማንበብን የምናስበውስ እንዴት ነው? እንደአንድ አስጨናቂ ሥራ ወይስ እንደ አዝናኝ የአዕምሮ ምግብ? መልሱን ለእያንዳንዳችን ልተወው።

ከዚሁ ከንባብ ፍቅር ጋር በተያያዘ አንድ ወዳጄ ያወራኝን ቀልድ የምትመስል ዕውነት ነግሬያችሁ ወደ ቀጣዩ ሃሳቤ ልለፍ። "ልጆች ያስቀመጥከውን ብር እያነሱ ካስቸገሩህ መጽሐፍ ውስጥ ደብቀው፣ ሌባ ይወስድብኛል የሚል ስጋት ካለህም ይህ ዘዴ ግሩም መፍትሄ ይሆንልሃል"። አይገርምም? በእኛ አገር መጽሐፍት የሚፈለጉና የሚፈቀሩ ሳይሆኑ የሚያስፈሩና የሚያስጠሉ ናቸው ማለት ነው? ታዲያ እውነት መጽሐፍትን እየፈራናቸውና እየጠላናቸው፤ እንዲህ እየሰለቸናቸው ከሆነ እንዴት ነው የንባብ ባህላችን የሚያድገው?

ይሁን እንጂ በተለያዩ መስኮች የዓለማችንን ስልጣኔ ከፊት ሆነው በፊታውራሪነት የመሩ ሁሉም ታላላቅ ተፅዕኖ ፈጣሪ ስብዕናዎች ለንባብና ለመጻሕፍት ልዩ ፍቅር ያላቸው ናቸው። በአንድ ወቅት መላ አውሮፓን ጠቅልሎ ከገዛው ታላቁ ንጉስ ናፖሊዮን ቦናፖርቲ፣ ከአንድ ሺ በላይ ፈጠራዎችን እስካበረከተው ቁንጮ ሳይንቲስት ቶማስ ኤዲሰን፤ ከባለቅኔው ሸክስፔር እስከ ፈላስፋው ሶረን ኪርክጋርድ ሁሉም ስለመጻሕፍት ያልተቀኘ የለም።

"የታላቅ አገር መሠረቱ የሕዝብ አንድነት ነው" በሚል ፍልስፍናቸው የሚታወቁትና በግለኝነት አስተሳሰብ በዘቀጡ ዘመነ መሳፍንታውያን ተከፋፍላ የተዳከመችውን ኢትዮጵያን ሕይወታቸውን ጭምር በመክፈል ወደ ቀድሞ አንድነቷ የመለሷት፤ ለታላቅነቷ ታላቅ ራዕይን ይዘው ሕይወታቸውን እስከ መስጠት ድረስ የታገሉላት፣ የጀግንነትና የታላቅ ስብዕና ምልክት የሆኑት ኢትዮጵያዊው ንጉሠ ነገሥት አፄ ቴዎድሮስም ለመጽሐፍ ልዩ ፍቅር ነበራቸው። በዚህም ንጉሡ በሕይወት ዘመናቸው ልዩ ልዩ ዕውቀትና ጥበብ የያዙ እስከ አንድ ሺ የሚደርሱ መጽሐፍትን በመቅደላ ጊዜያዊ ቤተ መንግሥታቸው ሰብስበው እንደነበር የአገር ውስጥና የውጭ የታሪክ ምሁራን ጽፈዋል።

እናም ብሒላችን እንደሚለው "ከመጠምጠም ማወቅ ይቅደም"። የንባብ ባህላችን እንዲዳብር ከፈለግን በቅድሚያ ለመጻሕፍት ያለን ፍቅር እናሳድግ። የንባብ ባህላችን እንዲዳብር መጻሕፍትን እንደእናትና አባቶቻችን፣ እንደምንወዳቸው ፍቅረኞቻችንና የትዳር አጋሮቻችን፣ እንደምንሳሳላቸው ልጆቻችን ከልባችን ልንወዳቸውና ልናፈቅራቸው ይገባናል።

ውሃን ከጥሩ ቢጠጡት፣ ነገርን ከሥሩ ቢሰሙት መልካም ነውና፤ ስለንባብ ፍቅር የዓላማችን ታላላቅ ሰዎች በተናገሩትና በተግባር በኖሩበት አባባሎቻቸው የዛሬውን ትዝብቴን ላጠቃልል።

"ሁልጊዜም ትንሿን ልጄ ስለማስደሰቴ ሐሴት ይሰማኛል-እርሷ መጽሐፍትን የመውደዷን ያህል ደግሞ የሚያስደስተኝ ምንም ነገር የለም። ምክንያቱም እንደ እኔ እድሜዋ ሲገፋ መጽሐፍት ከየትኛውም ኬክ፣ አሻንጉሊትና ከማንኛውም ጨዋታና ትዕይንት ሁሉ የተሻሉ መሆናቸውን ትገነዘባለች።

ማንም እስከ ዛሬ ከኖሩት ነገስታት ሁሉ ታላቁ እንዲሁም ባለ ቤተ መንግሥትና ባለ አትክልት ሥፍራ ቢያደርገኝ፣ የተመረጠ የእራት ግብዣ ከወይን መጠጥ ጋር የሚቀርብልኝ ንጉሥ ሊያደርገኝ ቢፈልግ እንኳ መጽሐፍትን የማነብበት ዕድል ከሌለኝ ንጉሥ መሆንን ነፍሴ አትቀበለውም። ማንበብን የማያፈቅር ንጉሥ ከመሆን ከበርካታ መጽሐፍቴ ጋር በአንዲት ትንሽ ክፍል ብታጎር እመርጣለሁ።"

- ሎርድ ማክዋሌ፣ ብሪታኒያዊ ታሪክ ጸሐፊ፣ ሃያሲና ፖለቲከኛ

"የመጽሐፍት ፍቅር በየዕለቱና በየሰዓቱ ገደብ የለሽ የሆነ በማንም ጥገኛ ያልሆነ አግባብነት ያለውን የፍስሐ ምንጭ ይከፍትልናል። እናም ከቀኑ የተወሰኑ ሰዓቶቹን በክፍሉ ውስጥ ሆኖ በመጽሐፍት ውስጥ ከሚኖሩ ከበሬታን የሚያላብሱ ታላላቅ ሰዎች ጋር ከማያሳልፍ ሰው ምንም ዓይነት ሰብዓዊ ዋጋ ያለውን አንዳች ነገር ተስፋ ማድረግ አያስፈልገንም።"

**- ፍሪዴሪክ ፋበር**

"የመጽሐፍት ፍቅር ብዙ ጠባብ ነፍሳትን አስፍቷል፤ ብዙ የተዘጉ፣ የተገደቡ፣ መስኮት አልባ ልቦችን በተራራማ አየርና የፀሐይ ብርሃን ሞልቷል፤ ለመለኮትም ሆነ ለስብዕና አስቀድሞ ክፍል ያልነበራቸው ቤቶችን አስለቅቆላቸዋል።"

**- ሪቻርድ ዲ በሪ**

# ዓለም አቀፍ

## በትዊተር የታገዱ አካውንቶች ሲመለሱ ነው



ኤሎን መስክ ከዚህ ቀደም በትዊተር የታገዱ አካውንቶችን ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ ሊመልስ ነው። የትዊተር አዲሱ ባለቤት ኤሎን መስክ እንዳለው «ምህረት» አደርጋለሁ ብሏል። ኤሎን መስክ በያዝነው ሳምንት ረቡዕ ለትዊተር ተጠቃሚዎች «ሕግን ያልጣሱ ወይም በአስደንጋጭ ሁኔታ ያጭበረበሩ» አካውንቶችን ባላካተተ መልኩ ሌሎች የታገዱ አካውንቶች እንዲመለሱ የሚጠይቅ የሕዝብ አስተያየትንም ሰብስቧል።

ከዚህም ጋር ተያይዞ በርካታ አካውንቶች እገዳቸው የተነሳላቸው ሲሆን ከነዚህም መካከል የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ይገኙበታል። የዓለማችን ባለጸጋው መስክ ትዊተርን በ44 ቢሊዮን ዶላር የገዛው ባለፈው ወር ነበር። ከ3 ነጥብ 1 ሚሊዮን በላይ የትዊተር ተጠቃሚዎች ለመስክ ድምጽ ስጡ ምላሽ የሰጡ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 72.4 በመቶ የሚሆኑት እገዳው እንዲነሳ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። «ሕዝቡ ፈርዷል። ምህረት ማድረግ በሚቀጥለው ሳምንት ይጀምራል» በማለት በትዊተር 118.7 ሚሊዮን ተከታዮች ያሉት ኤሎን መስክ በትዊተር ገጹ አስፍሯል።

መስክ በተጨማሪም «የሕዝብ ድምጽ የአምላክ ድምጽ ነው» የሚለውን የላቲን ሐረግም ተጠቅሟል። ኤሎን መስክ የይቅርታው ሂደት እንዴት ተፈጻሚ እንደሚሆን ዝርዝር መረጃ አልሰጠም። ባለፈው ሳምንት ቅዳሜ የትዊተር ተጠቃሚዎች ይሁንታን አግኝቻለሁ በማለት የዶናልድ ትራምፕን እገዳ አንስቷል።

ነገር ግን የቀድሞው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ከዚህ ቀደም ወደ ማህበራዊ ሚዲያው ለመመለስ «ምንም ምክንያት አይታየኝም» ማለታቸው ወደ ትዊተር ላይመለሱ ይችላል የሚለው ጠቋሚ ነው ተብሏል። የቀድሞው ፕሬዚዳንት የትዊተር ገጻቸው የታገደው ባለፈው ዓመት ሲሆን ይህም ግጭትን እና ሁከትን በማነሳሳት በሚል ነበር።

የዶናልድ ትራምፕ ደጋፊዎች በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘውን ካፒቶል ሂል ጥሰው ከገቡ ከቀናት በኋላ የትዊተር የቀድሞ አስተዳደር እርምጃ ወስዷል። መስክ ከትራምፕ በተጨማሪ የራፐር ዬ (የቀድሞው ካንዬ ዌስትና የተፅእኖ ፈጣሪውን አንድሪው ታቴ) የትዊተር አካውንታቸው እንዲመለስ አድርጓል።

ሆኖም ባለጸጋው ኤሎን የሴራ ጽንሰ ሃሳብ ተንታኙ አሌክስ ጆንስ ወደ ትዊተር እንዲመለስ አይፈቀድለትም ብሏል። የኢንፎዋርስ የተሰኘው ፕሮግራም አዘጋጅ የሆነው ጆንስ በአውሮፓውያኑ 2012 ሳንዲሁክ ትምህርት ቤት 20 ሕፃናትንና ስድስት ጎልማሶችን የቀጠፈው ጥቃት ውሸት ነው በማለቱም 1.44 ቢሊዮን ዶላር ካሳ ለመክፈል ተገድዷል። መስክ እንዳለው «የልጆችን ሞት ለጥቅም፣ ለፖለቲካ ወይም ለዝና ለሚጠቀም» ለማንኛውም ሰው «ምንም ዓይነት ምህረት እንደሌለው» በጽሑፍ ማስፈሩን ቢቢሲ ዘግቧል።



## በሱዳን ዳርፉር ግዛት ዳግም ግጭት ማገርሸቱ ተገለጸ

በማዕከላዊ ዳርፉር በተፈጠረው ግጭት 13 ሰዎች ሲሞቱ በርካቶች ደግሞ መቁሰላቸው ተገልጿል። በጎረቤት አገር ሱዳን ዳርፉር ግዛት በተፈጠረ ግጭት ምክንያት የ13 ሰዎች ሕይወት ሲያልፍ ስድስት ሰዎች ተጠልፈው ያሉበት የማይታወቅ ሲሆን አራት ሰዎች ደግሞ መቁሰላቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

እንዲሁም 12 ሰዎች ደግሞ እስካሁን በግጭቱ ይሙቱ ወይም በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ እንደማይታወቅ የተገለጸ ሲሆን፣ ግጭቱ ሊቀጥል እንደሚችልም ተሰግቷል። የምዕራብ ሱዳን አካል የሆነው ዳርፉር ግዛት በተደጋጋሚ ግጭት የሚከሰትበት ሲሆን ከሦስት ቀናት በፊት በማዕከላዊ ዳርፉር ልዩ ቦታው ኡሙ እና አርሽን በሚባሉ ቦታዎች አዲስ ግጭት መፈጠሩ ተገልጿል።

ተመድ በሪፖርቱ እንዳሳወቀው፣ ግጭቱ የተቀሰቀሰው በሱዳን ነፃ አውጪ አማጺ ቡድን እና ከዚህ ቡድን ተከፍለው በወጡ አባላት መካከል ነው። ግጭቱ በመስፋፋት ላይ እንደሆነ የገለጸው ተመድ በተለይም ዳያ፣ ዋራ እና ኪያ በተባሉ መንደሮች ተስፋፍቷል የተባለ ሲሆን፣ በዚህ ግጭት ምክንያት እስካሁን ከ5 ሺህ 600 በላይ ነዋሪዎች ከቀያቸው መፈናቀላቸውንም ገልጿል።

ተፋላሚ ወገኖች ዳግም ለመዋጋት ኃይል እያሰባሰቡ መሆኑን መረጃ እንዳለው የሚገልጸው ይኸው ተቋም ግጭቱ እንዲቆም እና የሚመለከታቸው ሁሉ ጫና እንዲያደርጉም አሳስቧል። ባሳለፍነው ጥቅምት ወር ላይ ተመሳሳይ ግጭት ተከስቶ 13 ሰዎች ሲሞቱ 15 ሰዎች ደግሞ ቆስለው እንደነበር በዘገባው ላይ ተጠቅሷል።

የሱዳን ነፃ አውጪ አማጺ ቡድን ወይም በምህጻረ ቃሉ "ኑር" በመባል የሚጠራ ሲሆን በፈረንጆቹ 2020 በደቡብ ሱዳን መዲና ጁባ የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ካልፈረሙ አማጺ ቡድኖች መካከል አንዱ ነው ተብሏል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በዚህ አማጺ ቡድን አባላት መካከል መከፋፈል የተከሰተ ሲሆን፣ ይህ መከፋፈል ወደ ማህበረሰቡ ወርዶ ለንጹሃን መሞት ምክንያት እንደሆነም አል ዐይን ዘገባ አስታውሷል።

# መጋቢ አዕምሮ

## ‘የአድማጭ ያለህ’ የሚሉ ድምጾች



**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

በቤተሰቡ ላይ የወደቀው ዝምታ አስፈሪ ነው። ድንጋጤው ከቤተሰብም አልፎ ጎረቤት ደርሷል። ወዳጅ ዘመድም በሰማው ነገር እየተከዘ ነው። «እውን ወይንስ ቅዠት» የሚለው የሁሉም ጥያቄ ነው። ያልተፈታ እንቆቅልሽ ሆኖ በሁሉም አእምሮ ውስጥ ይመላለሳል። ለማስተዛዘን የማይመችም ጉዳይ ሆኗል። አስደንጋጭ አሟሟት። በቁም ያሉትን አንገት ያስደፋ።

በዝምታ፣ ጨዋ በሚል መጠሪያ ወይም በቤት ልጅነት መድብ ውስጥ ብትመደብ ተቃውሞ የማይቀርብባት ወጣት። አንድ ቀን ራሷን ለማጥፋት ወስና አድርጋው ተገኘች። ታላቅ ድንጋጤ። በቤተሰቡ ውስጥ የሆነው ምን እንደሆነ ግልጽ የሚሆንለት ሰው እንዲጠፋ ያደረገ ክስተት። በለቅሶ ቀናት ውስጥ ኀዘን ከቤተሰቡ ሊወጣ አልቻለም። «እንዴት ሆነ?» የሚለውን ጥያቄ ሊመልስ አቅም ያለው ሰው አልነበረም። ግን ሆነ!

ለማጽናናት የሚመጣ ሰው ተመሳሳይ ታሪኮችን እያነሳ ማውራቱ የተለመደ ነውና መሰል ታሪኮች ከየአቅጣጫው ተሰሙ። ተመሳሳይ ታሪክ መብዛቱ ለቤተሰቡ ግን ጉዳዩ እንቆቅልሽ ሆኖ ከመቆየት ሊያስቀር አልቻለም። ፖሊስ ፍንጭ ለማግኘት ያደረገው ጥረት ከብጣሽ ወረቀት ያለፈ ሊሆን አልቻለም። ሟች ያስቀመጠችው ማስታወሻ ልብን በሚነኩ ቃላት የተከተበ ነው። እንዲህ ይላል «የሚሰማው ያጣ ሰው ይህን አደረገ። ኃላፊነቱ በራሴ ነው። በአጠገባችን ያለውን ሰው እንወቀው ደግሞም እናድምጠው። » ይላል። ፖሊስ እያንዳንዱን ቃል እየመነዘረ አንዳች የወንጀል መስመር ይገኝ እንደሆን ሞከረ። ብጫቂ ማስታወሻው ከአንድ የወንጀል ክስተት ይልቅ የሕይወት መስመር ግራ መጋባት ሊሆን እንደሚችል ወደ መደምደሙ ነው። የበዛው የቤት ሥራን ለቤተሰብ የተወ።

በሥራ በብዙ ተጠምደው ለቤተሰብ ሁሉ እንዲሞላ የሚተጉ እናትና አባት ራሳቸውን እየወቀሱ የሞትን መንገድ ለራሳቸው ተመኙ። እንዴት ይህ ሆነ? እንዴት? አሁንም እንዴት? የሚለው ጥያቄ ቀጥሏል።

መሰል ታሪኮችን ካለንበት ቤት በተወሰነ ርቀት ላይ ሊገጥመን እንደሚችል ጸሐፊው ያምናል። በዙሪያችን ድምጻቸው ሊሰማ የሚገባ ነገር ግን ያልተሰሙ ሰዎች አሉ። ድምጻቸውን ሊያሰሙ ፈልገው ያልተሳካላቸው ሰዎች በገባቸው መንገድ ሕይወትን ሊፈልጉ ይማስናሉ፤ የስህተት መንገድንም ጨምሮ። አብረን እንደ ቤተሰብ፣ አብረን እንደ አካባቢ፣ አብረን እንደ ማህበረሰብ አብረን እንደ አንድ አገር ሕዝቦች ወይንም እንደ ሰው እየኖርን ያልተሰሙ ድምጾች መኖራቸው ያሳዝነናል።

ዛሬ የምናነሳው ሃሳብ ያልተሰሙ ድምጾችን ስለመስማት ነው። ከዙሪያችን ተነስተን በሁሉም ኃላፊነት ባሉብን መስመሮች ሁሉ። ሌሎችን ከማድመጥ በፊት የሚቀድመውን ራስን ማድመጥን በማስቀደም።

### ራስን ማድመጥ

ያለንበት ዘመን «የመርካት አለመርካት» ተቃርኖ ዘመን ነው ልንል እንችላለን። በአንድ በኩል ሕይወትን ለማቅለል የሚረዱ እርካታን የሚፈጥሩ የብዙ ጥረቶች የሚደረጉበት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተቃራኒው የውስጥ እርካታ ጥፋት የሰዎችን ሕይወት ትርጉም አልባ ያደረገበት። ‘የሰው ልጅ ከእዚህ በኋላ እንዴት በቴክኖሎጂ ሊያድግ ይችላል?’ ተብሎ እስኪታሰብ ድረስ ቴክኖሎጂው አስደማሚ ሆኗል። በግንኙነት መስመሩ የሰው ልጅ ከዓለም አንዱ ጫፍ ከሌላኛው ጫፍ ጥርት ባለ መንገድ በቀላል ዋጋ በፍጥነት ማገናኘት ተችሏል። አንድ ዕቃ ከአንድ አቅጣጫ ወደ ሌላ አቅጣጫ ለመውሰድ ትርጉም ባለው ሁኔታ አሠራሩ የተቀየረበትም ሆኗል። እውቀት ለማግኘት እንዲሁ የሚደረገውን ጉዞ ቴክኖሎጂ ተአምር በሚባል ሁኔታ ቀይሮታል። የእነህ ነገሮች ድምር ውጤት የሰውን ልጅ አኗኗር በመሠረታዊ ደረጃ በአወንታዊ መልኩ የቀየሩት መሆኑን እንረዳለን። ነገርግን በውስጣዊ እርካታ ማጣት የሚበላሸው በዝቷል። ራስን ማድመጥ ካለመቻል የሚነሳ ህመም።

ሰው ወደ ውስጡ መመልከት እንዳይችል የሕይወት ዘይቤን ከፈጣሪ በማዞር ወደ ራስ ለማድረግ የሚደረገው ትግል ከፍተኛ ነው። የሰው ልጅ በፈጣሪ ላይ የሚያደርገውን መደገፍ እንደ ደካማነት በመቁጠር በራሱ ያለፈጣሪ ለመቆም የሚያደርገው ሙከራን አስተውለናል። ‘ተፈጥሮን በቁጥጥር ስር እናደርጋለን ’ በሚል አመለካከት ለፈጣሪ ጀርባን ለመስጠት የተሄደባቸው ዘመኖችም እሩቅ አይደሉም። የሰው ልጅ በዚህም ተባለ በእዚያ የውስጥ እርካታው ጉዳይ ሚዛን ላይ ሆኖ መፍትሄን በሚሻበት ወቅት ላይ ሆኖ ሰሚ ስላጡ ድምጾች እናስባለን።

እርካታን በገንዘብ ውስጥ፣ እርካታን በትምህርት ውስጥ፣ እርካታን በስልጣን፣ እርካታን በሌሎችም ነገሮች ውስጥ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት ወደ ውጤት እንዳላመጣን ጸሐፊው በማመን ከቁስ ባሻገር ስለሚገኝ እርካታን እያነሳን ነው። ራስን በማድመጥ ውስጥ ስለሚገኝ እርካታ፤ ድምጽ ልንሆንላቸው ስለሚገቡ ድምጽ በመሆን ከራስ ባሻገር በመሄድ ስለሚገኝ እርካታ።

### እርካታ ያጣው ቱጃር

በፕሮቴስታንት እምነት ውስጥ መንፈሳዊ መነቃቃት/ሪቫይቫል ታሪኮች ውስጥ ከሚጠቀሰው መካከል አርጀንቲና አገር የሆነው አንዱ ነው። ከአንድ ሪቫይቫል ጀርባ በልዩ ሁኔታ እግዚአብሔር የሚያስነሳቸው ሰዎች እንዳሉ ይታመናል። ከአርጀንቲናው ሪቫይቫል ጀርባ እርካታ ያጣን አንድ ሰው እናገኛለን። እርካታን ፍለጋ በብዙ ቁሳቁስ ውስጥ ራሱን ፈለገ፤ ፍለጋው በቁስ ውስጥ አለመሆኑንም አረጋገጠ። ይህ ሰው ካርሎስ አናኮንዲያ ይባላል።

አርጀንቲና ከ1982 ጀምሮ በእዚህ ሰው አገልግሎት የተነሳ በሪቫይቫል ውስጥ እንደሆነችም ትቆጠራለች። ካርሎስ አናኮንዲያ ከድሃ ቤተሰብ የተወለደ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ በንግድ አማካኝነት ባለጸጋ ለመሆን የበቃ ሰው ነው። በገንዘብ ላይ ገንዘብን እየጨመረ በሄደ ቁጥር በውስጡ ያለውን ጥያቄ መልስ እየሰጠ እንደሚሄድ ያምን ነበር። በተጨባጭ ግን ሳይሆን ቀረ። «ከገንዘብ ክምችት ባሻገር ጭፈራ ቤት ቢኖረኝ እኮ እርካታዬን አመጣዋለሁ» ብሎ በማሰብ በውድ ዋጋ የጭፈራ ቤት አስገነባ። ነገርግን አሁንም በውስጡ ላለው ጩኸት ምላሽ ሊያገኝ አልቻለም። ያልተደመጠው ጩኸት ያመጣው የፈጠረው እርካታ ማጣት። አሁንም ሌላ ሙከራ ባለቅንጦ ቤት ባለቤት መሆን። እጁ ላይ ያለው ገንዘብ ይህን ለማድረግ የሚያስችለው ነበረና በበቂ ሁኔታ ገንዘብ የፈሰሰበትን ቤትም አስገነባ። አሁንም ለውጥ የለም። በአውሮፓ ጎዳናዎች ላይ በቅንጡነታቸው የተዘመረላቸውን መኪኖቹ አምጥቼ ብነዳቸው አለ፤ እነርሱንም አስመጣና ከሀብቱ ዝርዝር ውስጥ አደረጋቸው። አሁንም አዲስ ነገር የለም።

የውስጡ ነገር እርካታ ከማጣት ወደ ፍርሃት አደገ። ሀብቴ በአንዴ ቢጠፋስ የሆነ ነገር ቢገጥመኝስ የሚለው ፍርሃት ያስጨንቀው ጀመር። የሞት ፍርሃት ወረረው። ነፍሱ አንዳች የታዳጊ ያለህ ማለት ጀመረች። በእዚህ ጊዜ ከውጭ ይልቅ ወደ ውስጥ ሲመለከት በውጫዊ ቁስ ሊሞላው ያልቻለው አካል መኖሩን ተመልክቶ ለመንፈሳዊ ሕይወት ስፍራን ሰጠ። የጀመረው ጉዞም የሪቫይቫል መነሻ ሆነ።

እርካታ ያጣው ቱጃር ውስጡን ለማድመጥ የሄደበት ርቀት ለብዙዎቻችን ትምህርት አለው። በሃይማኖቶች ውስጥ የምንማረው ትምህርት ወደ ውስጣችን መመልከት እንዳለብን የሚያስገነዝብ ነው። ወደ ውስጥ መመልከት፤ ራስን ማዳመጥ። ቁስ የማያረካው ውስጣዊ አካላችንን ፈልገን በማግኘት ማዳመጥ መቻል። ራስን ማድመጥ ተከትሎ ሌሎችን ማድመጥም ይከተላል።

### ሌሎችን ማድመጥ

«ከአሜሪካ ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎች መካከል ዘርዝር ብትባል የማንን ስም ትጠቅሳለህ? ፕሬዚዳንቶቹን ትጠቅስ ይሆን? ወይንስ ማይክል ጆርዳንን? ወይንስ ቢል ጌትስን? እኔ ግን በዝርዝርህ ውስጥ ኦፕራ ዊንሬን እንድትጨምር እጠይቅሃለሁ።» ይላሉ ጆን ማእክስዌል ናቸው። ስለ ኦፕራ ሲጽፉም «ኦፕራ በ1985 እ.አ.አ በተግባር የማትታወቅ ተራ ዜጋ ነበረች። በቺካጎ አካባቢ ስርጭት ባለው የጠዋት ሾውን በመምራት ለአንድ አመት ወደ መድረክ ስትወጣ ትኩረት መሳብ ጀመረች። የእርሷ ስኬት ጀርባ ያለው ጉዳይ የመናገር አቅሟ ጥሩ መሆኑ እንደሆነ በብዙ ሊታሰብ ይችላል፤ በእርግጥ ትክክል ነው። በልጅነት ወቅት ማለትም የሁለት አመት ልጅ እያለች በቤተክርስቲያን መድረክ ላይ ንግግር አድርጋ ምእመናኑ ጥሩ ተናጋሪ ነሽ ብለዋት እንደነበር ታስታውሳለች። ነገር ግን ከመናገር በላይም የማዳመጥ አቅሟም ትልቅ ነው። ከዘወትር ልምዷ መካከል ዋናው ለመማር ያላት ፍላጎት ነው። የጸሐፊያንን ጥበብ በንባብ ውስጥ እንደሚገኝ በማዳመጥ ውስጥ በሰዎች ውስጥ ያለውን ጥበብ ለማግኘት ትወዳለች። ሰዎች እንዴት እንደሚያስቡና እንደሚሰማቸው ለማወቅ ልብወለድ መጻሕፍትን፣ የግልታሪኮችን ወዘተ ለማወቅ ትጥራለች። የአድማጭነት አቅሟ የሥራዋን መስመር አሳድጎታል። በተግባርም በቴሌቪዥን መስኮት የምታቀርበውን ፕሮግራም ተወዳጅነት ጨምሮታል። ጉዳዮቹን ለአየር ለማብቃት በተከታታይነት ነገሮችን መመልከት እና ማድመጥ ትወዳለች። ወደ ፕሮግራሙ የምታቀርባቸውን ባለሙያዎች፣ ጸሐፊዎች፣ አርቲስቶች በትኩረትና ከውስጥ በሆነ መስማት ታደምጣቸዋለች። ኦፕራ ባላት የአድማጭነት አቅም ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎች ተርታ እንድትሰለፍ ሆናለች። እርሷ የዓለማችን ከፍተኛው የመዝናኛ ዘርፍ ተከፋይ ባለሙያዎች ተርታ ትመደባለች፤ ግማሽ ቢሊዮን ዶላር የሚገመትም ሀብት አላት። በአሜሪካ ብቻ የሳምንቱ ሰላሳ ሦስት ሚሊዮን ሕዝብ የእርሷን የቴሌቪዥን ፕሮግራም ይከታተላል። »

ሌሎችን ማድመጥን የቻለበት ሰው ለራሱም የቀናው መንገድ ላይ እንዲገኝ ያግዘዋል። «ማንን ላዳምጥ?» የሚለውን ጥያቄ በአግባቡ በመመለስ የሚጀምር ከሆነ።

### ማንን ላዳምጥ?

በተግባቦት ትምህርት ውስጥ መደማመጥ ያለውን ትልቅ ቦታ እንረዳለን። ከመናገር በፊት ማድመጥ መቻል እንደ ብልሃትም ይወሰዳል። ብዙ የሚያደምጥ ብዙ ከሚያወራም በንግግሩ ከሚመጣ አደጋም የተጠበቀ መሆኑ ግልጽ ነው።

«ማንን እናዳምጥ?» የሚለው ጥያቄ በዙሪያችን ያሉትን በአግባቡ እንድንቃኝ ዕድልን ይሰጠናል። ራሳችንን ባለብን ኃላፊነት ውስጥ ሆነን ዙሪያችንን ስንመለከት ማንን ማድመጥ እንዳለብንም እንድንወስን ያደርገናል።

ሁሉንም ሰው ማድመጥ አንችልም፤ ነገር ግን ከኃላፊነት የሚመነጭ አድማጭነት የግድ ሊደመጡ የሚገባቸውን አካላት እንድንለይ ያደርገናል። ከኃላፊነት የሚመነጭ አድማጭነት ውጤታማ አድማጭነት ነው። በትዳር ውስጥ ያለ አባት ሚስቱን እና ልጆቹን ማድመጥ መቻል የግድ ሊያደርገው የሚገባ አድማጭነት ነው። ከኃላፊነቱ የሚመነጭ አድማጭነት። ተቋም የሚመራ ግለሰብ ሠራተኞቹን፣ ደንበኞቹን፣ አቅራቢዎቹን፣ የመንግሥት አካላትን ወዘተ ለማድመጥ ጆሮውን ሲከፍት የግድ መሆን ያለበት አድማጭነት ነው፤ ከኃላፊነት የሚመነጭ አድማጭነት። ከእዚህ በመነሳት የአድማጭነት አቅማችንን ምን ይመስላል?

በኃላፊነት ውስጥ የሚሆን ማድመጥ ሁሉንም ነገር ተቀብሎ ማስተናገድ ማለት አይደለም። ነገር ግን ከኃላፊነት የሚወጣው አድማጭነት የወሰድነውን ኃላፊነት ዳር ማድረስ እንድንችል ዕድልን የሚሰጥ ነው።

አንድ አባት እየመራሁ ነው ብሎ የሚያስበውን ቤተሰብ ካላደመጠ ማንን ሊያደምጥ ይችላል? የቤተሰቡ አባላት ያሉበትን ሁኔታ የማያውቅ በፈጠረው በራሱ ዓለም ውስጥ ብቻ የሚኖር ከሆነ እርሱ አስቸጋሪ ይሆናል። አብረው እየኖሩ አብረው ወጥተው እየገቡ ነገርግን አንዱ ሌላውን የማያውቅበት ሕይወት በመግቢያችን ላይ ላነሳነው ዓይነት ገጠመኝ ይዳርግም ይሆናል።

ማንን ላዳምጥ የሚለው ጥያቄ በአግባቡ ምላሽ እንዲያገኝ የትስስር ሕግን ማሰብ ተገቢ ነው።

### የትስስር ሕግ

ማድመጥን በተመለከተ ጆን ማእክስዌል «የትስስር ሕግ» ብለው የሚያነሱትን ነጥብ እንመልከት። አንድ ሰው የሚከተሉትን ሰዎች እጅ ለሥራ ከመጠየቁ በፊት ልባቸውን ማግኘት አለበት። ያንን «የትስስር ሕግ» እንለዋለን። መሪው የግለሰቡን ልብ ከመንካቱ በፊት በግለሰቡ ልብ ውስጥ ያለውን ነገር ማወቅ አለበት። ማወቅ የሚችለው ግን ማድመጥ በመቻል ነው።

በደካማ ሰዎች ዘንድ መስማት ያለመፈለግ ዝንባሌ አለ። የአሜሪካን ማኔጅመንት አባት ተብሎ የሚጠቀሰው ፒተር ድራከር 60 በመቶ የሚሆነው የማኔጅመንት ችግር ስህተት ያለበት ግንኙነት ነው ይላል። ግንኙነትን መሠረት ካደረግ የማኔጅመንት ችግሮች መካከል ደግሞ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ደካማ የማዳመጥ ችግር ነው።

ትኩረትን የሚፈልጉ በርካታ ድምጾች በዙሪያችን አሉ። የማዳመጥ ጊዜን እንዴት ማሳለፍ እንዳለብን ስናስብ ውጤታማ ለመሆን ሁለት የማዳመጥ አላማዎች ልብ ማለት አለብን እነርሱም ከሰዎች ጋር ትስስርን ለማድረግ እና ለመማር ዝግጁ መሆን።

የትስስር ሕግን ከኃላፊነት የሚመጣ ማድመጥ ካልነው ነጥብ ጋር አገናኝተን ስናስበው ማንን ማድመጥ እንዳለብን በግልጽ እንረዳለን። በእዚህም ምክንያት ለሚከተሉት ሰዎች ጆሮን መክፈት የግድ ይላል፣

### 1. ተከታዮችን ማድመጥ

ልጆች በልጅነት ወቅታቸው የአባትና እናት ተከታዮች ናቸው። በተለያየ ጉዳይ መሪዎች ካሉ ተመሪዎች ደግሞ እንዲሁ ይኖራሉ፤ ተከታይ ልንላቸው የምንችል። ጥሩ የሚባሉ መሪዎች ከተከታዮቻቸው ጋር ግንኙነት ሲያደርጉ የሥራ ጉዳይን ከመፈጸም ያለፈን ግንኙነት ያደርጋሉ። እንደ ግለሰብ እያንዳንዱን ሰው ስሜት ለማዳመጥ ይሞክራሉ። ተከታዮች ወደ ውጤት እንዲደርሱ አስከታዩም ኃላፊነቱን መወጣት እንዲችል ያደርጋል። ከኃላፊነታችን የሚወጡ ተከታዮቻችንን ከልብ ማድመጥ መቻል ራሳችንን ከጥፋትም የሚጠብቀን መሆኑን መረዳት አለብን።

### 2. ግል-መካሪ የሆንክላቸውን ሰዎች፣

በሀገራችን ግለ-መካሪነት/mentoring ትኩረት ተሰጥቶት የሚሠራ አይደለም። ነገርግን አንዳንዴ በሃይማኖት፣ በሙያ፣ በጉርብትና፣ በማህበራዊ መስተጋብር ወዘተ ምክራችንን ፈልገው አጠገባችን የሚገኙ ሰዎች አሉ። እኒህ ሰዎች መደመጥን ይፈልጋሉ። እኛ የመናገር ዕድል ስላገኘን ሰዓቱን በሙሉ ተቆጣጥረን እኛ ብቻ እያወራን የምንመልሳቸው እንዳይሆን ማሰብ አለብን።

የግል-መካሪ ሊኖረው የማይገባ አንድም ሰው የለም በተለይም መሪዎች። የግል-መካሪ ከሌለን ዛሬ ነገሳንል እንፈልግ። ግለ-መካሪ ስንሆን ደግሞ ግል-መካሪ የሆንላቸውን ሰዎች በማድመጥ ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖረን እናድርግ።

### 3. ደንበኞችን ማድመጥ

ከቤተሰብ አልፈን ወደ ሥራው ዓለም ስንሄድ የሥራው ዓለም ደንበኛ በሚባሉ ሰዎች ላይ በደንብ የተደራጀ ነው። ተቋማት ደንበኛዬ ብለው ያሉትን ሊያገለግሉ በብዙ ይደከማሉ። ደንበኞች አድማጭ ካገኙ በሹክሹክታ መናገር ይችሉበታል። የሚያደምጣቸው ካጡ ሌላ አማራጭ ካለ ይሄዳሉ፤ አማራጭ ካጡ ግን ይጮሃሉ። ችሮኪ የተባለሰው እንዲህ አለ «በሹክሹክታ የሚነገርህን አዳምጥ ይህን ካደረክ በቁጣ ውስጥ ሆኖ የሚጮህ ሰውን ከመስማት ትድናለህ። » ከራሳቸው ሀሳብ ውጪ የደንበኞቻቸውን ስጋት፣ ቅሬታ እና ሃሳብ የማይሰሙ መሪዎች በእውነቱ አስገራሚዎች ናቸው። ቢልጌት Business @ the Speed of Thought በተሰኘው መጽሐፉ ላይ «እርካታ ያልተሰማቸው ደንበኞች ሁልጊዜ ስጋት ናቸው እንዲሁም ዕድል። » ማለታቸውን ብናነሳ ሃሳባችንን ያጠናክርልናል።

### አድማጭ ለመሆን ተግባራዊ እርምጃ

ዛሬ በእጃችን ሳለ ወደ አድማጭነት ለማደግ እንድንጠቀም ተግባራዊ ነጥቦችን በመጠቆም እናጠቃልል። ንድፈሃሳባዊ ነጥቦችን በአንድ በኩል ይዘን በተጨባጭ እንዴት መተግበር እንችላለን የሚለውን ማሰብ አስፈላጊ ነው።

*** ልብንና ጆሮን እኩል መስጠት** - ትኩረት መስጠት ለብዙ ነገሮች አስፈላጊ ነው። ባለንበት ዘመን ትኩረት የሚነጥቁ የበዙ ነገሮች አሉ። ትኩረትን የሚነጥቁ ነገሮች ባሉበት ሁኔታ በተበታተነ ትኩረት ውስጥ ማድመጥን በተግባር ማድረግ አስቸጋሪ ነው። ማድመጥ ውጤታማ መሆን እንዲችል ልብንና ጆሮን እኩል መስጠታችንን እርግጠኛ መሆን አለብን። ልጃችንን እያናገርን በአንድ በኩል ቲቪ እየጮኸ በሌላ በኩል ሞባይላችን አስሬ እያናገርን ወዘተ ውጤታማ መደማመጥ ማድረግ አንችልም። ሰዎች ሁካታ በሌለበት ድባብ ውስጥ የተሰማቸውን ለመናገር ይበረታታሉ በአግባቡ በመደመጣቸው ውስጥም ደስታን ያገኛሉና ልብንና ጆሮን እኩል በመስጠት ውስጥ እንዲሆን ማድረግ ወሳኙ የተግባር እርምጃ ነው። በትኩረት ውስጥ ስንሆን አጀንዳ ተኮር፣ መረጃ ተኮር ወይንም የሆነ ይዘት ተኮር ሆነን ሙሉ ትኩረታችን ጉዳዩ ላይ ይሆናል። ከእዚህ በተጨማሪ ግን ስሜት ተኮር የሆነ ድባብን ይፈጥራል። ለመደመጥ አስፈላጊ የሆነ።

***ጊዜን መመደብ** - ጊዜ ውድ የሆነበት ጊዜ የተረፈ መሆኑን በሚያሳብቅ በተቃርኖ ዘመን ውስጥ አለን። ሰዎች በማህበራዊ ሚዲያ ትርኪምርኪ ሲቃርሙ የሚውሉበትን ሁኔታ ስናይ ጊዜ ተረፈ እንላለን፤ ለመልካም ነገር እርስበርስ ለመደማመጥ ጊዜ ሲጠፋ ደግሞ የተቃርኖውን ሌላኛውን ገጽታ እናገኛለን። ቤተሰብህን፣ ተከታዮችህን፣ ደንበኞችህን፣ ተፎካካሪዎችን እና የግል-መካሪህን ለመስማት ጊዜ ትመድባለህ? እኒህ አካላት በመደበኛነት በካላንደርህ ውስጥ ከሌሉ ለእነርሱ ትኩረት አልሰጠህም ማለት ነው። በየዕለቱ፣ በየሳምንቱ ወይንም በወር ውስጥ ከእነዚህ ጋር የምትገናኝበትን ጊዜ አስቀምጥ። ይህን ማድረግ ለማድመጥ የሰጠኸውን ቦታ ያሳያል። ስለሆነም ሁለተኛው ተግባራዊ እርምጃ ዛሬውን ልታደምጣቸው ለተገቡት ጊዜ መመደብ ነው።

***በሰውዬው ጫማ ውስጥ መሆን** - አድማጭነትን ተቀብለህ በጊዜ ሰሌዳህ ላይም መድበህ ያንን ሰው ስታገኘው በእርሱ ጫማ ውስጥ በተግባር መሆን አለብህ። ይህን ለማድረግ ሰውዬውን ከግንኙነታችሁ በፊት አስበው፤ ስለ እርሱ ልትሰበስብ የምትችለውም መረጃ ይኑርህ። ጥሩ አድማጭ የመሆን ቁልፉ የጋራ መቆሚያ ቦታን ማግኘት መቻል ነው። ግለሰቡን ለማወቅ በምታደርገው ጥረት ውስጥ የጋራ መቆሚያ ቦታን ማግኘት ትችላለህ። በተጨማሪም በሚኖርህ ግንኙነት ወቅት ከግለሰቡ ራሱ በመጠየቅ በሰውዬው ጫማ ውስጥ መሆንን ልትለመድ ትችላለህ። በሚቀጥለው ጊዜ ከልጅህ ይሁን ከሠራተኞችህ ወይንም ከደምበኞችህ ጋር ስትገናኝ ስለግለሰቡ የግል ሕይወት አራት ወይንም አምስት ጥያቄዎች ልትጠይቀው ሞክር። ማን እንደሆነ ልታውቀው ሞክር በመካከላችሁ ትስስርን ለመፍጠር ይረዳሃልና።

ዛሬ በዙሪያችን፣ በአካባቢያችን፣ በከተማችን፣ በአገራችን፣ በዓለማችን ‘የአድማጭ ያለህ’ የሚሉ ድምጾች በርክተዋል። ኃላፊነት-መር አድማጭነትን መነሻ አድርገን በማድመጥ እንንትረፈረፍ ዘንድ ይህ ተጻፈ። መልካም አድማጭነት!

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ኢትዮጵያዊ ቀለም ካለው የስፌት ሥራ የተወዳጀች ወጣት



**ፍሬሕይወት አወቀ**

ትናንት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ደሳሳ ጎጆ ውስጥ በየጥጋ ጥጉ ተጎሳቁለው ስናያቸው የነበሩ ባህላዊ ቁሳቁሶች ዛሬ አምረውና ደምቀው በአደባባይ መታየት ጀምረዋል። ለወትሮው በዘመናዊ የመኖሪያ ህንጻዎች የውስጥና የውጭ ግድግዳዎች ላይ የምናስተውላቸው ዘመናዊ ጌጣጌጦችም ኢትዮጵያዊ ባህል በሆኑ በእነዚሁ የስፌት ሥራዎች ተተክተዋል። እነዚህ የስፌት ሥራዎች በልዩ ልዩ ዲዛይንና ከዘመኑ ጋር በዘመነ መንገድ በእጅ ተሰርተው ለተለያየ አገልግሎት መዋል እየቻሉ ነው። በዚህም የበርካቶችን ቀልብ መያዝ ችለዋል።

አሁን አሁን እየተለመደ የመጣውና የበርካቶችን ቀልብ መግዛት የቻለው የስፌት ሥራን ኢትዮጰያዊ ከሆኑ እናቶቻችን በተጨማሪ በዘመናዊ መንገድ እያሳመሩ ወደ አደባባይ የሚያወጡት ወጣቶች ናቸው። የዛሬው የስኬት አምድ እንግዳችንም ኢትዮጵያዊ የሆነውን ቱባ ባህል በድንግዝግዝ ሳይሆን በግልጽ የተረዳች ወጣት ናት። ወጣቷ ስንደዶን ከመርፌ፣ ከክርና ከወርቀዘቦ እያዋሃደች ኢትዮጵያዊ መገለጫ የሆኑ ቁሳቁሶችን በአይነት በአይነቱ ሰፍታ ለገበያ ታቀርባለች።

የእጅ ሥራን በገጠሪቷ ኢትዮጵያ ከሚኖሩ እናቶች እግር ሥር ተቀምጣ ነው የተማረችው። ያኔ ታድያ ሙያውን ለመቅሰም ስታስብ የደራውን ገበያ አስባ አልነበረም። “እንዲያው አለ አይደል!” ውስጣዊ ፍላጎቷን ለማሟላት እንጂ። ታዲያ ከጥልቅ መሻት የመጣው መነሳሳት የስፌት ሥራን እንዲሁም ጥጥ መፍተልን አቀላጥፋ መሥራት እንድትችል አገዛት። ይህ ደግሞ የስፌት ሥራዋን በዘመናዊ መንገድ ለማሳደግ በር ከፈተላት። ዛሬ ከአገር ውስጥ አልፋ በውጭው ዓለም ሳይቀር ኢትዮጵያዊ የሆኑ ሥራዎቿን ታቀርባለች። በተለያዩ ውድድሮች ላይም ትሳተፋለች። እየደበዘዘ የመጣውን ኢትዮጵያዊ ቱባ ባህል እየተረተረች ከአገር አልፋ ለዓለም ማሳየት የቻለችው ወጣት አርክቴክት አራራት ታምራት “የቱባ ባይ አራራት” መስራችና ባለቤት ናት።

ተወልዳ ያደገችው አዲስ አበባ ከተማ መሀል አራት ኪሎ ነው። ከልጅነት ዕድሜዋ ጀምራ ለእጅ ሥራዎች ትኩረት ትሰጣለች፤ መሥራት ያስደስታታል። በተለይም በቤታቸው የነበሩ የተለያዩ የስፌት አይነቶች ትኩረቷን ይወስዱት እንደነበርም አትዘነጋም። ውስጣዊ ፍላጎቷ የሆነውን የእጅ ሥራ ለመልመድና ለመሥራት የተነሳሳችውም የዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበረችበት ጊዜ መሆኑን አጫውታናለች።

አራራት በሙያዋ አርክቴክት ብትሆንም ለሥራዬ ያግዘኛል ያለችውን አካውንቲንግና ማኔጅመንትን ጨምሮ የተለያዩ ኮርሶችን ወስዳለች። ‹‹ከልብ ካለቀሱ እምባ አይገድም›› እንዲሉ የመጀመሪያ ዲግሪዋን በጎንደር ዩኒቨርሲቲ በምትማርበት ጊዜ ውስጣዊ ፍላጎቷ የሆነውን የእጅ ሥራ በቀላሉ መልመድ ችላለች። የለመደችበት መንገድም በጎንደር ገበያ ጥጥ የሚፈትሉ፣ የስፌት ሥራና ሌሎች የእጅ ሥራዎችን ከሚሠሩ ሰዎች ጋር በመወዳጀት ነው። አሠራሩን ጠይቃ በመረዳት የተረዳችውንም በተግባር በማዋል ዛሬ የስፌት ሥራዎችን በተለያየ ዲዛይን እያሳመረች ለገበየ ታቀርባለች።

የእጅ ሥራዎቿም አይነ ግቡ የሆኑ፣ ቀልብን የሚስቡና እጹብ ድንቅ ናቸው። እንደዘበት የተረሳውን፣ ኢትዮጵያዊ መገለጫ የሆነውን ቱባ ባህሎች ማስታወስ የሚያስችሉም ናቸው። አገርኛ ቀለም የያዙ ቱባ ባህሎችም ዛሬ ከወዳደቁበት ተነስተው አቧራቸው በመራገፉ ከራስ አልፈው በውጭው ዓለም መታወቅ ጀምረዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዘመናዊ መንገድ በመሰራታቸው ትኩረት ያገኙት የእጅ ሥራዎቹ ከቤት ውስጥ መገልገያነት ባለፈ የቤት ውስጥ ማስዋቢያና ጌጥ ሆነው በትላልቅ ሆቴሎች፣ ዘመናዊ መኖሪያ ቤቶችና በተለያዩ ተቋማት ውስጥ መታየት ጀምረዋል። የስፌት ሥራዎቹ ዛሬ ላይ ለመድረሳቸው ኢትዮጵያዊ እናቶች ትልቅ ሚና ቢኖራቸውም በተለይም የስፌት ሥራዎቹ ከዘመኑ ጋር ዘምነው ከአገር አልፈው በውጭው ዓለም ለመቅረባቸው ግን እንደ አራራት አይነት ወጣቶች ጉልህ ድርሻ አላቸው።

የእጅ ሥራ ሞያን ከውስጧ በመነጨ ፍላጎት መማር የቻለችው አራራት፤ ለሙያው ፍላጎት ቢኖራትም ቁሳቁሶቹን ከመገልገያነት ውጭ በቤት ውስጥ ሲሰራ ያየችው ሰው አልነበረም። ያም ቢሆን ግን ሙያውን የመልመድ ጥሩ አጋጣሚ አግኝታለች። በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ በለመደችው የስፌት ሥራ ገቢ ከማግኘቷ በተጨማሪ ኢትዮጵያዊ የሆነውን ቱባ ባህል በዘመናዊ መንገድ ለጌጣ ጌጥና ለመገልገያ መዋል እንዲችል ማድረጓ በእጅጉ እያስደሰታት የመጣ ጉዳይ መሆኑን ትናገራለች።

‹‹የስፌት ሥራ ኢትዮጵያዊ ባህላችንን ከሚያንጸባርቁት እንደ ሸክላና እንደ ሸመና ሁሉ ማንነታችንን የሚገልጽ የጥበብ ሥራ ነው›› የምትለው አራራት፤ በጎንደር ቆይታዋ ከትምህርቷ ጎን ለጎን የስፌት ሥራን በቀላሉ መልመድ ችላለች። እርሷ ይህን የጥበብ ሥራን ለመማር ዝግጁ እንደነበረችው ሁሉ የጎንደር እናቶችም ሙያውን ለማስተማር ፍጹም ፈቃደኞች እንደነበሩ በማስታወስ፤ ከመግዛት ባሻገር ሰዎች ባህላቸው ሲታወቅላቸው የሚያስደስታቸው እንደሆነ ነው የተረዳቸው።

የአርክቴክት ትምህረቷን አጠናቅቃ፤ የስፌት ሙያንም ለምዳ ወደ ሥራ የገባችበት ወቅት የኤፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶክተር ዓብይ አህመድ ወደ ሥልጣን የመጡበት ወቅት መሆኑ ጥሩ አጋጣሚ እንደፈጠረላት ታስታውሳለች። በወቅቱ በርካታ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የውስጥ ዲዛይን ሥራን በመሥራት የተዋቡ ቢሮዎች እንዲኖራቸው ተደርጓል።በመሆኑም ለወትሮው ምንም አይነት ውበት ያልነበራቸውና የእቃ ማጠራቀሚያ ይመስሉ የነበሩ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ደረጃቸውን በጠበቀ መንገድ የውስጥ ዲዛይን አሰርተዋል። በዚህ ወቅት ታድያ የአርክቴክት ሙያዋን ተጠቅማ ወደ ሥራው የመግባት ዕድል ያገኘችው አራራት፤ የብዙ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን ቢሮ የውስጥ ዲዛይን ሥራ መሥራቷም በእጅጉ ጠቅሟታል።

ከውስጥ ዲዛይን ሥራዋ ጎን ለጎንም ታስብ የነበረው ባህላዊ ቁሳቁሶችን ዘመናዊ በማድረግ ወደ ፊት ማምጣት ነበር። በወቅቱም መሰል ሥራዎች ገና አልተጀመሩም። ይሁን እንጂ እርሷ እንደ አርክቴክት የተለያዩ ንድፎችን ባልተለመደ ቀለምና ፓተርን ተመሳሳይ የሆኑ ቁሳቁሶችን በኮምፒውተር ታዘጋጅ ነበር። በውስጥ ዲዛይን ሥራዋ ወቅት ያስተዋለችውን ክፍተትም ባዘጋጀቻቸው ዲዛይኖች ለመሙላት ወስና ወደ ሥራው ገባች። ወደ ሥራው ስትገባ ታድያ እንደዋዛ አምስት ሺ ብር በመያዝ ስንደዶ፣ ሰበዝና ክር በመግዛት ነበር።

በቤቷ ውስጥ ተቀምጣ ከጀመረችው ሥራዎቿ መካከል በስፌትና በክር የተሠሩ የአበባ ማስቀመጫ ገንቦዎች ቀዳሚዎች ነበሩ። ገንቦዎቹን ለደንበኞቿ ማቅረብ ጀመረች። ሥራዎቿ ተቀባይነት እያገኙ ቀስ በቀስ እያደገ መምጣት ሲጀምርም ሥራዋን በማስፋት አንድ ሁለት በማለት ሠራተኞችን በመቅጠር ቱባ ባይ አራራት በሚል ስያሜ ድርጅቷን ማቋቋም ቻለች። በአምስት ሺ ብር እንደቀልድ የተጀመረው የስፌት ስራም አሁን ላይ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ደረጃ ላይ ደርሷል።

በስፌት ሥራዎቿ የተለያዩ የቤት ውስጥና የቢሮ ጌጣ ጌጦችን እና የመገልገያ ቁሳቁሶችን በመሥራት ለገበያ እያቀረበች የምትገኘው አራራት፤ ሥራዎቿን በሒልተን ሆቴል፣ በኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና በተለያዩ ሎጆች ውስጥ የሚገኙ እንደሆነ አንስታለች። ከምትሠራቸው የሥፌት ሥራዎች መካከል አንደኛው እርቦ የሚባለው ሰፌድ ሲሆን ሰፌዶቹ የተለያየ አይነትና መጠን ያላቸውና ለግድግዳ ጌጥ መሆን የሚችሉ ናቸው።

ከሰፌዶቹ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ የአበባ ማስቀመጫ ገንቦዎችንም እንዲሁ በዲዛይንና መቀለማቸው በማመሳሰል የምትሠራ ሲሆን በሽመና የሚሠሩ የሶፋ ትራሶች፣ ከምንጣፍና ከመጋረጃዎች ጋር በማመሳሰል እጅግ ዘመናዊ በሆነ መንገድ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን በዲዛይንና በቀለም አመሳስላ ትሠራለች። የስፌቱም ሆነ የሽመና ሥራው አርት ነው የምትለው አራራት፤ የዲዛይንና የቀለም ሥራው ኮምፒዩተር ላይ ከተጠናቀቀ በኋላ በሰዎች እጅ የሚሠራ እንደሆነም አስረድታለች።

ሥራው በእጅ የሚሠራ እንደመሆኑ በአሁን ወቅት ለሥራው ንቁና ብቁ ለሆኑ 40 ሴቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ችላለች። የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሴቶችም የቤት እመቤት የሆኑና በተለያዩ ችግሮች ውስጥ የሚገኙ የጎንደር ሴቶች እንደሆኑ ትናገራለች። ከእግራቸው ስር ተቀምጣ የስፌትና ጥጥ የመፍተል ሞያን የተማረችው አራራት፤ የሥራ ዕድሉንም ለእነዚሁ ሴቶች ሰጥታለች። ሴቶቹ ለቤታቸው አገልግሎት የሚውል እንዲሁም ትናንሽ ወጪያቸውን ለመሸፈን ያስችላል በሚል የተሰማሩበት የስፌት ሥራ በቋሚነት ገቢ እንዲያገኙበት አድርጓቸዋል።

ሥራውን የሚሠሩት ሴቶች በተለያየ ምክንያት ሙሉ ጊዜያቸውን በቤት ውስጥ የሚያሳልፉ እናቶች እንደሆኑ ያነሳችው አራራት፤ በተለይም የስፌት ሥራ ሙያው እያላቸው ነገር ግን ሥራውን ገቢ ማግኛ ያላደረጉና በተለያዩ ጫናዎች ከቤት መውጣት ያልቻሉ እናቶች ከቤት ሳይወጡ ሠርተው ገቢ ማግኘት የቻሉበት መንገድ በመፈጠሩ እጅግ ደስተኛ እንደሆነች ትናገራለች። ሥራውን ለመሥራት የሚያስችሉ ስንደዶ፣ ሰበዝ፣ የተለያዩ ክሮች፣ መስፊያና ሌሎች ግብዓቶች ጭምር ባሉበት የሚቀርብላቸው ሲሆን በኮምፒዩተር የተዘጋጀው ዲዛይንም በወረቀት ይቀርብላቸውና ዲዛይኑን መሠረት አድርገው ይሠራሉ።

የስፌት ሥራዎቹ በአገሪቱ የተለያ አካባቢዎች የተለመዱ ቢሆንም እንደየ አካባቢውና አሰራሩ የሚለያይ እንደሆነ ያስረዳችው አራራት፤ በተለይም በሀረርጌና በጉራጌ ማህበረሰብ በስፋት የሚታወቁ ስለመሆናቸው ታነሳለች። ሙያውን የለመደችው በሰሜኑ የአገሪቱ አካባቢ እንደመሆኑ በአካባቢው የተለመደውን በክር የሚሠራውን ስፌት ትሠራለች። የስፌት ሥራውም በስንደዶው ላይ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ክሮች በተቀመጠው ዲዛይን መሰረት የተጠለፉ እጅግ የተንቆጠቆጡ የስፌት እና የአበባ ማስቀመጫ ገንቦዎች ናቸው። ከአካባቢው ባገኘችው ልምድና ዕውቀት በመነሳት ወደ ሥራ የገባቸው አራራት፤ ቁሳቁሶቹን የምታሠራው በጎንደርና ባህርዳር አካባቢ ነው።

ለስፌት ሙያና ለጥጥ መፍተል ባላት ተነሳሽነት ሙያውን ተምራ ወደ ሥራ መቀየር የቻለችው አራራት፤ ተዘንግቶ የቆየውን ቱባ ባህል በዘመነ መንገድ ከማስተዋወቅ ባለፈ ምርቶቿን ለውጭ ገበያ በማቅረብም የኢትዮጵያን ባህል የማስተዋወቅ ሥራ እየሠራች ትገኛለች። ኢትዮጵያዊ ማንነትን አንጸባርቆ የሚያሳይ ስዕል በመፍጠር ሰዎች ወደ ቱባ ባህላቸው መመለስ እንዲችሉ ከማድረግ ባለፈም የስፌት ሥራ ዓለም አቀፍ እንዲሆን እያደረገች ትገኛለች።

“ባህላዊ የሆነን ማንኛውም ነገር ከዘመኑ ጋር አቆራኝቶ ማቅረብ ሲቻል የራስ የሆነ እሴትን ማቆየትና ለትውልድ ማስተላለፍ ይቻላል” የምትለው አራራት፤ ከዚህ ቀደም እናቶች ብቻ ይለብሱት የነበረው የሀገር ባህል አልባሳት አሁን ላይ ባለስልጣናቱን ጨምሮ ወንዱም፣ ሴቱም፣ ህጻናቱም በተለያዩ ፕሮግራሞች እንደሚዋቡበት ትገልፃለች። ይህ የሆነውም አልባሳቱ በዲዛይነሮች አማካኝነት እጅግ ዘመናዊ በሆነ መንገድ መቅረብ በመቻሉ እንደሆነ ትናገራለች። እርሷም በስፌት ሥራዎቿ በተለይም ወጣቱ ላይ ትኩረት በማድረግ እየደበዘዘ የመጣውን ባህል በጥሩ ጎኑ እንዲነሳና በስፋት እንዲተዋወቅ እያደረገች መሆኑን ነው የገለፀችልን።

እየደበዘዘ የመጣውን ኢትዮጵያዊ ቱባ ባህል ከማስታወስ ባለፈ በውጭው ዓለም እንዲተዋወቅ እያደረገች የምትገኘው አራራት በስፌት ሥራዎቿ ተወዳድራ ኢትዮጵያን በመወከል በተለያዩ አገራት ተጉዛለች። በቅርቡ ኔዘርላንድ ኤምባሲ ባዘጋጀው ውድድር ላይ ተሳትፋ አሸናፊ በመሆን ወደ ኔዘርላንድ በመሄድ የእጅ ሥራዎቿን አቅርባለች። በውድድሩ ተሳታፊ ከነበሩ በርካታ አገራት ጋር የመገናኘት ዕድል የገጠማት ሲሆን፤ ብዙ አፍሪካ አገራት በዘርፉ ሩቅ እንደተጓዙና ኢትዮጵያ ደግሞ ወደኋላ እንደቀረች መታዘብ ችላለች።

“የገበያ ክፍተት አለ ማንም ውስጣዊ ፍላጎት ያለው ሰው ገብቶ ቢሰራበት ተጠቃሚ ይሆናል” የምትለው አራራት፤ ትላልቅ በሚባሉ ሁነቶች ላይ መሳተፍ በመቻሏ በውጭው ዓለም የመታወቅ እድል ፈጥሮላታል። ለአብነትም እንደ አፍሪካ ህብረት የመሳሰሉ ጉባኤዎች ላይ በመሳተፍ የስፌት ሥራዎቿን ታቀርባለች። በዚህ አጋጣሚም ከአፍሪካ ሚዲያዎች ጋር የመተዋወቅ እድል አግኝታ ደቡብ አፍሪካ በሚገኝ Lioness of Africa በተሰኘ መጽሔት ምርጥ ሥራ ፈጣሪ ኢትዮጵያዊ ወጣት በሚል በፊት ገጽ ወጥታለች።

በአሁን ወቅት ወጣቱ የተዘነጋውን ቱባ ባህል በዘመናዊ መንገድ ሠርቶ ለዓለም የማቅረብ ሰፊ ዕድል ያለው መሆኑን ያነሳችው አራራት፤ ለዚህም በቂ የሰው ኃይልና አስፈላጊው ግብዓት መኖሩን በመጥቀስ የዓለም አገራት በቴክኖሎጂው መድረስ የሚገባቸው ደረጃ ደርሰዋል። በአሁን ወቅት ደግሞ ትኩረታቸውን እየሳበ ያለው ባህላዊ ቁሳቁሶች ናቸው። በመሆኑም ወደ ኋላ በመመለስ ባህሉ ላይ ትኩረት እያደረጉ ነውና ይህን ዕድል በመጠቀም ኢትዮጵያዊ ባህሎቻችንን ማውጣት ይኖርብናል ትላለች።

በቀጣይም ሥራዋን በማስፋት ለበርካታ ሴቶች የሥራ ዕድል የመፍጠር ዕቅድ ያላት አራራት፤ ቀደም ባሉት ግዜያት በሰሜኑ የአገሪቷ ክፍል ሰፋፊ እቅድ የነበራትና በዚያም መሰረት ሥራውን ጀምራ የነበረ ቢሆንም በጦርነቱ ምክንያት መበላሸቱን ታስታውሳለች። አሁን ሰላም ከሰፈነ ወደ አካባቢው በመሄድ የስፌት ሥራውን በስፋት ለመጀመር በአካባቢው ለሚገኙ ሴቶች ሰፊ የሥራ ዕድል የመፍጠር እቅድ እንዳላት ነግራናለች።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## አልጣጣም ያለው የሲሚንቶ ፍላጎት፤ አቅርቦትና መፍትሄው

**መሳኩ ሔሮሴ**



የኮንስትራክሽን ዘርፉን እየፈተኑ ካሉ ችግሮች አንዱ ዋነኛው የግብዓት እጥረት ነው:: በተለይም የሲምንቶ እጥረት እና ዋጋ መናር ዘርፉን መፈታተኑን ቀጥሏል:: ይህንን ችግር ለመቅረፍ መንግሥት የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ መሆኑን በተደጋጋሚ ቢገልጽም፤ መሬት ላይ ወርዶ የተለወጠ ነገር አለመኖሩን የዘርፉ ተዋናዮች ይናገራሉ:: በሲሚንቶ ላይ የተከሰተው የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች እንዲጓተቱ ከማድረጉም ባሻገር የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ክፉኛ እየጎዳው ይገኛል::

በቅርቡ በኮንስትራክሽን ዘርፍ በሚስተዋሉ ችግሮች ዙሪያ በተካሄደው አውደ ጥናት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ ይህው የሲሚንቶ ጉዳይ ነው:: የግንባታ ግብዓቶች አቅርቦት ላይ የፖሊሲ ግብዓት የሚሆን ጥናት ያቀረቡት አቶ ዘሪሁን ዘገየ እንደሚሉት የግንባታ ግብዓቶች በተለይም ለግንባታ ወሳኝ ግብዓት የሆነው የሲሚንቶ አቅርቦት ብዙ ክፍተቶች ያሉበት ነው::

በኢትዮጵያ ውስጥ እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ 20 የሚሆኑ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች አሉ:: እነዚህ የሲሚንቶ ፋብሪካዎችም የማምረት አቅማቸው የተለያየ ነው:: የፋብሪካዎቹ የማምረት አቅም 17 ነጥብ አንድ ሚሊየን ቶን ሲሆን ማምረት ያለባቸውን ያህል እያመረቱ አይደለም:: ወደ ስምንት ነጥብ አራት ሚሊየን ቶን አካባቢ ብቻ ነው የሚያመርቱት:: ይህ ከአቅርቦት አንጻር ስንመለከተ 45 ነጥብ 9 በመቶ ብቻ ነው::

አቶ ዘሪሁን እንደሚሉት ፋብሪካዎቹ በሚፈለገው ልክ አለማምረታቸው ብቻ ሳይሆን ከሚመረተው የሲሚንቶ ምርት ውስጥ አራት በመቶ የሚሆነው የሚባክን ነው:: ይህ የሚባክነው ሲሚንቶ ለፕሮጀክቶች በወቅቱ ተደራሽ ማድረግ ቢቻል ብዙ ገንዘብ እና ጉልበት የፈሰሰበትን ንብረት መታደግ ይቻል ነበር::

የሲሚንቶ እጥረት ጉዳይ በአሁኑ ወቅት አሳሳቢ ጉዳይ ከመሆኑ ባሻገር በቀጣይም እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ መቀጠሉ አይቀሬ ነው:: በቀጣይ መንግሥት ያቀዳቸው ሰፋፊ ፕሮጀክቶች አሉ:: በመንግሥት የተቀመጡ የአጭር፣ መካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶች አሉ:: መንግሥት በርካታ ቤቶችን ለመገንባት እቅድ ይዟል:: የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ያካሂዳል:: ግድቦች ይገነባሉ:: የሀገሪቱ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ማምረት ከሚጠበቅባቸው ውስጥ 45 ነጥብ 9 በመቶውን ብቻ እያመረቱ እነዚህን ፕሮጀክቶች ማሳካት የሚታሰብ አይሆንም::

እንደ አቶ ዘሪሁን ማብራሪያ የሲሚንቶ አቅርቦት በበርካታ ተግደሮቶች የተከበበ ነው:: ባለፉት ስድስት ዓመታት ከፍተኛ ግንባታዎች ነበሩ:: የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫዎች፣ የመንገድ ግንባታዎች፣ የቤቶች ግንባታ ነበር:: ይህ ሁሉ ግንባታ እየተካሄደ የሲሚንቶ እጥረት ያላጋጠመ መሆኑን በመጥቀስ የሲሚንቶ አቅርቦቱ በቂ እንደነበርና ከሀገር ውስጥ አልፎ ወደ ውጭ ሀገራትም ሲላክ እንደነበር ያስታውሳሉ::

ከዚህ ቀደም በሀገር ውስጥ ሲሚንቶ እየተመረተ ወደ ውጭ ሀገራት ሲላክም እንደነበር ያስታወሱት አቶ ዘሪሁን ሀገሪቱ በሲሚንቶ የወጪ ንግድ ብዙ ሚሊየን ዶላሮችንም ስታገኝ እንደነበር ያነሳሉ:: ነገር ግን ሲሚንቶ ሲመረት የነበረበት አካሄድ ትክክል አልነበረም:: ሀገሪቱ ሲሚንቶ ለማምረት ከፍተኛ የድንጋይ ከሰል ከውጭ ሀገራት ታስገባለች:: ይህ አሁን መቀጠል የለበትም:: የሀገር ውስጥ ግብዓቶችን በመጠቀም በሀገር ውስጥ ሲሚንቶ በስፋት ማምረት ይቻላል:: በስፋት ሀገር ውስጥ ሲሚንቶ አምርቶ በመሸጥ ኢኮኖሚውን መደገፍ ያስፈልጋል:: ካልሆነ ኢኮኖሚው ክፉኛ ይጎዳል::

ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ወደ ውጭ መላክ ቀርቶ የሀገር ውስጥ ፋላጎት ለማሟላት የሚያስችል ሲሚንቶ ማምረት አልተቻለም:: ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች አሉ:: ፕሮጀክቶቹ የሚጠበቅባቸውን ያህል እንዳያመርቱ ምክንያት ከሆኑ ተግዳሮቶች መካከል አንዱ ለሲምንቶ ማምረት የሚውል የጥሬ እቃ እጥረት ነው:: ከጥሬ እቃ ችግር ባሻገር የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረት፣ በፋብሪካዎች ብልሽት በሚያጋጥምበት ወቅት ማሽነሪዎችን መጠገን የሚችል የሰው ሀይል አለመኖር ችግር ዋነኛዎቹ ችግሮች ናቸው::

በዘርፉ ምርት እና ስርጭት ሂደት ኋላ ቀር እና ብልሹ አሰራሮች የሚስተዋልበት በመሆኑ ፋብሪካዎች የሚያመርቷቸው ምርቶች ወደ ቸርቻሪ ማህበራት እና ነጋዴዎች እንዳይደርስ እንቅፋት ሲሆን ይስተዋላል:: በዚህም ገበያ ውስጥ እጥረት እንዲፈጠር ምክንያት እየሆነ ነው::

እንደ አቶ ዘሪሁን ማብራሪያ ፋብሪካዎች ውስጥ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ከሚፈጠሩ ችግሮች ባሻገር የአቅርቦት እጥረቱ የበለጠ እንዲከሰት ፋብሪካዎች ውስጥ ገብተው ሆነ ብለው ችግር የሚፈጥሩ አካላትም አሉ:: ገብተው የፋብሪካዎችን ቺንጋ የሚቆርጡ ጭምር አሉ:: በሲሚንቶ ፋብሪካዎች ውስጥ ገብተው ችግር የሚፈጥሩበት ዋነኛው ምክንያት የሲሚንቶ እጥረቱ ሲባባስ የሲሚንቶ እጥረትን እንደ ምክንያት በመጠቀም ኮንትራክተሮቹ የሲሚንቶ አቅርቦት ውል ይገባሉ፤ በውሉ መሰረት 30 በመቶ ወስደው ወደ ሲሚንቶ ንግድ ይገባሉ::

የሲሚንቶ ስርጭት ሂደቱ ላይ ባለው ኋላ ቀር እና ብልሹ አሰራር ምክንያት ምን ያህል እንደተመረተ በአግባቡ አይታወቅም የሚሉት አቶ ዘሪሁን ምን ያህል ትራንስፖርት እንደተደረገ የሚመዘግብ ማሽን የለም:: እንዲህ አይነት ማሽኖች ቢኖሩ የተመረተውን የሲሚንቶ መጠን እና ወደ ፕሮጀክቶች የደረሰውን ማወቅ ይቻላል:: ችግሮች ሲፈጠሩም ማስተካከል ይቻል ነበር::

ሀገር በቀል አማራጭ የሀይል ምንጮች ላይ አለመመርኮዝ የሲሚንቶ ንዑስ ዘርፍን ክፉኛ እየጎዱ ካሉ ችግሮች አንዱ ነው:: በሀገሪቱ ውስጥ ሰፊ የሀይል አማራጮች አሉ:: ለሲሚንቶ ፋብሪካ ሊውል የሚችል ከፍተኛ ድንጋይ ከሰል አለ:: ሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል በመጠቀም ሲሚንቶ ለማምረት የሚወጣውን የነዳጅ መጠን መቀነስ ይቻላል:: ከድንጋይ ከሰል በተጨማሪ የተለያዩ ተረፈ ምርቶችን በመጠቀም ለሲምንቶ ምርት የሚወጣውን የነዳጅ ወጪን መቀነስ ይቻላል:: ይህንን መጠቀም ቢቻል የሲምንቶ ችግር ለመቅረፍ ወሳኝ ሚና መጨወት የሚችል ነው ይላሉ::

እንደ አቶ ዘሪሁን ማብራሪያ፤ የሲምንቶ ገበያን ለማረጋጋት መንግሥት ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ የሲሚንቶ ተመን ማውጣት ነው:: የሲሚንቶን ተመን በማውጣት ችግሩን መፍታት አልተቻለም:: የምርት እጥረት ካለ የምርት ተመን እና የትርፍ ጣሪያ በማስቀመጥ የገበያ ችግር አይፈታም:: ምክንያቱም ተመን እና የትርፍ ጣሪያ ከማስቀመጥ በፊት ምርቱ ሊኖር ይገባል:: ምርቱ ሲኖር ነው ያንን ምርት አለግባብ ሲሸጥ ከተገኘ ነው የትርፍ ህዳግ ማስቀመጥ እና በህዳጉ መሰረት እንዲሰሩ ማድረግ የሚቻለው::

ይሁንና በአሁን ወቅት የምርት ችግር ሳይፈታ ጣሪያ መቀመጡ ችግሩን እየፈታ አይደለም:: ስለዚህ የሲሚንቶ ችግርን ለመቅረፍ የሲሚንቶ ምርት መጨመር አለበት:: በየ ክልሎቹ ለሚገኙ ማህበራት ኮታ ተሰጥቷል:: ለማህበራቱ 50 ኩንታል ኮታ ነው የተሰጠው:: 50 ኩንታል በሁለት ቀን ነው የሚጨርሱት:: 50 ኩንታሉን ወስደው ለመሸጥ ይቸገራሉ:: ኮታው አነስተኛ ስለሆነ ወደ ጥቁር ገበያ እንዳይሄድ መከልከል አልተቻለም::

ምርት እንዳይጨምር ከሚያደርጉ ችግሮች አንዱ የጸጥታ ችግር ነው:: ከለውጡ ጋር ተያይዞ ከ2010 እና 2011 ዓ.ም ጀምሮ ሰፊ የሲሚንቶ እጥረት እንዲፈጠር እያደረጉ ካሉ ነገሮች መካከል በጸጥታ ችግሮች ምክንያት ኬላዎች መብዛት አንዱ ችግር ነው፤ የሚሉት አቶ ዘሪሁን፤ ሲሚንቶ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሲጓጓዝ ኬላ ዘግቶ ያለ አግባብ ቀረጥ መጠየቅ፣ ለማሳለፍ መከልከል ይስታዋላል:: በዚህ ምክንያት ብዙ ሲሚንቶ በመንገድ ላይ በዝናብ ተበላሽቷል::

ይህ ተገቢ አይደለም የሚሉት አቶ ዘሪሁን፤ አሁን ላሉ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች በየወሩ የሚሄደው የሲሚንቶ መጠን እየታወቀ፤ ሲሚንቶ እንዳያልፍ መንገድ እየዘጉ መኪናዎችን ማስቆም እና ለፕሮጀክቶች በጣም ወሳኝ የሆነው ሲሚንቶ እንዲበላሽ እና እንዲባክን ማድረግ የሀገር ሀብት ላይ መቀለድ ነው ይላሉ::

በሲሚንቶ ንኡስ ዘርፍ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ ተጨማሪ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል:: የግብዓት አቅርቦት ላይ መንግሥት እገዛ የሚያደርግበትን አሰራር መዘርጋት አለበት:: ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች ወሳኝ የሆኑ ግብዓቶች በሚፈለገው ልክ የሚቀርብበትን ሁኔታ ማመቻቸት የግድ ነው ብለዋል::

‹‹ሲሚንቶ ማጓጓዝ ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን መቅረፍም ሌላኛው ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው›› የሚሉት አቶ ዘሪሁን፤ ሲሚንቶ የሚያጓጉዙ ሹፌሮች ሲሚንቶን በወቅቱ ለማጓጓዝ እንደ ቦታው ርቀት እስከ 150 ሺ ብር የሚጠጋ ገንዘብ እየጠየቁ ነው:: ሲሚንቶ በወቅቱ እንዲደርስ የሚፈልግ አካል ብሩን መክፈል አለበት:: እስከ ጋምቤላ ለመውሰድ እስከ 150 ሺ ብር እየጠየቁ ነው:: እስከ ሀዋሳ ለማድረስ ደግሞ እስከ 100 ሺ ብር እየጠየቁ ነው:: ይህ አሰራር ሲሚንቶ በተፈለገበት ሰዓት ለፕሮጀክቶች እንዳይደርስ እያደረገ ነው:: ይህንን ብልሹ አሰራር ማስተካከል የሚያስችል የአሰራር ስርዓ መዘርጋት አለበት ብለዋል::

እንደ አቶ ዘሪሁን ማብራሪያ ሲሚንቶ ችግር ለመቅረፍ ለክልሎች የተቀመጠ ኮታ አለ:: ከኮታ በተጨማሪ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ደብዳቤዎችን ይጽፋል:: ሚኒስቴሩ ደብዳቤ የሚጽፈው ለመንግሥት ፕሮጀክቶች ነው:: ይህ የሚደረገው የእሴት ሰንሰለቱን ለማሳጠር ነው:: ይህ ጥሩ ነገር ሆኖ ሳለ ነገር ግን በትኩረት ባለመሰራቱ ክፍተቶችን ፈጥሯል:: የሚፈለገውን ውጤትም እያስገኘ አይደለም:: እሴት ሰንሰለቱን የማሳጠር ሥራ ጠንከር ባለ መልኩ ቢሰራበት መልካም ነው:: ልዩ ትኩረትም ሊሰጠው ይገባል::

ከመንግሥት ፕሮጀክቶች በተጨማሪ ከባድ ችግር ውስጥ እያለፉ ያሉት የግል ፕሮጀክቶች ናቸው:: የግል ፕሮጀክቶች በስፔስፊኬሽኑ መሰረት ጣሪያ ወጥቶላቸው ቀጥታ ከፋብሪካ እንዲያገኙ ቢደረግ መሃል ላይ ያለውን እንግልትና የሰንሰለቱን ርዝመት ሊቀንስ ይችላል:: ሊዚህም የአሰራር ስርዓት ቢዘረጋለት የሲሚንቶ እጥረት በዘላቂነት እስኪፈታ ድረስ በጊዜያዊነት የግሉ ፕሮጀክቶች እያጋጠማቸው ያለውን ችግር ለመፍታት የሚያስችል እንደሆነ አስረድተዋል::

ለዘርፉ ልማትና እድገት የሚያግዙ ዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ ግንኙነቶችን መፍጠር ወሳኝ እንደሆነ በማንሳት፤ በአሁኑ ወቅት ከውጭው ዓለም ጋር የሚኖር ጤናማ መስተጋብር ጠቃሚ በመሆኑም ትኩረት ያሻዋል:: ከውጭው ዓለም ባሻገር በሀገር ውስጥ ተናቦ መስራት አስፈላጊ እንደሆነ በመግለጽ በተለይም የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ሂደት ውስጥ የክልል አስተዳደሮች ከማዕድን ማምረቻዎች ጋር ያላቸውን አሰራር ማሻሻል አለባቸው:: በአሁኑ ወቅት ለሲሚንቶ ምርት ዋና ግብዓት ለመውሰድ በሚደረገው ጥረት ከገበሬ ጋር በሚፈጠር ጭቅጭቅ የክልሉ አስተዳደር ችግሮችን መቅረፍ አልቻለም:: ከዚህም ባሻገር የጥሬ እቃ አቅርቦት ምርት አለማሳደግ ስላለ እነዚህን ችግሮች የክልል መንግሥታት ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ጋር በጋራ መሥራት ከተቻለ መፍታት የሚቻል እንደሆነ አንስተዋል::

የሲሚንቶ ችግሮችን ለመቅረፍ ወሳኝ ከሆኑት ነገሮች አንዱ መሰረተ ልማት መሆኑን በማንሳትም፤ ሲሚንቶ ለፋብሪካዎች ለማቅረብም ሆነ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች ወሳኝ የሆኑ ግብዓቶችን በማቅረብ በዘርፉ የሚስተዋለውን ችግር መፍታት ተገቢ ነው:: በተለይ ጥሬ እቃዎች ካሉባቸው አካባቢዎች ወደ ፋብሪካዎች ለማቅረብ እና በቂ ምርት ማምረት እንዲቻል መሰረተ ልማት ወሳኝ ነው:: በተለይም በአካባቢዎቹ መሰረተ ልማቶችን መዘርጋት ትኩረት የሚያሻው ተግባር ነው:: ጥሬ እቃዎች ያሉባቸው አካባቢዎች በተለይም በዝናባማ ወቅት ጥሬ እቃዎችን ለማጓጓዝ እጅግ አዳጋች በመሆናቸው የሲሚንቶ ምርት በአግባቡ እንዳይመረት ከሚያደርጉ ችግሮች አንዱ የመንገድ ችግር ነው:: በመሆኑም እነዚህን መሰረተ ልማቶች ማሟላት እና አማራጭ ግብዓቶችን በመጠቀም የሚበረታቱበትን አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢኮኖሚያዊ ስኬቶችን በላቀ ደረጃ ማስቀጠል ይገባል!

ኢኮኖሚዋ በግብርናው ላይ ጥገኛ ሆኖ ዘመናትን የተሻገረችው ኢትዮጵያ፤ ከለውጡ ቀድሞ ባሉት ዓመታት ጭምር ለተከታታይ ዓመታት ባለሁለት አሃዝ እድገት ስለማስመዝገቧ ተነግሯል። በወቅቱ የተመዘገበው ዕድገት ታድያ ምንም እንኳን የሚካድ ባይሆንም፤ እድገቱ ግን ምሉዕ ያለመሆኑ በብዙ መልኩ ትችት ሲያስተናግድ ቆይቷል። ለዚህ እንደ ማሳያ ከሚነሱ ጉዳዮች መካከል ደግሞ፤ በአንድ በኩል እድገቱ ለጥቂቶች የሃብት ማማነት ከመዋል የዘለለ ለብዙሃኑ ያልፈየደ ስለመሆኑ፤ በሌላ በኩል እድገቱ በብድር ላይ የተንጠለጠለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ውጤቱ ሲመዘን ለአገራዊ ኢኮኖሚው እምብዛም ተደማሪ ፋይዳ ያልነበረው ስለመሆኑ፤ በተመሳሳይ መልኩ እድገቱ ግብርናው ላይ ብቻ የተመሰረተ እና ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፍ አማራጮችን ያልተመለከተ ስለመሆኑ ይነሳል።

የነዚህ ድምር ማሳያዎች መገለጫ ተብለው ከሚነሱ ጉዳዮች መካከል ደግሞ፤ የስራ አጥነት ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ መጨመር፣ የኑሮ ውድነት፣ ኢ-ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት፣ ከድህነት ወለል በታች ያሉ ዜጎች ቁጥር መብዛት እንዲሁም ከዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በቀዳሚነት የሚነሱ ሲሆን፤ ኢኮኖሚው የተንጠለጠለበት ግብርና በራሱ ያልዘመነ እና በመንግስትም ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑ ደግሞ የእድገቱን ነጠላነት ብቻ ሳይሆን የነጠላ ጉዞውም መሰረት ያልነበረው ስለመሆኑ አመላካች ነው። ግብርናው በራሱ ዘመናዊነት የራቀው፤ የውስጥ ብዝሃነት የተነፈገው፤ ከቴክኖሎጂ የተራራቀ፤ የአርሷደሩ ተጠቃሚነት ያልተረጋገጠበት፤... በጥቅሉ ግብርናው የተጣለበትን አገራዊ የኢኮኖሚ መዋቅር ሽግግር ለማሳካት በማይችልበት ችግር ውስጥ እንደነበር ብዙዎች የሚስማሙበት ሃቅ ነበር።

ይሄን እውነት የተገነዘበው የለውጡ አመራር ግን አገራዊ ኢኮኖሚውን ለማስፈንጠር እና ከተጨባጭ አገራዊ እውነቶች ጋር ያልተገናዘበውን አካሄድ ለመለወጥ የሚያስችል አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሪፎርም በማዘጋጀት ወደስራ መግባት ቻለ። የዚህ ማሻሻያ ትኩረት ደግሞ፤ በኢኮኖሚው ዘርፍ ያሉ ችግሮችን መለየት፤ የችግሮቹን መፍትሄ ማመላከት፤ ለኢኮኖሚ እድገት መሰረት የሆኑ ሃገራዊ አቅሞችን መለየት፣ እነዚህን አቅሞች ማልማት እና የኢኮኖሚው እድገት አጋዥ ማድረግ ነው። ይሄን መነሻ በማድረግም ኢትዮጵያ ያሏትን ሃብቶች የመለየት ስራ በማከናወን፤ በተለይ በግብርናው፣ በኢንዱስትሪው፣ በቱሪዝም፣ በማዕድን፣ በአገልግሎትና ሌሎችም መስኮች ያሏትን እምቅ አቅሞች ማልማትና ከዘርፎቹ ተገቢውን ተጠቃሚነት ማምጣት እየተቻለ ነው።

በዚህ ረገድ የቱሪዝም ሃብቱን ማልማትና ማስተዋወቅ ላይ የተሰሩ የሸገርና የሃገር ፕሮጀክቶች አበረታች ውጤት ታይቶባቸዋል። በማዕድን ዘርፉም የተጀመረውና እየተገኘ ያለውም ውጤት ይበል የሚያሰኝ ሆኗል። በአገልግሎት ዘርፉም ሆነ "ኢትዮጵያ ታምርት" ተብሎ እየተሰራበት ያለው የኢንዱስትሪው ዘርፍም ምንም እንኳን በግብዓትና ሌሎች ተዛማጅ ችግሮች እየፈተነ ቢሆንም ጅምሩ ትልቅ ተስፋ ሰጪና ውጤትም እየተገኘበት ያለ ነው። ከዚህ ሁሉ በላቀ መልኩ ግብርናው ላይ እየተመዘገበ ያለው ውጤት ከራስ አልፎ ለሌሎች መትረፍ እንደሚቻል ህያው ምስክር ሆኖ ተገልጧል።

ዛሬ ላይ ዘርፉ ቀደም ሲል ኢኮኖሚውን እንዲሸከም ሲደረግ በተለምዷዊው የአስተራረስ ሥርዓት ላይ ተመስርቶ ያለበቂ ትኩረት ሲከናወን ከቆየበት ወጥቶ፤ ወደ ሜካናይዜሽን የአስተራረስ ስርዓት እንዲቀላቀል እየተደረገ ይገኛል። በተበጣጠሰ ማሳ ላይ የሚፈጸመውን የሰብል ልማት በኩታ ገጠም እየተተካ ይገኛል። የስንዴ አብዮቱም፤ ስንዴ በመስኖና በቆላማ አከባቢዎች በስፋት እንዲመረት በማድረግ፣ ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናዋን አረጋግጣ ከስንዴ ተረጂነትና ሸማችነት ወደ ስንዴ ላኪነት የምትሸጋገርበትን ጊዜ አቅርቦታል። እንደ አጠቃላይ ከለውጡ ማግስት በኢኮኖሚው ላይ የተወሰደው ሃገር በቀል የማሻሻያ ርምጃ፣ እንደ ሃገር ኢኮኖሚው ከአንድ ዘርፍ ጥገኝነት ተላቅቆ ወደ ብዝሃ ዘርፍ እድገት የተሸጋገረበት፤ የዜጎችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራት የተከናወኑበት ሆኗል።

የኢኮኖሚው ዘርፍ እድገትና አጠቃላይ ስኬት በዚህ መልኩ ሲመዘገብ ሂደቱ አልጋ በአልጋ አልነበረም። ይልቁንም ኢትዮጵያ ጦርነትን ጨምሮ በበርካታ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች በብዙ እየተፈተነች ባለችበት ወቅት የተመዘገበ ነውና። ይሄ ደግሞ ሃገር በተረጋጋ ሰላም ውስጥ ከሆነች እና ሌሎች ሃገራዊና ዓለማቀፋዊ ተግዳሮቶች መቃለል ከቻሉ ኢኮኖሚዋ የበለጠ ሊያድግና የዜጎችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ስለመሆኑ እሙን ነው። ይህ እንዲሆን እና የተገኘው ውጤት የበለጠ እንዲልቅ በማድረግ ሂደት ደግሞ ሁሉም አካል በየተሰማራበት ዘርፍ የሚችለውን ሁሉ ማበርከትና መወጣት የሚጠበቅበት መሆኑን ተገንዝቦ፤ በችግር ውስጥም ተሁኖ የተገኙትን ኢኮኖሚያዊ ስኬቶችና ድሎችን በላቀ መልኩ ማስቀጠል እና የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግና እውን ማድረግ ተገቢ ይሆናል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## «ኮብራ ኢፌክት» እንዳይከሰት

**ታምራት ተስፋዬ**

ሆርስት ሲበርት በአለም አቀፍ ደረጃ ስመጥር የኢኮኖሚ ምሁር ነው።ስለ ኢኮኖሚ ሲነሳ«ኮብራ ኢፌክት፣Cobra effect»በሚለው እሳቤው ይበልጡን ይታወቃል።በጀርመናዊ ሰው እሳቤ«ኮብራ ኢፌክት»ለአንድ ችግር በምንሰጠው መፍትሄና መፍትሄው ላስከተለው ችግር የምንሰነዝረው ምላሽ የከፋ ችግር ሲፈጥር እንደማለት ነው።

«የኮብራ ኢፌክት» እሳቤ ምሳሌ ሆኖ በተለያዩ ክስተቶች ላይ ይጠቀሳል።እንግሊዛውያን ህንድን በቅኝ ግዛት ያስተዳድሩ በነበረበት ጊዜ የተከሰተው ታሪክ ደግሞ በግንባር ቀደምትነት ይታወሳል።ወቅቱ በህንድ ሀገር በደልሂ ከተማ የመርዘኛ ኮብራ እባቦች መበራከት አሳሳቢ ደረጃ ይደርሳል።እንግሊዞችም የእባቦቹን ቁጥር ለመቀነስ እባቡን ገድሎ ይዞ ለሚመጣ ማንኛውም ግለሰብ ከመንግስት ሽልማት እንደሚበረከትለት አዋጅ አስነገሩ።ይህን ተከትሎ የእባቦቹን ቁጥር ለጥቂት ጊዜ በእጅጉ ቀነሰ።

ከጊዜ በኋላ ግን ህንዳውያኑ ሽልማት ለማገኘት ሲሉ በየጓሮቸው እባብ ያረቡ ጀመር።ይህን የተረዳው የእንግሊዝ መንግስትም አዋጁን ሽሮ ሽልማት መስጠት አቆመ።በዚህ የተናደዱት ህንዳውያንም እያረቧቸው የነበሩትን እባቦች ለቀቋቸው።የመርዘኛ ኮብራ እባቦች ቁጥርም ከፊቱ የባሰ ሆነ።

ይሕ ታሪክ አመታትን ያስቆጥር እንጂ ዛሬም በአለም አቀፍ ደረጃ አገራት የተለያዩ ችግሮች ለመሻገር የፖሊስ እርምጃዎች ሲወሰዱ ውሳኔው ያስከተለው ተፅዕኖ፣ተፅዕኖውን ለመቀነስ የተወሰደው ማስተካከያ የባሰ ተፅዕኖ ሲፈጥር እንደምሳሌነት ይጠቀሳል።

ኮብራ ኢፌክት በኢትዮጵያም ላለፉት በርካታ አመታት በተለያዩ መንግስታት የፖሊሲና ሌሎች ማሻሻያ ውሳኔዎች ላይ ተደጋግሞ ታይታል።በዚህም እንደ አገር ውድ ዋጋ ተከፍሏል።የጠቅላይ ሚኒስተር ዶክተር አብይ አህመድ አስተዳደር ወደ ስልጣን ከመጣ ወዲህም ችግሮች ለመፍታት የተለያዩ የፖሊሲ ለውጦችና ማሻሻያዎችን እያደረገ ይገኛል። የፖሊሲ ማሻሻያ ከተደረገባቸው መካካል የፋይንስ ዘርፍ ተጠቃሽ ነው።

እንደሚታወሰው፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባሳለፍነው አመት የካቲት ወር አጋማሽ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሲሠጡ ካነሳቸው አበይት ጉዳዮች መካከል የባንክ ኢንዱስትሪው አንዱ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወቅቱ «የኢትዮጵያ ባንኮች ላለፉት 20 ዓመታት ብቻቸውን የሚሰሩበትን እድል አግኝተው ቆይተዋል፣የውጪ ባንክ አለማሳገባት እስካሁን ላለው ሁኔታ ጠቅሟል፣አሁን ግን ይህንን ማስቀጠል አይቻልም፤ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪና ሀብት ስለሚያስፈልግ የውጭ ባንኮች መምጣታቸው አይቀርም» ብለዋል። ባንኮች በቴክኖሎጂ እና በዘመናዊ አሰራር ራሳቸውን በማደራጀት ከፍ ላለ ውድድር ራሳቸውን ማዘጋጀት እንዳላባቸውም አፅእኖት ሰጥተው አስገንዝበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስገነባው ህንጻ በተመረቀበት ወቅትም ካስተላለፏቸው መልዕክቶች አንዱ በቀጣይ የውጭ ባንኮች ስለሚገቡ የሀገር ውስጥ ባንኮች ከወዲሁ እራሳቸውን እንዲያዘጋጁ የሚመክር ነበር።ላለፉት ሶስት አስርት ዓመታት ያህል የውጭ ባንኮችን ገድቦ የቆየው ይሕ አሰራር በአሁን ወቅት በለውጥ ሂደት ላይ ይገኛል። በእኔ እምነትም ውሳኔ እጅጉን ወሳኝ ነው። ምክንያቱ ኢትዮጵያ በየትኛውም መስፈርት ከአለም አቀፉ የፋይናንስ ስርአት ውጪ ልትራመድ አይገባም።አለም በደረሰበት የፋይንንስ ደረጃ እድገት ላይ መድረስ ይኖርባታል።የኢትዮጵያ ህዝብም ማግኘት ያለበትን የተቀላጠፈ፣ የተሳለጠና የተሟላ አገልግሎት ማግኘት አለበት። በአሁን ወቅት የኢትዮጵያ ባንኮች በአገር ውስጥ ባላቸው ተሳትፎ ውጤታማና አትራፊ ናቸው። ሀብታቸው ከአመት አመት እያደረገ መጥቷል።የባለድርሻዎች የሀብት መጠንም እንዲሁ ጭማሪ እያሳየ ይገኛል።የባንኮች የቅርጫፍ መጠንም ከፍ እያለ መጥተዋል።

ይሑንና አለም ከደረሰበት የፋይናንስ ኢንዱስትሪ አንፃር ረጅም እድሜ ያስቆጠሩትን ጨምሮ ቁመናቸው ሲፈተሸ በቴክኖሎጂ፣በተደራሽነትም ሆነ በካፒታል አቅም ጀማሪ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው።አንዳንዶቹ ባንኮች ደግሞ እንኳን ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪ ሊሆኑ ቀርቶ የሀገር ውስጥ ደንበኞችንም የማርካት አቅም እንደሌላቸው በርካቶች ይስማሙበታል።ይሕ ማለት ግን የአገር ውስጥ ባንኮቹ ራሳቸውን አልቻሉምና «አትምጡባቸው»ማለት ብዙ ርቀትን አያስኬድም።

የውጭ አገራቱ ባንኮች መግባትም የተለያዩ አገር ኢንቨስተሮች በአንድ አገር ኢንቨስት ለማድረግ ሲፈልጉ ከሚጠይቋቸው ጥያቄዎች አንዱና ዋነኛው የባንክ ዘርፉ ሁለናተናዊ አቅም ነው።ኢንዱስትሪው ለውጭ ተዋናዮች ክፍት መሆኑም በተለይም በሀገሪቱ የሚከናወኑ ትላልቅ ፕሮጀክቶች በብድርና በልመና ከመስራት ተላቀው የሚፈልጉትን ብድር የሚያገኙበትን አማራጭ የመፍጠር አቅሙ ከፍተኛ ነው።

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ብቃትን ለመጨመር ያግዛል።ከውድድር በተጨማሪ ቴክኖሎጂ፣እውቀትና አዳዲስ አሰራሮችም ያስተዋውቃል።የአገር ውስጥ ተቋማት በሥጋት ሳቢያ ገሸሽ ያደረጓቸውን ዘርፎች በመድፈር ጭምር አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉበት አግባብ ሊፈጥርም ይችላል።አንዳንዶች የቢዝነስ እውቀት፣ አቅምና ችሎታ ኖሯቸው ማስያዣ ስለሌላቸው ብቻ ብድር ማግኘት የማይችሉበትን አሰራር የማስቀረት አቅም ይኖረዋል።

ይሕ ማለት ግን ስጋቶች አይኖሩም ማለት አይደለም።የውጭ ባንኮቹ የፋይናንስ ኢንዱትሪውን መቀላቀል በቅርብ ለተቋቋሙ አዳዲስ ባንኮች አይደለም ለነባሮቹ ጭምር ከባድ ውድድርን ይዞ እንደሚመጣም እርግጥ ነው።በተለይ እነዚህ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ የማቅረብ አቅማቸው ከፍተኛ ስለሆነ ብዙ የውጭ ምንዛሪ ይዘው መጥተው ትልልቅ እና ዋነኛ ደንበኞችን ከአገር ውስጥ ባንኮች ሊነጥቁ የሚችሉበት እድልም ሰፊ ነው።ይህ ከሆነ ደግሞ የታሰበው ቀርቶ ያልታሰበው መምጣቱ እና በመግቢያ ላይ እንደጠቀሰውን አይነት «ኮብራ ኢፌክት» መከሰቱ አይቀሬ ይሆናል።

ይሑንና ከተሰራበት ኮብራ ኢፌክት እንዳይከሰት ማድረግም በጣሙን ቀላል ነው።ስራው ግን ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ አይነት ፈፅሞ መሆን የለበትም።ከወዲሁ ከፍተኛ ዝግጅት ማድረግና አስፈላጊውን የቤት ስራ ሰርቶ መጠበቅ የግድ ይላል። በተለይ ባንኮቹ ተወዳዳሪ በሌለበት ይህን ያክል ትርፍ አግኝተናል እያሉ መኩፈስ ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩ እርምጃ ከወዲሁ ደንበኞቻቸውን ማስቀጠል የሚችሉባቸውን አሰራሮች ከመዘርጋት ጀምሮ ለሁሉ አቀፍ ተወዳዳሪነት ራሳቸውን ዝግጁ ማድረግ ግድ ይላቸዋል።

ከሁሉ በላይ የሀገር ውስጥ ባንኮች በሃይማኖት፣ፖለቲካ በዘር ሳይሆን ዓለም አቀፍ ገበያው ላይ አቅም የሚፈጥሩበትና ከሀገር ውስጥ መውጣት የሚችሉበት አደረጃጀት ይዘው ስለመምጣት ሊጨነቁ ይገባል።በተለይ ግዙፍ አቅም ለመገንባት ነባሮችም ሆነ አዳዲስ ባንኮች ጥምረትን እንደ አንድና ዋነኛ አማራጭ ቢመለከቱት አትራፊ እንጂ ተጎጂ እንደማይሆኑ ማሰብም ይኖርባቸዋል። በተለይ ባንኮች ተወዳዳሪ ሆነው በኢንዱስትሪው ለመዝለቅ በካፒታል ሊጎለብቱ በሰው ኃይል ረገድ ብቃት ባለው አመራርና በዲጂታል ቴክኖሎጂ ሊያዘምኑ ይገባል።የአገልግሎታቸውን ተደራሽነትና ጥራት በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግም ደንበኞቻቸውን ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ አዳዲ ፓኬጆችን ተግባራዊ ማድረግና ደንበኞችን የሚያሸሹ አላስፈላጊ ድርጊቶችን ማስወገድም የግድ ይላቸዋል።

የውጭ ባንኮች ተዋናይ ሆነው ወደ ኢንዱስትሪው ሲመጡ በተለይ ብሄራዊ ባንክ የሀገሪቱን የፋይናንስ ዘርፍና የህዝብን ንብረት ለመቆጣጠርና ደህንነትን ለማስጠበቅ አሁን ካለው የበለጠ አቅም መፈጠር ይኖርበታል። ባንኮቹ የሚሰጡት አገልግሎት አንዳንዴ የተወሳሰበ ስለሚሆን መመሪያዎቹም ለዚያ በሚመጥኑ መልኩ መቀመር የግድ ይላል።ለውጭ ባንኮች በራቸውን ክፍት አድርገው ከኪሳራ ይልቅ ትርፋማ ከሆኑት ሲንጋፖር፣ ሆንግ ኮንግ፣ ቻይናን የመሳሰሉ አገራት ተሞክሮ መቀመር መዘንጋትም የለበትም።

በተለይም ባንኮቹ እንዴት ወደ መግባትና አገልግሎት መስጠት አለባቸው?አገሪቱ ውስጥ ከሚገኙ ባንኮች ጋር የሚኖራቸው ትብብርስ ምን መምሰል አለበት?በተወዳዳሪነት ወይንስ በተባባሪነት?የሚለውን በጥልቀት በመቃኘት መሆን ያለበትን በአግባቡ መቀመር የግድ ይላል። የፋይናንስ ኢንዱስትሪውን በምሳሌነት አነሳን እንጂ «ኮብራ ኢፌክት»በሌሎችም ዘርፎች እንዳይከሰት አስፈላጊውን ሁሉ ጥንቃቄና ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ፈፅሞ ሊዘነጋ አይገባም።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብሰው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ነገ እስኪነጋ...

መልካምሥራ አፈወርቅ

### ከዓመታት በፊት- ልጅነት

ከስራ መልስ በእጇ ያለውን ገንዘብ ደጋግማ ትቆጥራለች ። ለዛሬ ውሎዋ በቂ ነው ። ከእሷ ይህን ያህል ካለ ሌሎች ባልንጀሮቿን አትረሳም። የያዘችውን ይዛ ከያሉበት ትፈልጋቸዋለች ። ሲገናኙ እንደ አቅሟ ትጋብዛቸዋለች። እነሱም ቢሆኑ እንደ እሷ ናቸው። ያላቸውን ይዘው፣ ያገኙትን ቋጥረው ይፈልጓታል። እንዳሻቸው ተገባብዘው የልባቸውን ሞልተው ይሸኛኛሉ ።

ጓደኛሞቹ አይለያዩም። መፈላለጋቸው ሁሌም ለአንድ ዓላማ ነው። በቀጠሮ ተገናኝተው ዋንጫቸውን ያነሳሉ። በርከት ሲሉ ግብዣው ይደራል፣ መጠጡ ይደረደራል። ጅማሬቸው ፈዘዝ፣ ቀዝቀዝ፣ እንዳለ ጥቂት ይዘልቃል ። ቆይቶ ጨዋታ ሳቁ ፣ ሞቅታው ስካሩ ይከተላል። ልክ እንደ ትናንቱ፣ እንደአምና ካቻምናው ።

ደግሞ በሌላ ቀን ሌላ ቀጠሮ ይያዛል ። ለቁምነገር አይደለም ። ለመጠጥ፣ ለጨዋታው ቀን ቀጠሮ ይቆረጣል። ሁሉም ለልምዱ ያለውን ይዞ፣ ያገኘውን ቋጥሮ ከመሸታው ይገኛል ። ድራፍት፣ ቢራው ይቀዳል፣ ሙዚቃ ዳንሱ ይደራል ። ሳቅ ጨዋታው ይደምቃል። የዛኔ ወጣትነት ትርጉሙ ፣ ልጅነት ለዛው ይታያል።

በዚህ ሰዓት ማንም ምንም አይመስለውም። የእጁ እስኪያልቅ፣ የኪሱ እኪሲደርቅ በዛሬ አናት ቆሞ ነገውን ያስባል። የነገው ንጋት ከትናንቱ አይለይም። ለሁሉም ብርጭቆ ውስጥ ተደብቆ፣ ራስን የመርሳት ቀጠሮ ነው ። ቀኑ ከመጠጥ ፣ ከጭፈራው ተዋዶ፣ መልሶ ከእነሱ ሊዛመድ ጊዜውን ሳይስት ይደርሳል ። ሁሉም ‹‹በአስረሽ ምቺው››፣ በመዝናናት ሰበብ ዕድሜ ጊዜውን ይፈጃል።

### ከዓመታት በኋላ

ሲቲና ሀሰን ዛሬ ላይ ሆና የልጅነት ጊዜዋን ስታስብ ውስጧ በዥንጉርጉር ስሜት ይመላል ። የአፍላነት ዕድሜዋ ለእሷ መልከ ብዙ ሆኖ አልፏል ። የዛኔ ከትምህርት ይልቅ ማንነቷ የተሰጠው ለጉልበት ስራ ነበር። እሷን መሰል ከሆኑት ጋር በቡና ለቀማ ስራ ገንዘብ ታገኛለች ። ከምታገኘው ገንዘብ ጥቂቱን ብቻ ለእናቷ እየሰጠች በርከት ያለውን ብር በእሷ አገላለጽ ‹‹ትጨስበታለች፣ ትጨብስበታለች››

እናት ልጆቻቸውን የሚያሳድጉት ያለአባት ነው። አባወራው ከሞቱ በኋላ በቤታቸው ድህነት ሰፍኗል ። ቀድሞ የነበረው አቅም ማጣት ብሶ ቤተሰቡ ቢቸገር ወይዘሮዎ ልጆቻቸውን ለማሳደግ ጉልበታቸውን ከፈሉ። እንዲያም ሆኖ ለእሳቸው የሚያስብ አልተገኘም። ሁሉም በአፍላነት ዕድሜ ተፈተነ፣ እናትን የሚረዳ በወጉ የሚያግዝ ልጅ ጠፋ ።

ሲቲና ዛሬም ድረስ የሚቆጫት የእናቷ ህይወት ነው፡፤እሳቸው ለልጆቻቸው መኖር ማንነታቸውን ሰጥተዋል ።ቤተሰቡ እንዳይቸገር፣እንዳይራብ ያልሆኑት የለም። እሷ ወጣትቷን ለውለታቸው አልከፈለችም። በየቀኑ መጠጣት፣ ማጨስና መቃም ልምዷ ነበር።

ዛሬ ያለፈውን ታሪክ መለስ ስትልበት ስለእናቷ አብዝቶ ይቆጫታል።በአንድ ወቅት ለደረሰባቸው የመኪና አደጋ ራሷን ተጠያቂ ታደርጋለች።በወቅቱ ህይወታቸው ቢተርፍም አንድ እግራቸውን አጥተው ነበር፡፤ከጉዳታቸው በኋላም እግራቸው አርተፊሻል ሆኖ ዓመታትን ለልጆቻቸው ዋጋ ከፍለዋል።

በወቅቱ የቤቱ ትልቅ ልጅ የቤተሰቡን ሀላፊነት ተረክቦ የሙት አባቱን ድርሻ ተወጥቷል። ታናናሾቹን እንደ ልጆቹ እያየ ፣ ወጣትነቱን፣ አፍላነቱን ቆጥቦ የቤቱ ሻማ ሆኗል። ሲቲና ግን ይህ ሁሉ አይገባትም። የእሱን ልፋት ድካም ከምንም አትቆጥርም።

ሌላው ወንድሟ እንደእሷው በሱስ የተጠመደ



ወጣት ነበር ። እናት ከክፉ ባህሪይው ሊመልሱ ብዙ ታግለዋል።ከሌሎች እንዳይጋጭ፣ ሰላማዊ እንዲሆን ያልሞከሩት የለም።

ከዓመታት በኋላ ሲቲና በዕድሜ በሰለች። ይህ ጊዜ ከፍቅር ጓደኛ አጣምሮ ከትዳር፣ ቁምነገር አደረሳት። እናት አሁንም ‹‹ደከሞኛል›› አላሉም፣ፈጽሞ አልራቋትም። ከጎኗ ሆነው ፍቅራቸውን ለገሷት።የትዳሯ ቀኝ እጅ ሆነው ‹‹አለሁሽ ››አሏት።

የሲቲና የትዳር ህይወት ከአውቶቡስ ተራ ይጀምራል። ባለቤቷ የስራ ሰው ነው። ድለላ እንጀራው ከሆነ ቆይቷል። እሷን ጨምሮ አንድ ልጃቸውን በወጉ ለማሳደር ሮጦ ያድራል። ስለኑሮ አስባ አታውቅም። እናቷም ከጎኗ አልራቁም። በችገራት እየጠየቁ፣ በጎደለው እየሞሉ፣ አብረዋት ዘለቁ ። ለሲቲና የእሳቸው መኖር ችግር ያቀላል። ከሰው ያውላል። እሷ እንዳሻት ሆና ለመግባት እናት የልብ አድርሰዋል።

ሲቲና አሁን ሁለተኛውን ልጅ አርግዛለች ። ከጎኗ ባልና እናቷ አልራቁም ፡ ያሻትን እየሞሉ፣ የጠየቀችውን ያቀርባሉ። ባተሌው ባለቤቷ ሌት ተቀን ይለፋል። ቤተሰቦቹ ያላቸው የሞላቸው ቢሆኑም ከእነሱ አይፈልግም። ለአንድ ልጁና ወደፊት ለሚወለደው ህጻን አርቆ ያስባል። የእሱ መስራት ለራሱ ቤተሰብ መድህን ነው። የእሱ መድከም ለወደፊት ህይወቱ ህይወት ነው።

ሲቲና ያለፈችበትን አትረሳም። ድህነት ለእሷ ብርቅ አይደለም። ማጣት ይሉትን አሳምራ ታውቀዋለች። እሷና ወንድሞቿ ከአጉል ባህሪያቸው ጋር ችግር ሲፈትናቸው ኖሯል። ዛሬ ላይ ሲቲ ትዳር ይዛለች። ስለቤተሰቧ እያሰበች ፣ እሷም ለጎጇዋ ታቅዳለች። ለትንሹ ልጇዋና ፤ላልተወለደው ህጻን ትጨነቃለች።

አንድቀን ግን ህልሟን የሚያጨልም፣ ውጥን ዕቅዷን የሚሰብር ክፉ አጋጣሚ አገኛት። ‹‹የቤቴ ራስ፣ ትዳሬ›› ያለችው አጋሯን ድንገቴ ሞት ነጠቃት። ቅስሟ ተሰበረ፣ ቀኗ ጨለመ። የተረገዘ ልጁን ሳያይ ሞት ስለወሰደው ባለቤቷ አምርራ አለቀሰች፣ክፉኛ አዘነች።ሲቲና ገና የስድስት ወር ነፍሰጡር ናት። ድንገቴው ሀዘን ግራ አጋብቷታል። ትይዘው ትጨብጠው አጥታለች።

አሁን ለሲቲና ህይወት ቀላል አይደለም፤ ራሷንና ቤተሰቦቿን ለማኖር ልፋት ድካም ይጠብቃታል። ከዚህ በኋላ በባሏ ትከሻና ሀሳብ ማደር አይኖርም። መለስ ብላ የእናቷን ልፋት፣ ድካም አሳታወሰች። እሷና ወንድሞቿ አባታቸውን በልጅነት ዕድሜያቸው አጥተዋል፤ እናት እነሱን ለማሳደግ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል። ጎንበስ ቀና ብለው ጎዶሎ ሞልተዋል።አሁን ደግሞ ይህ ዕጣ በእሷ ላይ ደርሷል። እናት ዛሬም ቢሆን ከጎኗ ናቸው ። ሀዘኗን ተጋርተው ‹‹አለሁሽ›› ብለዋታል። ያም ሆኖ ተዝናንታ አልተቀመጠችም። ጎዶሎውን ሞልታ የባሏን ድርሻ ለመሸፈን ፣ በጉልበት ስራ ዋለች።

### ስመኖር

ሲቲና ባለቤቷ እንደሞተ ውላ አላደረችም ። በየቤቱ ልብስ ማጠብ ጀመረች፡ ይህን ለማድረግ ውሀ የሞላ ጀሪካን መሸከም፣ በምልልስ ጉልበት መክፈል ግድ ይላታል። ይህ አጋጣሚ ግን ሌላ ችግር አስከተለ፣ ነፍሰጡሯ ያለዕረፍት መድከሟ ለእሷና ለጽንሱ ጤና እክል ፈጠረ።

እርግዝናዋ ስምንት ወር እንደያዘ ሲቲና ክፉኛ ታመመች። ጠዋት ማታ ጎኗን እየሸነቆረ ምኾት ለነሳት ህመም ፈጥና ሆስፒታል ደረሰች። ሀኪም ዘንድ በቀረበች ጊዜ ህጻኑ በአቀማመጡ ቦታውን እንደለቀቀ ተነገራት። ደነገጠች ፣ አተርፍ ባይ አጉዳይነቷ ዋጋ አስከፈላት። ወደ ጤናዋ ለመመለስ ቀናትን በቆጠረ ህክምና በስቃይ ከረመች።

ሲቲና ዘጠኝ ወር ስኪሞላት ከስራ አልራቀችም። በተገኘው ሁሉ እየገባች ጉልበቷን ትከፍላለች፤ ገንዘብ ይዛ ለመመለስ ከታዘዘችው ትውላለች።ይህ ሁሉ ሲሆን እንደ ነፍሰጡር በወጉ ‹‹ልብላ ልጠጣ›› አትልም።አንዳንዴ ርሀብ ሲጸናባት ጽንሱ አይንቀሳቀስም። እንዲህ ባጋጠማት ጊዜ ትደነግጣለች፡፤ ተመልሳ እንደማትሰራም ለራሷ ትወስናለች። ግን አትችልም።ህይወት ዳግም ያሮጣታል። አንዳንድ ልበ ቅኖች ችግሯን አውቀው ያጎርሷታል፡ ይህኔ ዛሬን ትረሳለች፤ መልሳ የነገ ውሎዋን ታስባለች፡፤

### ጨለማ የዋጠው ደስታ

ከፉዎቹ የችግር ቀናት እንዳለፉ የሲቲና ሁለተኛ ልጅ በሰላም ተወለደ። ለእሷ ይህ ጊዜ ድብልቅልቅ ስሜት ነበረው። አዲሱን ልጅ ስትቀበል ከደስታዋ ሀዘኗ አመዘነ፤ ፈገግታዋን ዕንባዋ ዋጠው ፣ ሳቋን ለቅሶዋ ነጠቀው። ልጇን ታቅፋ ባሏን አስታወሰች ፤ዛሬን ከጎኗ ቢኖር የሚሆነውን እያሰበች አነባች ። ክፉኛ ሆድ ባሳት።

የባሏ ቤተሰቦች ያላቸው ፤የሞላቸው መሆኑን ታውቃለች፡፤በቅርቧ ቢገኙም ችግሯን ይዛ ፊታቸው መቆም አልፈለገችም። ጓደኞቹ ያዋጡላትን ጥቂት ገንዘብ ይዛ መሮጥ ያዘች ። በአራስ ጎኗ ልብስ ማጠብ፣አሻሮ መቁላት ጀመረች። በደረቷ ጀብሎ ይዛ ማስቲካ ከረሜላ ሸጠች።

እናቷ ልጆቿን ይይዛሉ፣ እሷ ከሌላ ስራ የተረፋትን ጉልበት በድንጋይ ሸከማ ታውለዋለች። ሰርታ ስትገባ እጇ ባዶ አይሆንም። ለቤቷና ለልጆቹ የጎደሎውን ትሞላለች፣ ሲነጋ በትናንቱ ድካም ለመመለስ ጸንታ ትቆማለች። ጥቂት ጊዜያትን እንዲህ በድካም አለፈች። እናቷ ሁሉን ትተው ከእሷ ናቸው። እሷም ለሁለቱ ህጻናት ብቸኛ ተስፋቸው ናት።

አሁን ልጇ፣ቿ ትምህርት ቤት መዋል ጀምረዋል። የእሷ መጥቆር መከሳት ለእነሱ ነውና ድካሟ ልፋ አይሰማትም።ጥቅት ቆይቶ ትንሹ ልጅ ታመመ። እናት በየቀኑ ግንባሩን እየዳሰሰች ‹‹አይዞህ›› ትለዋለች። እያደር ግን የልጁ ጉዳይ አሳሳቢ ሆነ። ህመሙ ሰላም ነሳው፤ ይዛው ሀኪም ፊት ቀረበች ። የህክምናው ውጤት በጭንቅላቱ ውስጥ የነርቭ ችግር መኖሩን አመለከተ ። ልጁ ሲጫወት የወደቀ ቢሆንም ይህን ደብቆ አልተናገረም። እንዲህ መሆኑ ለሲቲና ስጋት ሆነ ልጇን እንዳታጣው ፈራች ።የጭንቅ ዓመታት አለፉ።

### ዛሬን

አሁን የሲቲና ሁለት ልጆች ወጣቶች ሆነዋል። የመጀመሪያው ሀያአንድ፣ ሁለተኛው ደግሞ አስራስምንተኛ ዓመቱን ይዟል። ሁለቱም ለስራ ደርሰዋል። እናታቸውን ለማገዝ፣ ከድካም ለማሳረፍ የሚያንሱ አይደሉም። ዛሬም ግን ሁለቱም ለእናታቸው ልጆች እንደሆኑ ነው ።

አሁንም ልጆቿን እናት ሲቲና ከትከሻዋ አላወረደቻቸውም። ዛሬም የእሷን እጅ ያያሉ። አሁንም ከእሷ ይጠብቃሉ። ሁለቱም ስለነገ ያስቡ አይመስልም። ከራሳቸው ይልቅ የእናታቸውን ትኩስ እንጀራ ይናፍቃሉ። በዕድሜቸው ከመስራት ይልቅ የእናታቸውን ጉልበት ይጠብቃሉ።

ሲቲና ግን ይህ ሁሉ ምንም መስሏት አያውቅም። ዛሬም ስለ ልጆቿ ልፋቷ ቀጥሏል። እሷም እንደ እናቷ ታትራ፣ ለፍታ በላቧ ወዝ ታሳድራቸዋለች። በጉልበቷ ድካም ታኖራቸዋለች ። ሁሌም ስለነገ ስታስብ ከልጆቿ አጣምራ ነው። እነሱን ለማስተማር ፣ ከቁምነገር ለማድረስ ሰልችቷት አያውቅም ።

አሁን ትናንት ብዙ የሆኑላት ደግ እናቷ ከጎኗ የሉም ። ስለእሳቸው ብዙ ቢቆጫትም ከመልካምነታቸው ተምራለች፤ ስለእሷ የከፈሉትን ዋጋ በልጆቿ ልትደግም፣ በራሷ ህይወት ልታሳይ ዛሬን እንደነቃች ነው ።‹‹ለላም ቀንዷ አይከብዳት›› ሆኖ ‹‹ልጆቼ ደርሰዋል፣ ይበቃኛል›› ብላ አልተወቻቸውም። ዛሬም ለእሷ ልጆች ናቸው። አሁንም ከእጇ አልወጡም፤ ከዓይኗ አልራቁም።

ሁለተኛው ልጇ በልጅነቱ የደረሰበት ጉዳት ዛሬ ድረስ ተከትሎታል።ይህ ችግር እናት ሲቲናን ሲያሳስባት ኖሯል። በቅርብ ጊዜ ያገኘው ህክምና ግን ተስፋ ሰጪ ነው። እንዲህ መሆኑ ከማንም በላይ እናትን በተስፋ አኑሯል።

ወይዘሮ ሲቲና ቤት ዛሬም ችግር ነቅሎ አልወጣም። በወር ትንሽ ደሞዝ ከሚከፈላት ቦታ የጽዳት ስራ አላት። ገቢው ሶስት ነፍሶችን አጥግቦ አያሳ ድርም። ዛሬ ቢሞላ ነገ ጎዶሎው ይበዛል። አሁን ቢገኝ ኋላ የሚያሳስብ፣ የሚያስጨንቀው ይበዛል። ሲቲና ልክ እንደትናንቱ ሩጫዋን ይዛለች።

አሁንም አስኪደክማት ትሮጣለች፤ ለመኖር በአማራጮች ሁሉ ትገኛለች። እንዲሁ ሆኖ ኑሮን ለማሸነፍ ደክሟት አያውቅም። አንዳንዴ ደግሞ ከእጅ ይጠፋል፣ ከቤት ይጎድላል፤ ልምዱ ሲቀር ፣ የታሰበው ሲጠፋ ይከፋል፤ ያስተክዛል። አጋጣሚው ባስ ሲል አይኖች ይማትራሉ። እግሮች ከአንድ ሰፍራ ያዘወትራሉ። እንዲህ መሆኑ ለጎደለው ሆድ፤ ላጣው እጅ መፍትሄ ያመጣል።

በቅርቡ በልደታ ክፍለከተማ አካባቢ የተከፈተው የምገባ ማዕከል እናት ሲቲናን የመሰሉ ወገኖችን ያስታውሳል። በራባቸው ጊዜ ጎራ ብለው ይጎርሱበታል። ቢሻቸው የያዙትን ቋጥረው ሌሎች ያቃምሳሉ። ቢያንስም ይህ ቁራሽ ዛሬን ያሳድራቸዋል። ነገን ያሻግራቸዋል።

አንዳንዶች በቀን ለአንዴ ቀምሰው የማያድሩ ምስኪኖች ናቸው። ሮጠው መስራት፣ ያልሆነላቸው በርካቶች ደግሞ በሚያገኙት በረከት ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ፤ እንደ ሲቲና አይነቶቹም ምገባውን ይመርጡታል። በዕድሜ ባይደከሙም የዕለት እንጀራው ለእጃቸውን መንጣት፣ ለቤታቸው ማጣት መፍትሄ ሆኗል። ሰርተው፣ ሮጠው ቢያድሩም እንጀራው እንጀራቸው ነው። ቀን አልፎ ፣ ነገ አስኪነጋ ተስፋቸው ሆኗልና።

**ከኢትዮጵያ የጤና መድህን አገልግሎት**
**ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም**

# ስልታዊ የጤና አገልግሎት ግዢ ለሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት ቀዳሚ ተግባር ኅብረተሰቡ ለህክምና በሚያወጣው ወጪ ምክንያት ላልታሰበ ወጪ እንዳይጋለጥ ቀድሞ በሚሰላ የክፍያ ስልት መሠረት መዋጮ እየከፈሉ አባል የሚሆኑበት የጤና ክፍያ ሥርዓት ነው። ይህንን መተግበር ሲቻል ሁሉም ዜጋ የጤና መድህን አባል ሆኖ በሚፈልገው ማዕቀፍ ውስጥ፤ በማንኛውም ሰዓት ህመም ሲሰማው ያለምንም ወጪ ጫና፤ ህመሙን ብቻ በማሰብ መታከም የሚችበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህ ማለት እያንዳንዱ ሰው ባልታሰበ ወጪ ለኪሳራ ሳይዳረግ ጥራቱ ሳይራቆት አገልግሎቱን ለማግኘት የሚያስችለው ይሆናል። በተጨማሪ የጤና መድህን በመላው ሀገሪቱ ተግባራዊ መደረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተተገበረ የሚገኘው ጤና ለሁሉም የሚል መርህ ተግባራዊ እንዲሆን ያስችላል።

ነባራዊው ሁኔታ የሚያሳየን ግን ብዙ ሰዎች ወደ ጤና ተቋማት ህመም ገጥሟቸው የሚሄዱት ተዘጋጅተውበት አይደለም፡፡ በዚህም በአንድ ወገን ላልታሰበ ወጪ የሚዳረጉ ሲሆን በሌላ በኩል እጃቸው ላይ ወደ ህክምና ጣቢያ ለመሄድ የሚያስችላቸው በቂ ገንዘብ ከሌለ ‹‹ከዛሬ ነገ›› ገንዘብ አግኝቼ እታከማለሁ እያሉ ሲቆዩ ህመማቸው ተባብሶ ለከፍተኛ ወጪ ለመዳረግና በቀላሉ መዳን የሚችለውም በሽታ ስር በመስደድ ለስቃይ ይዳረጋሉ።

ይህንን ሀገራዊ ችግር ለመቅረፍም ዜጎች የጤና መድህን ዋስትና በመግባት በየወቅቱ የሚጠበቅባቸውን ከፍለው ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቃል። በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ የጤና መድህን ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ ከጀመረ ከአስር አመታት በላይ ሆኖት በርካታ ተግባራትን ማከናወን የቻለ ቢሆንም ከሚጠበቅበት አኳያ ሲመዘን ብዙ ሥራዎች የሚቀሩት ይሆናል። በአሁኑ ወቅት በመንግሥት ለጤናው ዘርፍ የሚመደበው ገንዘብ ሆነ በጤና መድህን አማካይነት ከማህበረሰቡ የሚሰበሰበው ገቢ በሀገሪቱ ተደራሽነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የጤና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አይደለም።

በመሆኑም በተቻለ መጠን የሚሰበሰበውን ገንዘብ ለታቀደለት አላማ በውጤታማነት ለመጠቀም በጤና መድህን የሚፈጸመው የጤና ግዥ አገልግሎት መረጃን መሠረት ባደረገና ስልታዊ በሆነ መንገድ ሊከናወን ይገባል። በአጠቃላይ ወደ ጤና ተቋማት የሚገባው ገቢ ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ ብሎም ወጪ ቆጣቢ እንዲሆንና በፍትሃዊነት ተዳራሽ እንዲሆን ስልታዊ የጤና አገልግሎት ግዥን ተግባራዊ ማድረግ የሚጠበቅ ይሆናል።

ፍትሃዊና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ ማለት አቅም በፈቀደ መጠን ለደሀውም ለሀብታሙም እንዲሁም በዕድሜና በጾታ ሳይለይ ማህበረሰቡ እኩል የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ማብቃት ማለት ነው። ለዚህም የጤና መድህን ሥርዓቱ

> **«ስልታዊ የጤና አገልግሎት ግዢን መተግበር ጥራቱ የተጠበቀና ፍትሃዊ የጤና አገልግሎት ለዜጎች ተደራሽ ለማድረግ ይረዳል።»**

ውጤታማ ለማድረግ የሀብት ማሰባሰብ ሥራ ከተከናወነ በኋላ ስልታዊ የጤና መድህን ግዢ ሥርዓት መፈጸም ይጠበቃል። ይህ ማለት እያንዳንዱ የጤና ተቋም በግምት ወይንም በቅድሚያ በሚደረግ ትንበያ ሳይሆን አንድን ሥራ ካከናወነ በኋላ ከጤና ተቋሙ የተሰበሰበን መረጃ መሠረት በማድረግ ክፍያ እንዲያገኝ የሚያስችል ይሆናል። በመሆኑም ገንዘቡ ሊሰጥ የሚገባው ጤና ተቋሙ ለኅብረተሰቡ የሰጠውን አገልግሎት መረጃ በመሰብሰብና ያንን መነሻ በማድረግ ይሆናል።

እስካሁን ባለው አሠራር መንግሥት «ፓሲቭ» የሚባለውን ዓይነት አሠራር ይከተል ነበር። ይህም ማለት ለምሳሌ ለአንድ ሆስፒታል የተወሰነ መጠን ያለው ገንዘብ ሲመደብ የሕዝብ ብዛትና በአካባቢው በጤና ረገድ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችና ሌሎችም ታይተው ነው። ነገር ግን በአንድ አካባቢ በስፋት የሚስተዋሉት የጤና ችግሮች በሌሎች አካባቢዎች ላይስተዋሉ ይችላሉ። ወረዳዎች አካባቢ ደግሞ ይኸው አሠራር ለጤና በሚል ብቻ ዝርዝር ሁኔታዎችን ከግምት ሳያስገባ በጀቱ የሚለቀቅበት አካሄድ አለ። ይህ የጤና አገልግሎትን ለሁሉም ተደራሽ ለማድረግ የተያዘውን እቅድ ለማሳካት የሚያስችል አይደለም። በመሆኑም ለኅብረተሰቡ እንዲቀርብ የሚያስፈልገው የጤና አገልግሎት መቅረብ ያለበት መረጃን መሠረት በማድረግ ነባራዊውን ሁኔታ የጤና ችግር ከግምት ያስገባ መሆን አለበት።

በመሆኑም ለጤና ተቋማት በጀት ሲለቀቅ ዝርዝር መረጃዎችን በመሰብሰብና መነሻ በማድረግ ፍኖተ ካርታ በማዘጋጀት ስልታዊ የጤና አገልግሎት ግዢ መፈጸም ይጠበቃል። ይህ አካሄድ ጤና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት መረጃን መሠረት በማድረግ ለሰጡት አገልግሎት ተገቢው ክፍያ እንዲደርሳቸው የሚያደርግም ነው። ይህንን መተግበር መቻል ኅብረተሰቡ በድንገተኛ ወጪ ጥሪቱን ሳያሟጥጥና ወደ ድህነት ሳይገባ አገልግሎቱ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችለው ይሆናል።

**ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም**
**ጋር በመተባበር በየሣምንቱ የሚታተም**

# ከአምስት አመት መከራ በኋላ በእንባ ጠባቂ የታበሰ እንባ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አቶ አብዱ ኑረዲን መሀመድ በከፋ ዞን ዴቻ ወረዳ ጉንድራ ሾራ ቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በመሆን ለዘጠኝ አመታት አገልግለዋል። ለዘጠኝ አመታት በትጋትና በታማኝነት ሥራቸውን ሲያከናውኑ ቢቆዩም ባላሰቡት አጋጣሚ የተፈጠረው ነገር ግን ሕይወታቸው ወደ ፈተና እንዲያመራ ያደርገዋል። ጉዳዩ ደግሞ እንዲህ ነበር፤ በዞኑ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ለአርሶ አደርና ለወጣት መሬት እየተከፋፈለ የይዞታ ማረጋገጫ የመሬት ባለቤትነት ደብተር ይሰጥ ነበር። አቶ አብዱ በሥራ አስኪያጅነት በሚመሩት ቀበሌም ይህ ሥራ ሲከናወን በቀበሌው ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ሌሎች አመራሮች አርሶ አደር ደብተር ላይ ካለፈቃድ የወረዳው ኃላፊ ሊያደርገው የሚገባውን ማህተም በቀበሌው አድርገው የባለቤትነት ደብተር ሰጥተው በመገኘታቸው ክስ ይመሰረትባቸዋል። ምንም እንኳን አቶ አብዱ ተሠራ በተባለው ወንጀል ተሳታፊ ባይሆኑም የተመሠረተው ክስ ግን እሳቸውንም ተጠርጣሪ በማድረጉና በስልጣን እስከነበሩ ድረስ እርስዎንም ይመለከትዎታል በሚል በፖሊስ ተይዘው ለእስር ይዳረጋሉ። የወረዳ አመራሮችም ፍርድ ቤት ቀርበው ነገሩ ሥራ አስኪያጁንም ይመለከታቸዋል ብለው በመናገራቸው ውሳኔ ተሰጥቶባቸው በማረሚያ ቤት እንዲቆዩ ይደረጋል። አቶ አብዱ ግን ነገሩን አለመሥራታቸውንና በሕግ ሊጠየቁበት የሚያስችል እንዳልሆነ ስለሚያውቁ ማረሚያ ቤት ሆነው ይግባኝ በመጠየቅና ያላቸውን መረጃ ለፍርድ ቤቱ በማቅረብ ሁለት ወር ከዘጠኝ ቀን ከታሰሩ በኋላ በፍርድ ቤቱ በነፃ እንዲለቀቁ ይደረጋል።

> **ውሳኔው የአምስት አመት ደመወዜን 214 ሺ 831 ብር እንዲከፈልም ያዝ ስለነበር በተገቢው ደረጃ እንድካስ አድርጎኛል በአሁኑ ወቅት ኑሮዬ ብቻ ሳይሆን በጭንቀት ብዛት ወደሌላ ነገር ሲያመራ የነበረው አእምሮዬም ተስተካክሏል።**

በዚህ ዓይነት ነፃነታቸውን ካወጁ በኋላ ነፃ የወጡበትን የፍርድ ቤት ማስረጃና ከወንጀሉ ነፃ ለመሆናቸው ለፍርድ ቤቱ ያቀረቡትን ማስረጃ ጨምረው በመያዝ ወደ ሥራቸው ለመመለስ ቢጠይቁ የወረዳ አመራሮች ከአምስት ቀን በላይ በሥራ ገበታህ ላይ ስላልተገኘህ ከሥራ ተሰናብተሃል ልንመልስህ አንችልም የሚል ምላሽ ይሰጧቸዋል። አቶ አብዱ የተሰጣቸውን ምላሽ በመያዝ ወረዳም፤ ዞንም ይመለከተዋል ብለው ያመኑበት ቦታ ሁሉ ቢሄዱ ምንም መፍትሄ ሳያገኙ ይቀራሉ። ወደ ክልል ለመሄድ ደግሞ ብቸኛ የገቢ ምንጫቸው የነበረውን ደመወዛቸውን ሳያገኙ በእስር የቆዩ በመሆናቸውና እሳቸውን ጨምሮ አራት ቤተሰብ የሚያስተዳድሩ በመሆኑ የገንዘብ እጥረት አላንቀሳቅስ ይላቸዋል። ደብዳቤ ጽፎ ይግባኝ ለማለትም የሚኖሩበት ቀበሌም ከክልሉ መቀመጫ በጣም ርቀት ስላለው በቂ ገንዘብ ሳይዙ ለመሄድ የሚያስችላቸው ሁኔታ አልነበረም።

በዚህ የተነሳ በፍጹም ችግር ውስጥ ከነቤተሰባቸው በመሆን አምስት አመታትን ለማሳለፍ ይገደዳሉ። በእነዚህ አምስት አመታት አቶ አብዱ ሁሉንም ዓይነት ችግሮች አስተናግደዋል። ወደ ትውልድ ቀያቸውም ተመልሰው በእርሻና በሌሎች ሥራዎች ለመስማራት ቢያስቡም ዘጠኝ አመት በመንግሥት ሥራ ለዚያውም በቀበሌ ሥራ አስኪያጅነት ሲሠሩ ስለነበር የቤተሰባቸው መሬት ለሌሎቹ ልጆች ተከፋፍሎ ሁሉም የራሱን ሕይወት ይመራበት ስለነበር የሚሆን ነገር አልነበረም።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ በአንዲት ገደኛ ቀን ቴሌቪዥን ሲከታተሉ እንባ የሚያብስ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ የሚባል ተቋም እንዳለና ስለሚሠራቸው ሥራዎችም ይሰማሉ። ወዲያውም ስልክ ይፈልጉና ያለውን የደረሰባቸውን ነገር ያስረዳሉ ሁኔታውን የሰማው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ባለሙያም በቃል የነገሩትን ነገር ሊያረጋግጥ የሚችል አለኝ የሚሉትን መረጃ በመሉ ይዘው እንዲመጡ ይነግራቸዋል። እሳቸውም ከአምስት የሰቆቃ አመት በኋላ ብልጭ ያለችውን የተስፋ ጭላንጭል በመተማመን ፍርድ ቤቱ ነፃ መሆናቸውን አረጋግጦ ከሰጣቸው ማስረጃ ጀምሮ ያላቸውን ሁሉ በማደራጀት ወስደው ያስረክባሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምም የደረሰውን መረጃ በማሰባሰብና በማደረጀት ወደሚመለከታቸው አካላት በመሄድ የመፍትሄ ሀሳብም አክሎ ጉዳዩ እንደ አዲስ እንዲታይ ያደርጋል። በተደረገው የማጣራትና የክትትል ሥራም የተወሰነው ውሳኔ ዳግም እንዲፈተሽ በመደረጉ አዲስ ዜና ለአቶ አብዱ ይደርሳቸዋል። እውነትም አቶ አብዱ ያለ ግብራቸው ግብር ተሰጥቷቸው ያለሀጢያታቸው ሲንገላቱ እንደነበር በመታመኑ ወደሥራቸው እንዲመለሱ ይወሰናል። ይህ ውሳኔ ለአቶ አብዱ ገንዘብና ሥራ የሚያገኙበት ብቻ ሳይሆን ነፃነታቸውንም ያወጁበት እንደነበር እንዲህ ይገልጻሉ።

«ውሳኔውን ስሰማ ከመቃብር የወጣሁ ያህል ነው የተሰማኝ፤ በእውነትም ደግሞ የነበርኩበት ሁኔታ ከመቃብር ያልተናነሰ ነበር። በተጨማሪ ውሳኔው የአምስት አመት ደመወዜን 214 ሺ 831 ብር እንዲከፈልም ያዝ ስለነበር በተገቢው ደረጃ እንድካስ አድርጎኛል በአሁኑ ወቅት ኑሮዬ ብቻ ሳይሆን በጭንቀት ብዛት ወደሌላ ነገር ሲያመራ የነበረው አእምሮዬም ተስተካክሏል። ደካማ እናቴንም እየጦርኩ ቤተሰቤንም በሰላም እያስተዳደርኩ እገኛለሁ ይላሉ።»

አቶ አብዱ እሳቸው ያገኙትን ዕድል ሌሎችም እንዲያገኙ የሚከተለውን መልዕክት አስተላልፈዋል። አቅም የሌለው ሚድያ የማይከታተል በርካታ የአስተዳደር በደል የተፈጸመበት ሰው በየቦታው አለ። ብዙዎቻችን ስለ እንባ ጠባቂ ተቋም ሥራ መረጃው የለንም። በመሆኑም ተቋሙ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ባይሳካለት እንኳን ቢያንስ በዞን ደረጃ ቅርንጫፍ በመክፈት ተደራሽ ሊሆን ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ ራሱንም የማስተዋወቁን ሥራ በስፋት መሥራት አለበት ሲሉ አሳስበዋል።